

‹‹ልጆቼ አንድ ቤት ተሰብስበው፣ መኝታ አግኝተው የሚያርፉበትን ቀን እናፍቃለሁ››

- ወይዘሮ ብርሃኔ ድጉማ

ገጽ 16

በጦርነት የወደሙ መሰረተ ልማቶች መልሶ ግንባታ - በአማራ ክልል

ገጽ 14


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 105 ታኅሣሥ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# የቦይንግ 737 ማክስ አውሮፕላን የአደጋ መንስኤ የሶፍትዌሩ ችግር መሆኑ ተረጋገጠ

## - የአውሮፕላን አደጋው የመጨረሻ የምርመራ ውጤት ይፋ ተደርጓል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ንብረትነቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሆነው ቦይንግ 737 ማክስ 8 የመንገደኞች አውሮፕላን የመከስከስ ምክንያት ‹MCAS› ኤምካስ የተሰኘ ሶፍትዌር እንደነበር የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትሯ ዳግማዊት ሞገስ ገለጹ። ንብረትነቱ የኢትዮጵያ የሆነው ET 302 ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላን አደጋ የመጨረሻ የምርመራ ሪፖርት ይፋ ተደርጓል።

የትራንስፖርት ሚኒስትሯ ዳግማዊት ሞገስና የአውሮፕላን አደጋ ቢሮ ኃላፊ ኮሎኔል አምድዬ አያሌው ትናንት የአውሮፕላኑን አደጋ የመጨረሻ ሪፖርት አስመልክቶ መግለጫ ሰጥተዋል።

በ2011ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የሆነው ቦይንግ 737 ማክስ 8 አውሮፕላን ላይ የደረሰው አደጋ የመጨረሻ የምርመራ ውጤት ይፋ በተደረገበት ወቅት ሚኒስትሯ እንደገለጹት፤ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ተነስቶ ወደኬንያ ሲበር የነበረው የመንገደኞች አውሮፕላን ከበረራ በመጥፋቱና ከአየር ትራፊክ ግንኙነት በመቋረጡ የፈልጎ ማዳን ቡድን ፍለጋ በማድረግ አውሮፕላኑ የተከሰከሰበትን ቦታ ከቦሌ 28 ማይል ርቀት ላይ ማግኘቱን አስታውሰዋል።

አውሮፕላኑ በአደጋ መውደቁ ከተረጋገጠ በኋላ በስምምነቱ መሰረት የምርመራ ቡድን በማቋቋም ሲሰራ መቆየቱን ሚኒስትሯ አስታውሰው፤ ቦይንግ 737 ማክስ

የቦይንግ 737 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- ገበቡ ገብሬ

ዳግማዊት ሞገስ

# ኅብረቱ ስሰላም ስምምነቱ ተፈፃሚነት የተወሰዱ እርምጃዎችን አደነቀ

## - በመጪዎቹ ቀናት የሰላም ስምምነቱ አተገባበር ይገመገማል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ሕብረት፣ የኢትዮጵያ መንግሥትና የሕወሓት ባለስልጣናት ለስምምነቱ ተፈፃሚነት የወሰዷቸውን አወንታዊ እርምጃዎች አደነቀ።

የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን፤ የፌዴራል መንግስት እና የሕወሓት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች የሰላም ስምምነቱን አስመልክቶ ሁለተኛው ዙር ውይይት በትናንትናው ዕለት በናይሮቢ ማካሄዳቸውን ገልጿል።

በአፍሪካ ዩኒየን የግጭት አፈታት ዳይሬክተር አልሃጂ ሳጂባህ በሰጡት መግለጫ፤ የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ሁለቱ አካላት ለወሰዷቸው አዎንታዊ እርምጃዎች አድናቆት ችረዋቸዋል። የኢትዮጵያን ሰላም፣ ደህንነት እና መረጋጋት ለመመለስ

ኅብረቱ ስሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



የፌዴራል መንግስት እና ሕወሓት በደቡብ አፍሪካ የሰላም ስምምነቱን በተፈራረሙበት ወቅት











# «የተፈጠረው የሰላም ዕድል ወደ ውጤት እንዲቀየር ሁሉንም ያካተተ ጠንካራ አስተዳደር መፈጠር አለበት»

- አቶ መኮንን አብርሃ
የቀድሞ የዋጅራት ወረዳ አስተዳዳሪ

ሄርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የተፈጠረው የሰላም ዕድል ውጤታማ እንዲሆንና ህብረተሰቡ ከሰላም ተጠቃሚ እንዲሆን በክልሉ ሁሉንም አካላት ያካተተ ሕግና ስርአት

«የተፈጠረው የሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አዲሱ የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ የአቅርቦት ችግርን እንደሚቀርፍ ይታመናል

ገጽ 4








# የሀገር ሽማግሌዎች ለሀገር ሰላምና ልማት ለሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ዋጋ መስጠት ይገባል

ገጽ 3

ዜና

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN MEDIA AUTHORITY

# ባለሥልጣኑ ኃላፊነት የጎደላቸው መልእክቶችን በሚያስተላልፉ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ላይ ርምጃ እንደሚወስድ ገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በመገናኛ ብዙኃን ተሠራጭተው የዜጎችን ሰላምና አብሮነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉና ኃላፊነት የጎደላቸው መልእክቶችን በሚያስተላልፉ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ላይ በሕጉ መሠረት ርምጃ እንደሚወስድ የመገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን አስታወቀ።

ኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ክትትል ክፍል ግኝቶች ከዜጎችና ከተቋማት የደረሱት ቅሬታዎችና ጥቆማዎች እንዳመለከቱት፤ የተወሰኑ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚጠበቅባቸው ሕጋዊ፣ ማኅበራዊና ሙያዊ ሥነ ምግባር ያፈነገጡ መልእክቶች እንደሚተላለፉባቸው ተስተውሏል። አልፎም የዜጎችን የመቻቻልና አብሮ የመኖር እሴት የሚሸረሽሩ፣ ለሁከትና ግጭት የሚጋብዙ፣ በግለሰቦችና በማኅበረሰቦች ላይ አካላዊ ጥቃት እንዲፈጸም የሚያነሣሡ ንግግሮች ተሠራጭተውባቸዋል።

እንደ መግለጫው ማብራሪያ፤ በመገናኛ ብዙኃን ተሠራጭተው የዜጎችን ሰላምና አብሮነት አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉና ኃላፊነት የጎደላቸው መልእክቶችን በሚያስተላልፉ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ላይ በሕጉ መሠረት ርምጃ ይወስዳል። ከተቋቋሙበት መርህና ዓላማ በተቃረነ አኳኋን በተለያዩ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን የሚፈጸሙ ሕጋዊና ሙያዊ የሥነ ምግባር ጥሰቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙ ባለሥልጣኑ በጥብቅ አሳስቧል። ባለሥልጣኑ ከሰሞኑ በተወሰኑ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ላይ የቀረቡለትን ቅሬታዎች ከሕግና ከሙያ ሥነ ምግባር አንፃር መርምሮ እንደ አስፈላጊነቱ ውጤቱን ለፍትሕ አካላት እንደሚያቀርብ አስታውቋል።

የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ለኢትዮጵያውያን መልካም ዕሴቶች መጎልበት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው መንግሥት ያምናል ያለው መግለጫው፤ የዜጎችን ግብረገባዊነት፣ አብሮነትና ወንድማማችነትን የሚያጎለብቱ ማኅበራዊ ዕሴቶች ከማጠናከር፣ የሀገርን ሁለንተናዊ ሰላምና ዕድገት ከማረጋገጥ አንፃር የማይተካ ሚና ይጫወታሉ። መንግሥት ይሄንን ሚናቸውን በማመን ለተቋማቱ ሕጋዊ ዕውቅና በመስጠት ድጋፍና እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል ብሏል።

መንግሥት የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ሃይማኖታዊ አስተምህሯቸውን ለተከታዮቻቸው ሲያስተምሩ የሌሎችን ሃይማኖትና እምነት አክብረው እንዲያስተምሩ፣ ከተቋቋሙለት ሃይማኖታዊ ጉዳይ ውጪ ሌሎች ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ጉዳዮች በመገናኛ ብዙኃኑ ማስተላለፍ የለባቸውም። እንዲሁም ከጥላቻ፣ በዜጎች መካከል አብሮ መኖርን ከሚያውክ፣ በማንኛውም አግባብ ሁከትና ግጭት ሊቀሰቅስ ከሚችል፣ በዜጎች ላይ ሥነ ልቡናዊም ሆነ አካላዊ ጥቃት እንዲደርስ ከሚያነሳሳ ንግግርና ከመሰል አሉታዊ መልእክቶች ታቅበው እንዲሠሩ ይጠበቅባቸዋል ብሏል የባለስልጣኑ መግለጫ።

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት፤ እንዲሁም በመገናኛ ብዙኃን አዋጅ 1238/2013 አንቀጽ 70፤ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ በተደነገገው መሠረት፣ የሃይማኖት መገናኛ ብዙኃን ማኛውንም ሃይማኖት ተኮር ፕሮግራም ሲያሠራጩ በተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት ማነሳሳት፤ የሌሎችን ሃይማኖት ወይም እምነት ማንኳሰስ፣ ወይም በሃይማኖቶች ተከታዮች መካከል አለመቻቻል እንዲፈጠር መቀስቀስ እንደሌለባቸው በግልጽ መቀመጡን መግለጫው አትቷል።



ፎቶ፡- ሐዱሽ አብርሃ

በሚስጥራዊ መረጃ ምደባና ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ ላይ ውይይት ሲደረግ

# አዋጁ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለሕዝብ ጥቅምና ለሀገር ደህንነት ለማዋል ያስችላል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት አዋጁ የሚይዛቸው የመንግስት መረጃዎች ለህዝብ ጥቅምና ለሃገር ደህንነት ብቻ እንዲውሉ ያስችላል ሲሉ የአገልግሎቱ ምክትል ጄኔራል ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ ቶላ ተናገሩ።

የመንግስት ሚስጢራዊ መረጃ ምደባና ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ እና የቴክኖሎጂ ዝግጁነት ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ ትናንት በሸራተን አዲስ ሆቴል በተካሄደበት ወቅት ምክትል ጄኔራል ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ አዋጁ የመንግስት መረጃዎችን ለመመደብ እና ሚስጢራዊ መረጃዎች እንዲጠበቁ እንዲሁም እንዳይሰራጩ ለማስቻል የህግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት የሚያስችል ነው።

መረጃ በአግባቡ ከተያዘ ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም ይውላል። ነገር ግን በተቃራኒው ደግሞ በአላስፈላጊ ሰዎች ወይም ቡድኖች እጅ በሚገባበት ጊዜ ተመልሶ ለመንግስትም ሆነ ለሀገር ጉዳት የሚያስከትል ይሆናል ብለዋል።

መረጃዎች ቅደም ተከተል ተዘጋጅቶላቸው ወጥ የሆነ የጥበቃ ስርዓት ባለመኖሩ አሁን ሀገራችን ብዙ ጉዳቶች እያጋጠማት እንደሆነ በመጥቀስ፤ መረጃዎች ወጥተው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳት በማስከተል ላይ ይገኛሉ ብለዋል፤ ከዚህም አለፍ ሲል የመንግስት ወታደራዊ ዕቅዶች የኢኮኖሚ ፕሮግራሞችና የመሳሰሉ ጉዳዮች ተመልሰው ለህዝብና ለሀገር ደህንነት ጉዳት የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች እንደታዩ ገልጸዋል።

የዚህ ረቂቅ አዋጅ ዋና አላማ መንግስት መረጃን በማመንጨትና በመጠቀም ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ የሚያትት ሲሆን፤ በመንግሥት ውስጥ ያሉ ባለስልጣናትና ሰራተኞች አብዛኛውን መረጃ የሚያገኙት በተሰጣቸው የመንግስት ኃላፊነት እንጂ በግላቸው ባለመሆኑ እነኚህ አካላት የሚያወጧቸውን መረጃዎች ስርዓት ባለው መንገድ እንዲያስተዳድሩ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

መረጃዎች እጅግ ብርቱ ሚስጥር፣ ብርቱ ሚስጥር፣ ሚስጥርና ክልክል በሚል አራት ዋና ዋና ዘርፎች ለይተናል ሲሉም አስታውሰዋል።

እነዚህ አራት የመረጃ አይነቶች እንደየደረጃቸው የጥበቃ ስርዓት ይዘጋጅላቸዋል። ይህ ጥበቃም የአካላዊና የሳይበር ጥበቃ ሲሆን፤ ነገርግን በአዋጁ በተቀመጠው መሠረት በማይጠቀሙ አካላት ላይ ተመሳሳይ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው አዋጁ በዝርዝር እንደሚያስቀምጥ ምክትል ዳይሬክተር ጄኔራሉ አስታውሰዋል።

ውይይቱ የፍትህ ስርዓት ያልተበጀላቸውን የመረጃ አጠቃቀሞችን ለማስተካከልና ህዝብ ማግኘት ያለበትን የመረጃ ሚዛን ጠብቆ የሚያስኬድ ስርዓት ለመፍጠር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ መፍጠርን አላማ ያደረገ ነው ተብሏል።

በዓለም ሀገራት የመንግስት ሚስጢራዊ መረጃዎች ምደባና ጥበቃ ስርዓት ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ ሰንብቷል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ይሄንን የአሰራር ስርዓት በህግ ማእቀፍ ውስጥ አስገብታ ተግባራዊ ባለማድረጓ ለተለያዩ ሚስጢራዊ መረጃዎች ምዝበራ ተጋልጣ እንደነበር በውይይቱ ተመልክቷል።

በአሁኑ ወቅት ይሄንን ችግር ይፈታል የተባለ የመንግስት ሚስጢራዊ የመረጃ ምደባና ጥበቃ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችል ዘንድ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች እና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ውይይት ተደርጓል።

# ዲጂታል ኢኮኖሚውን ለመገንባት የሚያስችል ስምምነት ተደረገ

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል ስምምነት በአፍሪኮም ቴክኖሎጂ እና በአሸዋ ቴክኖሎጂ ሶሉሽን መካከል ተደረገ።

በትናንትናው እለት በአይሲቲ ፓርክ በተከናወነው በዚሁ ስነስርዓት ላይ እንደተገለጸው፤ ስምምነቱ በቴክኖሎጂው ዘርፍ በ2025 ዲጂታል ኢትዮጵያን ለመገንባት የተያዘውን እቅድ እውን ለማድረግ ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

የአፍሪኮም ቴክኖሎጂ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ባህሩ ዘይኑ እንደተናገሩት፤ የተደረገው ስምምነት አብሮ በመስራት ትልቅ ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ያለመ ሲሆን ህብረተሰቡ በቀላሉ መንገድ ቴክኖሎጂን መጠቀም እንዲችልና ከከተማ ባሻገር በገጠር ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን በማካተት አቅማችንን ለመገንባት ያስችለናል ብለዋል።

ስምምነቱ በጋራ በመሆን ከኢትዮጵያ ባለፈ በአፍሪካ ሀገሮች ብሎም በአለም ላይ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ እና የማስፋፋት ስራ እንደሚሰሩም ዋና ስራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

አፍሪኮም ቴክኖሎጂ አይ ኤስ ኦ ሰርተፍኬት ያለው እንዲሁም በቴክኖሎጂ ዘርፍ ውስጥ ትልቅ ስራ እየሰራ ያለ ድርጅት እንደሆነም አቶ ባህሩ ተናግረዋል።

ከተመሰረተ 18 አመታትን ያስቆጠረ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ እንዲሁም አለም አቀፍ የዲጂታላይዜሽን ስራዎችን የሚሰራው ኩባንያው፣ ሶፍትዌሮችን በሀገር ውስጥ በመስራት የውጭ ምዛሬን ከማስገባት ባለፈ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬን የማስቀረት እንዲሁም ለዜጎች የስራ እድል በመፍጠር በጥሩ እድገት ላይ ያለ ኩባንያ እንደሆነ ገልጸዋል።

አቶ በሀሩ ኩባንያቸው ኢንዱስትሪው እንዲያድግ ከተለያዩ የአይቲ ኩባንያዎች ጋር ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን በኢትዮጵያ የሚል ማህበር በማቋቋም እየሰሩ እንደሆነም ተናግረዋል።

የአሸዋ ቴክኖሎጂ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ዳንኤል በቀለ በበኩላቸው፤ ኩባንያቸው በቴክኖሎጂ ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ ለብዙዎች የስራ እድልን በመፍጠር እና ጥሩ የሆነ የግብይት ስርአት እንዲኖር በኢትዮጵያ ውስጥ እየሰራ የሚገኝ የቴክኖሎጂ ድርጅት እንደሆነ ተናግረዋል።




ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

የውል ስምምነት ሲካሄድ

ከአፍሪኮም ቴክኖሎጂ ጋር የተደረገው ስምምነት የማህበረሰቡን ህይወት ቀላል እና የተሻለ ለማድረግ የተያዘውን አላማ እንደሚወጣ ስምምነቱን የፈጸሙ የአሸዋ ቴክኖሎጂ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ዳንኤል በቀለ ተናግረዋል።

“በአንድ አላማ በጋራ መስራት ረጅም ጉዞ ለመሄድ ይረዳል የሚል ጽኑ አላማ እና እምነት አለኝ፤ ለሀገራችን የሚጠቅም ብዙ የሰው እና የእውቀት ሀብት በመጠቀም በርካታ ስራዎችን በጋራ እንሰራለን” ብለዋል።

አቶ ዳንኤል ስምምነቱ በሀገራችን የነበረውን ኋላ ቀር የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የማዘመን ስራ በጋራ ለመስራት እንዲሁም በቴክኖሎጂ ዘርፍ የማህበረሰቡን ችግር የማቅለል እና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል ብለዋል።

ስምምነቱ የተለያዩ ስራዎችን በመፍጠር የማህበረሰቡን ህይወት ቀላል እና የተሻለ የማድረግ አላማ ያለው ሲሆን በ2025 ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ እንደሚሰራ አቶ ዳንኤል ገልጸዋል።

የአይሲቲ ፓርክን ከመሰረቱት ተቋማት ቀዳሚ እና አንጋፋ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች መካከል አንዱ አፍሪኮም ቴክኖሎጂ ነው ያሉት የአይሲቲ ፓርክ ዋና ስራ አስኪያጅ ሱራፌል ሽመልስ፤ ዲጂታል ኢትዮጵያ ለማሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ከተያዙት እቅዶች አንዱ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነው ብለዋል።

በሁለቱ ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች መካከል የተደረገው ስምምነት የእውቀት ሽግግር እና የስራ እድል ለመፍጠር ትልቅ አቅም እንደሆነም ጠቁመዋል።

አቶ ሱራፌል እንደገለጹት፤ እነዚህ ሁለት ተቋማት በጋራ ሲሰሩ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አላማ ሙሉ ለሙሉ ማሳካት ይችላሉ፣ የስራ ትስስር እና የቴክኖሎጂ እውቀቶችን ወደ አንድ ቦታ በመሰብሰብ ውጤታማ በማድረግ ለዜጎች የስራ እድል ፈጠራ ይረዳል። ፓርኩንም ከማሳደግ አንጻር ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል።

ዜና

# የሀገር ሽማግሌዎች ለሀገር ሰላምና ልማት ለሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ዋጋ መስጠት ይገባል

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- በልማትና ሰላም ብሎም በሃገር ህልውና ላይ ሁነኛ አስተዋፅኦ ያላቸው የሃገር ሽማግሌዎች ክብር ሊሰጣቸው እንደሚገባ የአነሲሞስ ፋውንዴሽን መስራች አቶ አረጋ ጌላ አስታወቁ። ያለፉና የሚያጣሉ ታሪኮችን ወደ ኋላ በመጣል የወደፊቷን ሰላማዊና የበለፀገች ኢትዮጵያን መገንባት እንደሚገባም አመልክተዋል።

አቶ አረጋ ጌላ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ በቀደሙት ዘመናት የሃገር በሃገር ሽማግሌዎች ትመራ የነበረ ሲሆን ህዝቡም እነሱ የሚሉትን አክብረው የሚፈፅሙ አለመግባባቶች የከፋ ደረጃ ላይ ሳይደርሱ ይፈቱ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ሽማግሌዎችን የማክበር እሴት እየተሸረሸረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ መደማመጥና ተከባብሮ መኖር አደጋች የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

‹‹በእኛ ባህል የሃገር ሽማግሌ የማህበረሰቡ የበላይ ነው። ሲሄዱ እንኳን መንገድ ይለቀቅላቸዋል። ለግድያ የሚፈላለጉ ወገኖችን ሳይቀር ያስታርቃሉ›› ያሉት አቶ አረጋ፤ አሁን ላይ ግን የሃገር ሽማግሌዎች የሚሰማቸው ማጣታቸውንና ሁሉም በየፊናው ያሻውን እየፈፀመ መሆኑ በየአካባቢው ግጭቶች እንዲበራከቱ ምክንያት መሆናቸውን አመልክተዋል። በመሆኑም በተለይ አሁን ያለውን ችግር መፍታት ከተፈለገ በተለይ ወጣቱ ሽምግሌዎችን ማክበርና ማዳመጥ አለበት።

በሀገር ህልውና ላይ ሁነኛ አስተዋፅኦ ያላቸውን ሽማግሌዎች ዋጋ ካሳጣናቸው አደጋው የከፋ በመሆኑ



አቶ አረጋ ጌላ

ተገቢው ክብርና ቦታ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ተናግረው ‹‹ለዚህ ደግሞ መንግስትን ብቻ መጠበቅ የለብንም፤ ከቤተሰብ ጀምሮ፤ መምህራንና የሚመለከተቻው አካላት በሙሉ የቀደመውን የመከባበርና የመደማመጥ እሴታችንን መመለስ ይገባናል›› ብለዋል። ይህንን ማድረግ በተለይ ከተቻለም በጥፋት መንገድ ያለውን ወጣት መታደግና የሃገርን ህልውና ማስቀጠል እንደሚቻል ጠቁመዋል።

አንዳንድ ጊዜ ያለፉ ታሪኮች ለፀብና ለግጭት ምክንያት ሲሆኑ እንደሚስተዋሉ ያስታወሱት አቶ አረጋ ‹‹የሚያጣላን ያለፈ ታሪካችን ከሆነ ያለፈው አለፈ ብሎ ስለወደፊቱ መነጋገሩ ነው የሚበጀን። ለምሳሌ የባሪያ ንግድ ወይም የፊውዳል ስርዓት አልነበረም፤ በደል አልተፈፀመም ብሎ ከመከራከር ይልቅ ያለፈ መጥፎ ታሪክን ወደኋላ ጥሎ የአሁኑንና የወደፊቱን ቀናችንን ነው ማሳመር ያለብን›› በማለት ተናግረዋል። ለተፈጠረው ነገር ይቅርታ ተጠያይቆ ወደፊት መቀጠል ካልተቻለና ሁሉም የየራሱን ጥግ ይዞ ከቀጠለ ሃገርን ማዳን እንደማይቻል አስገንዝበዋል።

እያንዳንዱ ሰው በስጋትና በጥርጣሬ የሚኖር ከሆነ እንደሃገር ለመቀጠል አስቸጋሪ እንደሆነ የተናገሩት አቶ አረጋ ‹‹ለዚህ ሁኔታ መፈጠር ደግሞ ሁላችንም ብንሆን ከተጠያቂነት አናመልጥም›› ብለዋል። በተለይ ሁሉም ሰላም ናፋቂ ህዝብ የሌሎች ቤትና ሰፈር ሲቃጠል በምናገባኝነት ችላ ከማለት ይልቅ ራሳቸውን ከጥፋት ከማቀብ ጀምሮ የተግባሩ ፈፃሚዎችንም ጭምር በመገሰፅና ሰላማዊ አካባቢ በመፍጠር ሃገርን መታደግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

‹‹በመሰረቱ ማንኛውም ሰው ቢሆን በሰላም ወጥቶ መግባትን አይጠላም። እያንዳንዱ ሰው ቢጠየቅ በሰላምና በፍቅር መኖርን ነው ቀዳሚ ምርጫው የሚያደርገው። ለሰላም የምንከፍለው ዋጋ ለጦርነት ከምንከፍለው በጣም በእጅጉ ያነሰ በመሆኑ ሁሉም ለሰላም መስራት አለበት›› ብለዋል። በተለይም ደግሞ ቁጭ ብሎ በመነጋገር የሚታጣ ነገር ባለመኖሩ ፈጥኖ ወደ ግጭት ከመግባት ይልቅ ለውይይት እድል መስጠት እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ‹‹አሁን ላይ የሚያጋጩንን ርዕሰ ጉዳዮች በየአካባቢያችን ቁጭ ብለን ብንነጋገር ይፈታሉ። ሰፈራችንን ሰላም ካደረግን ሃገራችንም ሰላም ትሆናለች›› በማለት ተናግረዋል።



# በዞኑ ተማሪዎችና መምህራን ሰብል ሰበሰቡ


**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የምሥራቅ ጎጃም ዞን ትምህርት መምሪያ እየጣለ ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ከ365 ሺ በላይ ተማሪዎችና ከ20 ሺ በላይ መምህራን የአርሶ አደሮችን ሰብል መሰብሰባቸውን አስታወቀ።

የዞኑ ትምህርት መምሪያ ኃላፊ አቶ ጌታሁን ፈንቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እየጣለ ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ከታህሳስ 10 እስከ ታህሳስ 14 ቀን 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ትምህርት ቤቶች ተዘግተው መምህራንና ተማሪዎች በዘመቻ የአርሶ አደሩን ሰብል የመሰብሰብ ሥራ አከናውነዋል። በዘመቻው ከአንደኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ከ365 ሺ በላይ ተማሪዎችና ከ20 ሺ በላይ መምህራን መሳተፋቸውንም አስታውቀዋል።

ትምህርት ቤቶች ተዘግተው በዘመቻ መሠራቱ በተንጠባጠበ መልኩ ሰብል ሲሰባሰብ ሊደርስ የሚችለውን የምርት ብክነት ለመሰብሰብ እንደሚያስችል ጠቅሰው፤ በተጨማሪም ተማሪዎች በተናጠል ሰብል ለመሰብሰብ የሚያባክኑትን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመከላከል ያለመ መሆኑን አመላክተዋል።

የዘመቻ ሥራው አርሶ አደሮችን ከማገዝ ባለፈ ትምህርት ቤቶች የመልካም ስነምግባር መፍለቂያዎች፣ የመረዳዳትና የመተጋገዝ ባህል የሚዳብርባቸው ተቋማት መሆናቸውን በተግባር ማሳየት የተቻለበት መሆኑንም አቶ



ጌታሁን ጨምረው ገልጸዋል።

ከታህሳስ 17 ቀን 2015 ጀምሮ መደበኛ የመማር ማስተማር ሥራው እንደሚቀጥል ተረድተው ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው መመለስ እንዳለባቸው ጠቁመው፤ የባከኑ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በተቃራኒ ፈረቃዎችም የማካካስ ሥራ በመሥራት ተማሪዎች ለግማሽ ዓመቱ ፈተና የሚዘጋጁበት ሁኔታ እንደሚፈጠርም አስገንዝበዋል።

መምህራንና ተማሪዎች ያከናወኑት አርአያነት ያለው ተግባር ለዞኑ አርሶ አደሮች ትልቅ አቅም የፈጠረ መሆኑን ያመለከቱት የመምሪያ ኃላፊው፤ በዚህ ሥራ ላይ ለተሳተፉ ተማሪዎች፣ መምህራን ሌሎችንም ባለድርሻ አካላት ምስጋና አቅርበዋል።

በሰብል ስብሰባ ዘመቻው 924 የአንደኛና 72 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና መምህራን መሳተፋቸው የተገለጸ ሲሆን፤ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት ብቻ በተሠራው ሥራ ለመሰብሰብ ከታቀደው አጠቃላይ ምርት 84 በመቶውን መሰብሰብ እንዳስቻለ ተጠቁሟል።

የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚስተዋልበት ወቅት በመሆኑ በቀጣዮቹ ቀናት በአረብ ምድር ላይ ያለው ዝቅተኛ የአየር ግፊት እንደሚጨምርና በዚህም ምክንያት ቀላል ዝናብ ሊያስከትሉ የሚችሉ የዳመና ሽፋኖች በአንዳንድ አካባቢዎች መከሰታቸውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታውቋል።

በዞኑ 614ሺህ 489 ሄክታር መሬት በመኸር እርሻ ሰብል የተሸፈነ ሲሆን እስካሁን ድረስ ከደረሰው ሰብል 84 ከመቶ መሰብሰቡ ታውቋል።

# ስድስት አባላት ያሉት የባለሙያዎች ቡድን ወደ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ሊሄድ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከፊታችን ታህሳስ 17 ቀን 2015ዓ.ም ሰኞ ጀምሮ ስድስት አባላትን ያካተተ የባለሙያዎች ቡድን ወደ አክሱም ዩኒቨርሲቲ በማቅናት ምልከታ ሊያደርግ መሆኑ ተገለጸ።

በትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደር እና መሰረተ ልማት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ሰለሞን አብርሃ እንደገለጹት፤ በግጭቱ ምክንያት ሥራ ያቋረጡ የአክሱም፣ ራያ፣ አዲግራት እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲዎችን ወደ አገልግሎት ለመመለስ እንደሚኒስቴር መስሪያ ቤት ኮሚቴ ተቋቁሞ ዝርዝር ዕቅድ ተዘጋጅቶ እየተሠራ ነው።

ዩኒቨርሲቲዎቹ ዳግም የመማር ማስተማር ሥራ እንዲጀምሩ የሚያስችላቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው የሚለውን የመለየት ሥራ መከናወኑንም አስረድተዋል።

እስካሁን ባለው ሁኔታም ከአክሱም እና ራያ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ዳግም ወደ አገልግሎት በሚመለሱበት ሁኔታ ላይ ንግግር መጀመሩን ገልጸዋል።

በቀጣይም የስልክና ሌሎች አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች ሲሟሉ ከመቀሌ እና አዲግራት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ግንኙነት እንደሚጀምሩ አመላክተዋል።

አሁን በአክሱም የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ተከትሎ ስድስት አባላት ያሉት የባለሙያዎች ቡድን ከሰኞ ጀምሮ የአክሱም ዩኒቨርሲቲ ዋናውን ግቢ ጨምሮ ዐድዋ እና ሽረ ግቢዎችን በሥፍራው ተገኝቶ ምልከታ ያደርጋል ብለዋል።

በተዘጋጀው መመዘኛ (ቸክሊስት) መሰረትም ግቢዎቹ በሰው ኃይል፣ በመሰረተ ልማት፣ በቤተ ሙከራ፣ በመኝታና መማሪያ ክፍሎች፣ በማስተማሪያ ሆስፒታል፣ በቤተ መጻሕፍት እና በሰርቶ ማሳያ ለተማሪ እና መምህራን አገልግሎት የሚሰጡ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው መማር ማስተማር ሥራውን ለማስጀመር የሚያስችለውን ሁኔታ በጥልቀት ይመለከታል።

የባለሙያዎች ቡድን በሚያመጣው መረጃና ምክረ ሐሳብ መሰረት ዩኒቨርሲቲውን ዳግም ወደ ሥራ ለመመለስ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ትምህርት ሚኒስቴር እንደሚያመቻች እና ለመማር ማስተማር ዝግጁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ለተማሪዎች ክፍት እንደሚሆንም ማረጋገጣቸውን ኤፍ ቢ ሲ ዘግቧል።

ዜና

# አዲሱ የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ የአቅርቦት ችግርን እንደሚቀርፍ ይታመናል

**ልጅአለም ፍቅሬ**

<u>አዲስ አበባ</u> ፡- አዲሱ የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ የሲሚንቶ የአቅርቦት ችግር እንደሚቀርፍ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተሻለ በልሁ ከትናንት ወዲያ በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ በሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት ሂደት ላይ የነበረው መመሪያ ቁጥር 908/2014 ዓ.ም የራሱ በጎ ውጤቶች ቢኖሩትም የተለያዩ ክፍተቶች ተስተውለውበታል። ይህን ክፍተት ለማስተካከል የሚያስችል አዲስ መመሪያ በማዘጋጀት ወደ ተግባር ተገብቷል።

መመሪያ ቁጥር 908/4014 ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ የሲሚንቶ ምርት አቅርቦት ቅናሽ ማሳየቱን የተናገሩት አቶ ተሻለ፤ ሆኖም ከመስከረም 5 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በአግባቡ ሲሚንቶ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ቁጥር ከሶስት አይበልጡም ብለዋል።

መመሪያው የመንግስት ፕሮጀክቶች በቀጥታ ሲሚንቶ ከፋብሪካዎች እንዲያገኙ ፤የግል አልሚዎችና ሪልስቴቶች በፋብሪካው መሸጫ ዋጋ እንዲያገኙ ታስቦ የወጣ መመሪያ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የአቅርቦት ችግር፣ የምርት እጥረት፣ ህገ-ወጥ ሽያጭ፣ የችርቻሮ ስምሪት መጥበብ እና የመሳሰሉት ችግሮች እንዲከሰቱ በማድረጉ በአዲስ መመሪያ መቀየር ማስፈለጉን ገልጸዋል።

በቀደመው መመሪያ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎቹ፣ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች የሚመርጡላቸው ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮችና ክልሎች ነበሩ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤



በአዲሱ መመሪያ ግን አከፋፋዮችንና ቸርቻሪዎችን የመምረጥ ነጻነት ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ተሰጥቷቸዋል ብለዋል ።

በአዲሱ መመሪያ የመንግስት ድርሻ የሚሆነው ለተወሰነ ጊዜ ድረስ የፋብሪካዎች ምርታማነት እስኪጨምሩና በገበያ የሚፈለገውን ያህል መጠን ምርት አምርተው ማሰራጨት እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ብቻ መንግስት የሚተምን መሆኑን አመልክተው፤ በስድስት ወር አንዴ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል እንደሚችልም ጠቁመዋል ።

በመሆኑም የሲሚንቶ ምርት አቅርቦትና ፍላጎት በእጅጉ የሰፋ በመሆኑ አቅርቦቱ እስከሚስተካከል ድረስ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ በሚኒስቴሩ ተወስኖ ከትናንት ጀምሮ ተግባራዊ እንደሚሆን ገልጸዋል። በዚህም መሰረት ፋብሪካዎች የትራንስፖርትና ትርፋቸውን ታሳቢ ያደረገ የዋጋ ተመን በማውጣት ለመንግስት ያሳውቃሉ ብለዋል።

የሲሚንቶ አምራቾች ለመረጧቸው አከፋፋዮች፣ ቸርቻሪ ነጋዴዎች ምርት የሚያከፋፍሉ ሲሆን፤ አከፋፋዮቹ ከተቀመጠላቸው የዋጋ ተመን በላይ ሲሸጡ ካገኟቸው ውላቸውን አፍርሰው ለመንግስት ያሳውቃሉ ብለዋል።

መንግስት የሲሚንቶ ምርቱ ግብይት በተቀመጠለት ዋጋና በደረሰኝ መከናወኑን የመቆጣጠርና የመከታተል ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው መንግስት፤ ፋብሪካዎች የሚያወጡት የዋጋ ተፈጻሚነት፣ ስርጭቱ በማጓጓዣ ሰነዶች መሰረት መድረሱንና አለመድረሱን እንዲሁም የግብይት ስርዓቱ በህጋዊ ንግድ ፈቃድና በደረሰኝ መሆኑን ያረጋግጣል ብለዋል።

ለመንግስት ፕሮጀክቶች እና ለትላልቅ የግል አልሚዎች ቅድሚያ እንዲሰጥ የተወሰነ ሲሆን፤ በዚህም እንደ አስፈላጊነቱ ከአከፋፋዮችም ሆነ ከቸርቻሪዎች መግዛት እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

ክልሎችና ዞኖች እጥረት እንዳይገጥማቸው ፋብሪካዎች ዋጋ ተምነው ተደራሽነታቸውን የሚያሳይ አሰራር መዘርጋት እንደሚኖርባቸውም ገልጸዋል።

በኬላዎችና በተለያዩ ስፍራዎች የሲሚንቶ እንቅስቃሴን በመገደብና በማወክ በነፃ ግብይት ሂደቱ ላይ እንቅፋት መፍጠር እንዲሁም ሲሚንቶን ለመቆጣጠር በሚል መውረስ የተከለከለ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ተሻለ ገለጻ በመመሪያው መሰረት የሲሚንቶ ክትትል ቁጥጥር የሚባል ነገር የቀረ ሲሆን፤ ያለደረሰኝ መሸጥና ከፋብሪካ የሚወጣ ማንኛውም ሲሚንቶ የጫኑ መኪናዎች ያለ ጉዞ ሰነድ መንቀሳቀስ አይችሉም፤በጉዞ ሰነዱ ላይም መድረሻ ቦታና የጫነው ብዛት መጠን መጠቀስ ይኖርበታል። ይህም የተደረገው በግንባታ ሰበብ ህገ ወጥ ንግድ ላይ የተሰማሩትን ለመቆጣጠር ነው።

## የቦይንግ 737...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

8 አውሮፕላን አደጋ ኤምካስ በተባለ የሲስተም መቆጣጠሪያ ከቁጥጥር ውጭ መሆን የደረሰ መሆኑ ተረጋግጧል ብለዋል። የአውሮፕላን አደጋው የምርመራ ሪፖርት አደጋው በተከሰተ ከአንድ ወር በኋላ ይፋ መደረጉን ያስታወሱት ሚኒስትሯ፤ የኮሮና ቫይረስ መከሰት ለሪፖርቱ መዘግየት ዋነኛው ምክንያት እንደሆነም ገልጸዋል።

በተደረገው ምርመራም የበረራ ባለሙያዎች በረራ ማድረግ የሚያስችላቸው ብቃትና ፈቃድ እንዳላቸው መረጋገጡን ፣ አውሮፕላኑ የበረራ ፈቃድ፣ አብራሪና የበረራ መስመሩ የታወቀ እና የተፈቀደ እንደነበር፣ አውሮፕላኑ መብረር የሚያስችል የምስክር ወረቀት ያለው መሆኑና አውሮፕላኑ ለበረራ ሲነሳ ትክክለኛ ክብደት መሸከም በሚያስችለው ሁኔታ ላይ እንደነበር መረጋገጡን ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ ለአውሮፕላኑ መከስከስ ዋነኛ ምክንያትም MCAS የተሰኘው ሶፍትዌር በትክክል አለመስራቱ እንደነበር መረጋገጡን ገልጸው፤ በምርመራው ሪፖርቱ መሰረትም የማክስ 737-8 ማክስ አውሮፕላን ኤምካስ የተሰኘው የአውሮፕላኑ ፍጥነትና አቅጣጫ መቆጣጠሪያ በተደጋጋሚ ወደ ታች ማጎንበሱ የአደጋው ምክንያት እንደነበር አስታውቀዋል።

ከፈረንሳይ፣ ከአሜሪካ እና ከተለያዩ ድርጅቶች የተውጣጣው የምርመራ ቡድን ላደረገው የምርመራ ድጋፍ አመስግነው፣ በአደጋው ቤተሰባቸውን ለተነጠቁ ወገኖች፣ በአቬሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ድርጅቶች ሀዘናቸውን በመግለጽ መጽናናትን ተመኝተዋል።

የአውሮፕላን አደጋ የምርመራ ቢሮ ኃላፊ ኮሎኔል አምድዬ አያሌው፣ የምርመራ ቢሮው በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና በአለም አቀፍ የአቬሽን ስምምነት መሰረት የአደጋውንና ሁነቱን ሲመረመር ቆይቷል ብለዋል። በዚህም የምርመራ ኮሚቴ በማቋቋም የምርመራ ስራ ሲያከናውን እንደቆየና በምርመራው፣ የኦፕሬሽን፣ የአቬሽን ሰራተኞችና ሌሎች ባለድርሻዎች መሳተፋቸውን ገልጸዋል።

መጋቢት አንድ 2011 ዓ.ም 157 ሰዎችን አሳፍሮ ከአዲስ አበባ ወደ ናይሮቢ በመብረር ላይ እያለ ከስድስት ደቂቃ በኋላ ቢሾፍቱ አቅራቢያ ተከስክሶ በወቅቱ የበረራ ሠራተኞችን ጨምሮ የሁሉም መንገደኞች ሕይወት ማለፉ ይታወሳል። በወቅቱም ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የ35 ሃገራት ዜጎች 149 መንገደኞችና ስምንት የበረራ ስራተኞች በአደጋው ህይወታቸውን አጥተዋል።

## ኅብረቱ ስሰላም...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሚያደርጉትን ጥረት እንዲቀጥሉም አበረታተዋል።

የፌዴራል መንግስት እና የሕወሓት ከፍተኛ አዛዦች በሰላም ስምምነቱ አተገባበር ዙሪያ ባካሄዱት ሁለተኛው ዙር ስብሰባ የሰላም ስምምነቱ አፈፃፀም ላይ ውይይት ያደረጉ ሲሆን በውይይቱ የተለያዩ ጉዳዮች መዳሰሳቸው ተመላክቷል።

ኮሚሽኑ በሰላም ስምምነቱ አተገባበር ላይ ስለሚያደርገው ክትትል፤ ጥምር ምልከታ እና የተገዢነት አካሄድን አስመልክቶ ውይይት የተደረገ ሲሆን፤ በተጨማሪም ስብሰባው በትጥቅ አፈታት አተገባበር ላይ፤ ታጣቂዎችን ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ማንቀሳቀስን በተመለከተ እና በመልሶ ማቋቋም ላይ ውይይት ተካሂዷል።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የቀድሞው የኬንያ ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ በበኩላቸው፤ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ መሻሻሎች እየታዩ መሆናቸውን ጠቁመው "እኛ የሰላም ስምምነቱን ባካሄዱት ሁለቱም አካላት ደስተኛ እንደሆንን መግለጽ እፈልጋለሁ።" ብለዋል ።

ተግባራዊ እየተደረጉ የሚገኙት የሰላም ስምምነቶች ትግራይን ወደተስተካከለ ሁኔታ በማምጣት ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ወደተረጋጋ ሀገርነት መመለስን ዓላማ ያደረጉ ናቸው ሲሉም ተናግረዋል።

ሁለቱ የስምምነቱ ፈራሚዎች ባለፉት ሁለት ቀናት ውይይት ሲያደርጉ ቆይተዋል ያሉት ኬንያታ፤ ሆኖም ወደ ተጨባጭ አፈፃፀም መቀየር የሚቻለው በስምምነቱ ልክ የተሠሩ ሥራዎችን ወርዶ ማረጋገጥ ሲቻል መሆኑን ጠቁመዋል።

"በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት በመቀሌ በመገኘት በስምምነቱ መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን የማየትና የማረጋገጥ ሥራዎች እንሠራለን።" ያሉት ኡሁሩ ኬንያታ፤ የስምምነት ዶክመንቶች እንዳሉ ሆነው ትግበራዎችን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፤ ይህ የሚደረገው አሁን ዶክመንቱንም ሆነ ተግባራቱን መፈፀማቸውን ማረጋገጥ ስለሚያስፈልግ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ቀደም ሲል በናይሮቢ ውይይት ያደረጉት ሁለቱ የስምምነቱ ፈራሚ አካላት ያለው ግንኙነት የሚደነቅ እንደነበርም ተናግረዋል። ይህም ስምምነቱ በትክክለኛ አቅጣጫ እየተመራ ስለመሆኑ ከፍተኛ የሆነ በራስ መተማን መፍጠሩን ገልፀዋል።

የሰላም ስምምነቱ አተገባበር ውጤታማነት በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት የሚረጋገጥ እንደሆነ የጠቆሙት የቀድሞ ፕሬዚዳንቱ፤ ኢትዮጵያውያን መጪውን የፈረንጆች አዲስ አመት እና የገና በዓላቸውን በሰላም፣ በሚናፍቁት ተስፋ እና በደስታ ያከብራሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን ሲሉ አብራርተዋል።

## «የተፈጠረው የሰላም...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የሚያስከብር ጠንካራ አስተዳደር ሊመሰረት እንደሚገባ ቀደም ሲል በነበረው የትግራይ ጊዜአዊ አስተዳደር የዋጅራት ወረዳ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ መኮንን አብርሃ ተናገሩ።

አቶ መኮንን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደተናገሩት፤ ቀደም ሲል በትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ወቅት የተፈጠረው ችግር እንዳይደገምና ህዝቡ ተረጋግቶ ወደ ቀድሞ ኑሮው እንዲመለስ አካታች፣ ጠንካራ እና ስርአት የሚያስከብር አስተዳደር መገንባት ያስፈልጋል።

አሁን የተፈጠረው የሰላም አየር ለትግራይ ህዝብና ለአጎራባች ክልሎች እጅግ እረፍት የሚሰጥ እና በተለይ በሰላም እጦት ምክንያት የተቋረጠው የትምህርትና ማህበራዊ አገልግሎት ወደ ነበረበት እንዲመለስ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው ብለዋል።

አቶ መኮንን እንደተናገሩት፤የተፈጠረው የሰላም ሁኔታ ዘለቄታ እንዲኖረውና እንዲፀና በተለይ የሚዲያ ተቋማት ትልቅ ድርሻ አላቸው።

የትምህርት ስርዓቱና ሌሎች ተቋማትም አዲሱ ትውልድ በጎ ሃሳብ እንዲያመነጭ እና እርስ በርስ ከመጠላላት አጀንዳ ወጥቶ በመልካም ስነ ምግባርና በግብረ ገብ እንዲታነፅ ድርሻቸውን እንዲወጡ አቶ መኮንን ጠይቀዋል።

ያለፉት ሁለት ዓመታት ለህገራችን በተለይ ለሰሜኑ ክፍል እጅግ ከባድ ጊዜ እና ኪሳራ ያስከተለ እንደነበር በማስታወስ ከምንም በላይ በህዝባችን ላይ የደረሰው የስነ ልቦና ቀውስ እንዳይደገም ሁላችንም የበኩላችንን ጥረት ልናደርግ ይገባል ብለዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች ፣የሃይማኖት አባቶችና የሚዲያ አንቂ ግለሰቦች በህብረተሰቡ ስነልቦናዊ ውቅር ላይ ትኩረት አድርገው ቢሰሩና ከምንም በላይ በስነ ምግባር የታነፀ፣ ምክንያታዊ ትውልድ እንዲፈጠርና የተበላሸው እንዲስተካከል ቅድሚያ ሰጥተው ቢሰሩ ወደ ተሻለ ሁኔታ እንደሚደረስ ተናግረዋል።

መንግስት ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሁኔታዎችን የማስተካከል ድርሻ ከተወጣ ጠንካራ ማህበረሰብ ለመፍጠር አያዳግትም ያሉት አቶ መኮንን፤ በጦርነቱ የወደሙ መሰረተ ልማቶችና የተጎሳቆለው ማህበረሰብ መልሶ እንዲያገግምና ወደ እድገት እንዲያመራ የሰብአዊ እርዳታ ላይ እየተደረገ ያለው ርብርብ ጠቃሚ መሆኑን አቶ መኮንን ተናግረዋል።

ይህንን የሰላም ዕድል በተለይ የትግራይ ህዝብ በጉጉት ሲጠብቀው የቆየ በመሆኑ ይህንን ሊያስፈፅምለት የሚችል ጠንካራ አመራርና እና የህግ ተጠያቂነት ያለው ሁሉን አካታች አስተዳደር ዘርግቶ በትኩረት መስራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

የትግራይ ህዝብም የተፈጠረለትን የሰላም ዕድል በመጠቀም አጋጥሞት ከነበረው ችግርና መከራ ጨርሶ ለመውጣት ከመንግስትና ሲቪክ ማህበራት ጋር በመሆን መወያየትና ጠንክሮ መስራት ይጠበቅበታል ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል



## «መተማመን ሲኖር የተረጋጋና አስተማማኝ ሰላም ማግኘት ይቻላል»

- አቶ ዲባባ ተስፋዬ
የሰላም እና ግጭት አወጋገድ ባለሙያ

ገጽ 6

## ትራንስፖርት ላይ የሚፈፀመው የሴቶች ፆታዊ ትንኮሳ

ገጽ 11



## «ልጆቼ አንድ ቤት ተሰብስበው፣ መኝታ አግኝተው የሚያርፉበትን ቀን እናፍቃለሁ»

- ወይዘሮ ብርሃኔ ድጉማ

ገጽ 16

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

### ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው በመልካም አስተዳደር ችግር የተዘፈቁ ዘርፎች

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በከተማዋ ያለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍ ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ገደማ የተለያዩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ፕሮግራሞችን በመንደፍ ቤቶቹን ለቤት ዕድለኞች ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም ኮርፖሬሽኑ ለመምህራን የተሰጠውን አምስት ሺ ቤቶችን ጨምሮ በ20/80 ፣ በ10/90 እና በ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች መርሐ- ግብር እስካሁን በጥቅሉ ከ256 ሺ 251 ቤቶች በላይ ሠርቶ በማጠናቀቅ ለባለ ዕድለኞቹ በማስረከብ ከአንድ ሚሊዮን 281 ሺ በላይ እማወራዎችን እና አባወራዎችን የቤት ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓል።

ከዚህ ባሻገር ኮርፖሬሽኑ በ20/80 የቤቶች ልማት ፕሮግራም 100 ሺ 769 ቤቶች (የፓኬጅ 2A – 26 ሺ 613፣ የፓኬጅ 2B – 26 ሺ 203 እና የፓኬጅ 3 – 47 ሺ 952)፣ በ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም 38 ሺ 240 ቤቶች (የፓኬጅ 2 – 17 ሺ 737 እና የፓኬጅ 3 – 20 ሺ 503) በድምሩ 139 ሺ 8 ቤቶችን በነባር ግንባታ እያከናወነ ይገኛል። እንዲሁም በ2012 በጀት ዓመት የተጀመሩ አራት ሺ 287 ቤቶች (በ20/80 የቤቶች ልማት ፕሮግራም – 826፣ በ40/60 የቤቶች ልማት ፕሮግራም ሦስት ሺ 21 እና በኪራይ 440 ቤቶች) በጠቅላላው 143 ሺ 295 ቤቶች ግንባታን በነባርና በአዲስ የቤት ልማት ፕሮግራም በማካሄድ ላይ ይገኛል።

ኮርፖሬሽኑም እነዚህን በግንባታ ላይ የሚገኙ ቤቶችን አጠናቆ ለቤት ዕድለኞች ለማስረከብ እየተጓዘበት ያለው መንገድ ምን እንደሚመስል በየወሩ የተሠሩ ሥራዎችን ይገመግማል። በተመሳሳይ ኮርፖሬሽኑም ከሰሞኑ የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች፣ ዳይሬክተሮች እና ቡድን መሪዎች በተገኙበት የህዳር ወር የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርትና የወሩ የመልካም አስተዳደር ሪፖርት ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል። በውይይት መድረኩ የኮርፖሬሽኑ ዋና ዳሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት እንደገለፁት፤ ከሪፖርቱ እንደተረዳነው የአንዳንድ ዳይሬክቶሬቶች የወሩ አፈፃፀማቸው ሲታይ ክፍተት ያለበት ነው። ከመንግሥት ሥራው በተጨማሪ መልካም አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር አሁንም እንግልት እና ምልልስ የሚታይባቸው የብልሹ አሰራር ትግሉ የቀዘቀዘባቸው ዘርፎች አሉ። እነዘህ ክፍሎች በአስቸኳይ ካላስተካከሉ በቀጣይ የስድስት ወር አፈፃፀም ግምገማ ላይ በስም ጭምር በመግለፅና የተጠያቂነት እርምጃ ጭምር እንደሚወሰድ አስጠንቅቀዋል።



አቶ ሽመልስ ታምራት፤



የውይይቱ ተሳታፊዎች፤

ፈፃሚው አካባቢ የሚታዩ የሰአት መሸራረፍ፣ ፈርመው የሚወጡና ሳያስፈቅዱ ከሥራ ገበታቸው ላይ የማይገኙት ላይ ከዚህ በኋላ እያንዳንዱ ዳይሬክተር አስተማሪ የሚሆኑ እርምጃዎችን በመውሰድ በሪፖርት እንዲያሳውቁም ጭምር ነው አቶ ሽመልስ ታምራት ያሳሰቡት።

የኮርፖሬሽኑ የእቅድና በጀት ዳይሬክተር አቶ አለማየሁ ደንቦባ፤ የህዳር ወር አፈፃፀም ሪፖርትን ባቀረቡበት ወቅት የእያንዳንዱ ዘርፍ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በሚያሳይ መልኩ ሪፖርቱን አቅርበዋል። እንደ ችግርም ከጠቃቀሷቸው መካከል ሪፖርትን በተቀመጠው ጊዜ ፈጥኖ ያለመላክ ፣ ካለፈው ወር ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሪፖርት ሰርቶ የመላክና ሪፖርትን ገላጭ በሆነ መልኩ እቅድና አፈፃፀመን በማነፃፀር ሊመዘን በሚያስችል መልኩ ያለማቅረብ የሚጠቀሱ ችግሮች መኖራቸውን ተናግረዋል።

በሌላ በኩል ከስነምግባርና ከብልሹ አሠራር አንፃርም የመልካም አስተዳደር የህዳር ወር ሪፖርትን ያቀረቡት የስነምግባርና ክትትል ዳይሬክተር አቶ ሙላቱ ሰይፉ በበኩላቸው፤ አንዳንድ ዳይሬክቶሬቶች ላይ የተገልጋይ ምልልስና እንግልት አሁንም እየታየ እንደሆነና ዘርፎቹ ከተገልጋይ የሚደርሰውን ጥቆማ መሰረት በማድረግ ማብራሪያ እንዲሰጡ ሲጠየቁ ምላሽ የማይሰጡ ምንም የማይበርዳቸው ፣ የማይሞቃቸው ፈፃሚዎችና አመራሮች እንዳሉም ጠቁመዋል።

የስነምግባር ዳይሬክተሩ አቶ ሙላቱ ሰይፉ አክለውም፤ ከንብረት አያያዝና የመንግሥትን ሃብት በአግባቡ ከመጠቀም አንፃርም ሁሉም ፈፃሚ ራሱን ሊፈትሽ እንደሚገባ ጠቁመው፤ በቀጣይ ሊደረጉ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች በሪፖርታቸው ጠቅሰዋል።

በሪፖርት ግምገማው ተሳታፊ የነበሩ ዳይሬክተሮች እና የቡድን መሪዎች ሰፊ ውይይት ካደረጉ በኋላ የኮርፖሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት በሰጡት የሥራ አቅጣጫ እያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት በየዘርፋቸው የአምስት ወራት አፈፃፀማቸውን ገምግመው የአንድ ወር እቅድ በአክሽን ፕላን የተደገፈ እንዲያዘጋጅ መመሪያ ሰጥተው ውይይቱ ተጠናቋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ መተማመን ሲኖር የተረጋጋና አስተማማኝ ሰላም ማግኘት ይቻላል ››

**- አቶ ዲባባ ተስፋዬ**
**የሰላም እና ግጭት አወጋገድ ባለሙያ**

ምሕረት ሞገስ

አቶ ዲባባ ተስፋዬ ይባላሉ፡፡ በእንግሊዝ አገር ለ30 ዓመታት ኖረዋል፡፡ በወቅቱ በአገሪቱ በነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ተሰደው እንግሊዝ አገር ሲገቡ ‹‹ለምን በአገሬ ፖለቲካ ምክንያት ተበደልኩ?›› በማለት ፖለቲካ ለማጥናት ወሰኑ፡፡ ሙሉ ጊዜያቸውን ለትምህርት በመስጠት በታሪክ፣በፍልስፍና፣በሳይኮሎጂ፣በኢኮኖሚክስ እንዲሁም በኮምፒውተር ሳይንስ በመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን በአንድ ጊዜ ቀጠሉ፡፡ ሆኖም ጊዜው ስላልበቃቸው የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርትን አቁመው ሌላውን ማጠናቀቅ መቻላቸውን ይናገራሉ፡፡

በመቀጠልም የዓለም አቀፍ ሁኔታን ለመረዳት ከፍ ያለ ፍላጎት ስላደረባቸው ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣የሰብዓዊ መብት ሕግ፣ ዓለም አቀፍ ሕግ ፣ ልማታዊ ጥናት ፣ ሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን፣ የአፍሪካ ጂኦ ፖለቲካ ስትራቴጂክ፣ የሰው ሃብት ልማት፣ የሰላም እና ግጭት አወጋገድ ጨምሮ ሌሎችም የተለያዩ ዘርፎችን በመማር ምርምር ሲያደርጉ ቆዩ፡፡

ካካሔዷቸው ጥናቶች መካከል በብዛት ያከናወኗቸው በአፍሪካ የድንበር ግጭት ሳይ ነው። በተለይም በኢትዮጵያ እና በሱዳን፤ በኢትዮጵያ እና በሶማሊያ፣ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል ከድንበር ጋር ተያይዞ ባሉ ሁኔታዎች ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡ በኢትዮጵያ ዙሪያ ብቻ ሳይሆን፣በአፍሪካም የተለያዩ አገሮች ናሚቢያ፣ ሞዛምቢክ፣ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ አንጎላ፣ ኮንጎ፣ሳይቤሪያ እና ሴራሊዮ ብጥብጥ ባሉባቸው አገሮች በመገኘት ምክንያቱ ምንድን ነው? በማለት ሲያጠኑ ቆይተዋል፡፡

በሰላም እና ግጭት አወጋገድ ላይ የአፍሪካን ልጆች ለማሰልጠን የልህቀት ማዕከል ለማቋቋም ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በዚሁ እና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ በተለይም ትልቅ ውጤት ሊገኝባቸው በሚችሉ የጥናት መንገዶችን በሚመለከት እ.አ.አ በ2019 በስምንት ዩኒቨርሲቲዎች አስተምረዋል፡፡ በሰላም ጉዳይ ላይም ለሚመለከታቸው ተቋማት የማሰልጠን ሃሳብ አሳቸው። ለዛሬ የ‹‹ዘመን እንግዳ›› አድርገን ከመረጥናቸው ከአቶ ዲባባ ተስፋዬ ጋር በሀገራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ፣ በግጭት አፈታትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡



**አዲስ ዘመን፡- የሰላም መሠረቱ ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ ዲባባ፡-** ሰላም በማንኛውም ቦታ መሠረቱ መተማመን ነው:: በባልና ሚስትም ሆነ በተለያየ ጎሳ በማንኛውም ደረጃ በአገርም ሆነ በየትኛውም ደረጃ መሠረቱ መተማመን ነው:: አበጥሮ እና አንጠርጥሮ በመነጋገር መተማመን ላይ ካልተደረሰ በፍፁም ከሰማይ ሰይጣንም ሆነ ፈጣሪ ቢወርድ ግጭትን ማብረድ አይቻልም:: ሁልጊዜ የሰላም ፊርማ ተከናውኖ ውጤታማ የማይሆነው መተማመን ስለሌለ ነው:: መተማመን ሲኖር የተረጋጋና አስተማማኝ ሰላም ማግኘት ይቻላል::

**አዲስ ዘመን፡- በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት አጠቃላይ ለሃገራዊ ሰላም እና የወደፊት እድገት የሚኖረውን አንድምታ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ ዲባባ፡-** መጀመሪያ የሰላምን ፅንሰ ሃሳብ መረዳት አለብን:: ሰላም ሂደት ነው:: ይሔ ሂደት እንዴት ይመጣል የሚለውን ቀድሞ መረዳት ያስፈልጋል:: ቀድሞ የሰላምን ስረ መሠረቱን መረዳት ትልቁና የመጀመሪያው ደረጃ ነው:: ሌላው ይሄን ነገር መፍታት የምንችለው እንዴት ነው? የሚለው ላይ ምልከታ ያስፈልጋል:: ተቀራርቦ ዓይን ለዓይን ተያይቶ ሳይተፋፈሩ መተማመንን መገንባት የግድ ነው:: ለመተማመን ደግሞ የምላስ ድለላ ሳይሆን ከልብ በእውነት ላይ የተመሠረተ የሚታመን በግልፅ የሚታይ እውነተኛ ግንኙነት እና ንግግር መኖር አለበት:: እነዚህ ሳይኖሩ በፍፁም መተማመን መፍጠር አይቻልም::

በየትኛውም በኩል ያሉ ተስማሚዎች ወይም ተደራዳሪዎች በራስ መተማመን ያላቸው እና ብቁ መሆን አለባቸው:: በሚያደርጉት ነገር ግልፅ አቅጣጫ እና ግብ ሊኖራቸው ይገባል:: ግልፅነት ባለው መልኩ የጋራ ግብ ማስቀመጥ ያስፈልጋል:: ስምምነቱ ግልጽነት ከሌለው እና ድብቅ ፍላጎት ካለ አይሳካም:: በመጨረሻም ሕይወት ለመቀጠል በመተማመን በሰላም እና በእርቅ ላይ መመሥረት ይሻላል ወይስ ሸፍጥ መሥራት ይሻላል? የሚለው ፍርጥርጥ ብሎ መቀመጥ አለበት:: ማንም እያባበለ እና እያታለለ የሚፈፀም ሳይሆን በግልፅ ከሰላም የምናተርፈው ነገር እነዚህ ... እነዚህ... ናቸው:: በእኩልነት ላይ በጤናማ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ብንፈጥር ይሻለናል ወይስ ትርፍ የሚመጣው ሁልጊዜ እያጋደልን እና አንዱ ሌላውን እያቋሰለ ነው? የትኛው ይበልጣል? ጥቅም እና ጉዳቱን ቁጭ ብሎ ማፍረጥረጥ ሲቻል የጋራ ግብን ማምጣት ይቻላል::

በመጨረሻ ስምምነት ከኖረ እንዴት አድርገን ይህንን ወደ ሥራ እንለውጣለን? መሬት የምናወርደው እንዴት ነው? የሚለው በደንብ መታወቅ አለበት:: መጀመሪያ በሰላም ጉዳይ፣በአገር ጉዳይ፣በየትኛውም የስምምነት ጉዳይ ላይ መተማመን ካልተፈጠረ ማንኛውም ነገር ዋጋ የለውም::

ሰላም የሚፈጠረው እና ስምምነት ላይ ተደርሶ ውጤት የሚመጣው በሶስት መንገድ መሆኑ በሙያተኞች ተቀምጧል:: አንደኛው ዝግጁነት ነው :: ይሔ ጦርነቱን የሚያባብሱ ሰዎች ሲከዱ ወይም ዞር ሲሉ፤ ከኋላ ሆነው የራሳቸው ግብ ያላቸው ምናልባትም የውጪ ጠላቶች ሊባሉ የሚችሉ እየተንከባከቡ እና እየኮተኮቱ ሰላም እንዳይኖር የሚገፉፉ ሰዎች ሲሄዱ ወደ ስምምነት ይመጣል::

ሌላው የአንደኛው ወገን ኃይል ሲያመዝን ሌላኛው ወገን እጅ ይሰጣል:: እጅ የሚሰጠው አካል ከዚህ በላይ መጋፈጥ አንችልም ሲል ለስምምነት የዝግጁነት ደረጃ ላይ ተደርሷል ማለት ይቻላል:: ወይም ጦርነቱን የሚያቀጣጥሉ ሰዎች እድሜያቸው ሲገፋ ‹‹እንዴ ! ሳንበላ ልንሞት ነው? ›› ብለው መዋጋቱን ይተውታል:: እዚህ ላይ እንደምሳሌ የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ንቅናቄን ሲመራ የነበረው ጆን ጋራንግን መጥቀስ ይቻላል::

በባለሙያዎች (መዝጋት ወይም ማቋረጥ) የሚባለው ሌላኛው ወደ ሰላም የሚመጣበት መንገድ በሁለቱም በኩል መፈናፈኛ ሲጠፋ ነው:: በሁለቱም በኩል ምንም መንቀሳቀስ ሳይቻል ሲቀር እግር ሲታሰር እና አንገት ሲታነቅ ስምምነት ላይ መድረስ የግድ ይሆናል:: እዚህ ላይ ሦስተኛ ወገንም የሚካተት ሲሆን ሦስተኛ ወገን ‹‹ዱላ እሰነዝራለሁ›› ሲል፤ ሲያፈራርም ወደ ስምምነት ይመጣል:: ሶስተኛ ወገንም ‹‹ጥቅማ ጥቅም እሰጣለሁ›› ሲል የስምምነት በር ይከፈታል:: ይህንን የሚለው ለአንዱ ወይም ለሁለቱም ሊሆን ይችላል:: ልብ መባል ያለበት ሦስተኛው ወገን በስምምነቱ ላይ የራሱ ዓላማ ይኖረዋል:: የመጨፍለቅ እና በዛ ውስጥ ትልቅ ጥቅም የማግኘት እና የማኮላሸት ዓላማ ሊኖረው ይችላል:: ስለዚህ የሦስተኛ ወገን ዓላማ ሊኖር ይችላል:: ይሔን በደንብ ለማብራራት በጣም ጊዜን የሚጠይቅ በመሆኑ በቀላሉ በትንሽ ጊዜ ለመግለፅ ያስቸግራል:: ነገር ግን እዚህ ላይ አንዳንዴ ስምምነት አድራጊዎች የሦስተኛውን ወገን ሴራ የማይረዱበት አጋጣሚም ይኖራል:: ምክንያቱም ሦስተኛ ወገኖች በአብዛኛው የሚሠሩት በተንኮላዊ ጥበብ ነው:: ቦንብ ሲፈነዳ የሚፈነዳው እና የሚበታተነው እጅ የሚቆርጠውን እና አይን የሚያጠፋውን ብረት ማሳየት አይፈቀድም:: ከመፈንዳቱ በፊት የሚታየው ተሸፋፍኖ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ስምምነትን አስመልክቶ ጥሩ ማብራሪያ ሰጥተውኛል:: ነገር ግን በቀጥታ በፌዴራል መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት በተመለከተ ሃሳብዎትን ይግለፁልኝ::**

**አቶ ዲባባ፡-** እንዳልኩት ይሔ ስምምነት በተናገርኩት ቅደም ተከተል መሠረት በወሳኞቹ ነገሮች መተማመን ላይ ከተመሠረተ እና መተማመኑ ደግሞ በግልፅ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ከሆነ ጥሩ ነው:: ነገር ግን ሸፍጥ እየሸረቡ ከሆነ በፍፁም የፀና ሰላም ሊኖር አይቻልም:: ለቤት ዋናው መሠረቱ ነው:: መሠረቱ ጠንካራ ካልሆነ ቤቱ ይፈርሳል ወይም ይወድቃል:: መተማመን ላይ ለመድረስ በቅድሚያ ራስን ስለማኖር ይታሰባል:: እርሱ የሚጠፋ እና ሌሎች የሚኖሩ ከሆነ በራሱ ላይ መተማመን አይችልም:: ስለዚህ ተስማሚው አካል የሚመቸው ካልሆነ የማያስተማምን ነው:: ስለዚህ አንዱ ተስማሚው አካል ታማኝ አይሆንም::

ድምዳሜው ተስማሚው አካል በሁለት እግሩ ቆሞ ዓላማ ይዞ ቢሆን በራሱ ይተማመናል፤በራሱ መወሰን ይችላል:: ነገር ግን ሦስተኛ አካል ተስፋ እየሰጠው እና እያማለለው ከሆነ የማይቀረው ነገር መምጣቱ አይቀርም:: በአብዛኛው በኩል ያለው ተደራዳሪ በራሱ ፅኑ እምነት ላይ ተመሥርቶ ድርድር አድርጓል የሚል እምነት የለኝም:: ምናልባትም ሶስተኛ ወገን ወደ መንግሥት አድልቷል ብሎ በማሰብ ወደ ስምምነቱ መጥተው ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ምንም ቢሆን ምድሪቷን እና የራሱን ሕዝብ ሲያል እናድርግ ብሎ የሚነሳ ከሆነ አተገባበሩም ችግር ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ምናልባትም ብዙዎች እንደሚገልፁት የፌዴራል መንግሥት አሸናፊነት በማየሉ ወደ ስምምነት ተመጥቷል ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ዲባባ፡-** አዎ! አንዱ ኃያል ሲሆን፤ ሌላው አንወጣውም ብሎ ሲያስብ ለስምምነት ዝግጁ መሆን ይኖራል::

**አዲስ ዘመን፡- በየትኛውም መንገድ ቢሆን የሰላም ስምምነት ላይ ተደርሷል:: ይሄ የሰላም ስምምነት ለሃገራዊ ሰላም እና የወደፊት እድገት የሚኖረው አንድምታ ምንድን ነው?**

**አቶ ዲባባ፡-** ጦርነት ለማድረግ ተስፋ መቁረጥ ተፈጥሮ ከሆነ እና ሁላችንም ከምናልቅ ብለው ሰላምን እንደመጨረሻ አማራጭ ወስደው ከሆነ የሚሳካበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል:: ምናልባትም መንግሥት የሚሔድበት ትልቅ ጥበባዊ መንገድ ሰላም ያመጣ ይሆናል::

**አዲስ ዘመን፡- በትክክል ወደ ፊት ሰላም ይፈጠራል ብለን ተስፋ እናድርጋለን:: ሰላም ሲኖር በተለይ አሁን በተለያየ ሁኔታ ለተጎዳው ኢኮኖሚ የሰላም መምጣት የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድን ነው?**

**አቶ ዲባባ፡-** ስለኢኮኖሚ ከተነሳ የመጀመሪያው

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

እና ዋነኛው ጉዳይ ኢኮኖሚን የሚያሳድገው ነፃነት ነው። ብዙ ሰው ኢኮኖሚውን የሚያሳድገው እርዳታ ወይም ኢንዱስትሪ ነው ይላል። ነገር ግን ኢኮኖሚውን የሚያሳድገው በዋናነት ነፃነት ነው። አንድ ሰው ሠርቶ የማይዘረፍበት ሥርዓት መኖር አለበት። ድሮ ቆይቷል አያቴ ሱዳን እና ሶማሊያ ድረስ ለፍቶ ነግዶ ኬኒያም ሔዶ ሠርቶ ዘረፉት። ሃብት የሚያመጣ በጣም ብዙ ሰው ቀጥሮ የሚያሠራበትን ሥርዓት ከአንገቱ ቆረጡት። አያቴ ብቻ ሳይሆን ቀጥሮ የሚያሠራቸውም ብዙ ነገር አጡ። ነፃነት ሲኖር ሰው የሚበረታታበት ሁኔታ ይፈጠራል። ሰው ጥበቃ እና ደህንነት ይኖረዋል። ያገኘውን ቆፍሮ መደበቅ ወይም ትራስ ውስጥ ማስቀመጡን ትቶ ወደ ሥራ ይገባል። ጦርነት የአገር ኢኮኖሚን እንደሚጎዳ አጠያያቂ አይደለም። ጦርነት ሲኖር ለሌብነትም ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። በመጥፎ አጋጣሚው ብዙኃን ሲያጡ አንዳንዱ በዘረፋ ይከብራል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ዘላቂ ሰላም እየመጣ ነው ብለን ተስፋ እናድርግ?**

**አቶ ዲባባ፡-** ሰላም በተስፋ ብቻ አይመጣም። ጥበብን ይጠይቃል። ሰላም እና ኢኮኖሚ ከተባለ በኢትዮጵያ አካውንት ውስጥ እስከ አሁን ያወጣነው እና ያገኘነው (debit and credit) ቢሰላ በጥሬ ገንዘብ አይደለም ፤ በሌላ በኩል ክምችቱ ሀገርን የሚያጠነክር ነው ወይስ ሀገርን እና ትውልድን የሚበላ ነው? የሚለው መጠየቅ አለበት። ኢትዮጵያ ለዘመናት ምን ስታከማች ኖረች? ፍዳና መከራ ወይስ ነፃነት፣ብልጽግና እና ዕድገት አሁን ያለው ነገር ምንድን ነው? የሚለው መፈተሽ አለበት።

ሰላም የሚኖረው በጥበብ እና በድርጊት ነው። ሰላም በጠመንጃ እና በድሮን ሳይሆን በጥበብ የሚመጣ ነው። ጥበብ ከሌለ ሰላም ሰፍኖ ኢኮኖሚን ማሳደግ አይቻልም። ፍዳው ማቆሚያ አይኖረውም። ለመኖር ማድረግ ነው፤ለማድረግ ደግሞ መወሰን ያስፈልጋል። የሚወሰነው ብቃት እና ጥበብ ላይ ተመሥርቶ ነው። እያንዳንዱ መረጃ በትክክል ቀርቦ፣ ተተንትኖ ፣ተበጥሮ ሲከናወን ውጤቱ ጥሩ መሆኑ አይቀርም። ነገር ግን በሌላ ሰው ጭንቅላት ላይ ተመሥርተን የምናደርገው ከሆነ በተከታታይነት ፍዳው ይቀጥላል።

የሚወስነው ማን ነው? የመወሰንስ ብቃት አለ? ለመኖር ወስኖ ማድረግ የግድ ነው። ነገር ግን ለማድረግ ስንወስን ውሳኔያችን ምን ላይ ተመሠረተ የሚል ጥያቄ ይነሳል። ሰው በቀን ሙቶ ሲጋራ እያጨሰ ጨጓራዬን ታመምኩ ቢል ዋጋ የለውም። ውሳኔና ድርጊት መገናኘት አለበት። ላለመታመም እየወሰነ ሲጋራ ማጨስ ካላቆመ ችግር ነው። በአብዛኛው አፍሪካ ላይ ያለው ተመሳሳይ ነው።

ኢኮኖሚ ሲባል ተለይቶ ግብርናው ላይ ጥልቅ ትንተና አድርጎ በደንብ ፈትሾ፣ ወቅጦ በወንፊት አሳልፎ ለዳቦና ለኬክ የሚሆን ዱቄት ለማግኘት ጭንቅላት ያስፈልጋል። የድሃ ቤት እየተቃጠለ፤ ሕፃን ልጅ አንገቱ እየተቀላ ማድበስበስ አይቻልም። ሁሉንም ፍርጥርጥ አድርጎ በግልጽ መነጋገር ያስፈልጋል። አስፈፃሚውም የአገሪቷን ክምችት በግልፅ እስከ አሁን ያለው ይሔ ነው ብለው ማሳወቅ አለባቸው። አገር በምኞት አትለወጥም።

በሰሜን ያለው ጦርነት ቢቆምም በሌላ ቦታም ሰላም ያሳጣ እንቅልፍ የነሳ ችግር አለ። ኢትዮጵያን የማይወዷት ትልልቅ ጎጆ ያላቸው የኢትዮጵያ ጠላቶች በኢትዮጵያ ብዙ ቢሊዮን እያወጡ ትንንሽ ጎጆ ሠርተዋል። ኢትዮጵያን ለማጥፋት የመደቡትን ገንዘብ ኢትዮጵያ እንድታድግ ግብርናው እንዲደገፍበት ቢያደርጉ ከተተከለው ዛፍ ጣውላ ከተገኘው የግብርና ምርት ርካሽ ምግብ ያገኙ ነበር። ሕዝብ ተርቦ እንዲተላለቅ ከማድረግ ይልቅ ሕዝብ በልቶ እንዲጠግብ ቢያደርጉ ሰዎች ስለግጭት ከማሰብ ይልቅ ወደ ፈጠራ በመሄድ ለሁሉም የሚበጅ መልካም ነገር ይገኝ ነበር። አሁን ግን የኢኮኖሚው ችግር የሰውን ጭንቅላት ሳይቀር አደህይቶታል። ስለዚህ ሽሮ ለመብላት ብሎ ያምታታል፤ ያጭበረብራል።

ዋናው ነገር ሰላም የሚመጣው በውሳኔ እና በድርጊት ነው። እኔ ከጎረቤቴ ጋር ችግር መፍጠርም ሆነ በሰላም መኖር እችላለሁ። ሥራዬ ብዬ ለ24 ሰዓት ቤቴን የሚነቀንቅ የሙዚቃ ድምፅ ብከፍት ጎረቤት ዝም አይልም። ግጭት ውስጥ ይገባል። በተቃራኒው ሙዚቃ



መክፈት ቀርቶ ቀን ሳይቀር በር ስከፍትና ስዘጋ ተኝተው ይሆናል ብዬ ከተጠነቀቅኩ በሰላም መኖር ይቻላል። በግልፅ መነጋገር እንጂ መደባበቅ አያዋጣም።

ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ሀገራት በሙሉ ውዝፍ ዕዳ አለባቸው። ይሔንን ውዝፍ ዕዳ በግልጽ መግለጽ እችላለሁ። ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ፣ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ወለጋ ዩኒቨርሲቲ፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ አምቦ ዩኒቨርሲቲ እና ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ለማስተማር ሄጃለሁ። ሃዋሳ፣ ጂንካ እና እንጂባራ ዩኒቨርሲቲዎች ተጠርቼ ነበር። መቀሌ ሳይቀር ልሔድ ነበር። በ2009 ዓ.ም የተማሪ ብጥብጥ ስለነበረ እንጂ ወደ ሃያ ዩኒቨርሲቲዎች ለመሔድ አቅጄ ነበር። በየዩኒቨርሲቲዎቹ የሔድኩት የትምህርት አመራር ለማስተማር እና ለምክር ብቻ ሳይሆን የችግሩን መንስኤ ለማወቅ ነበር።

የትምህርትን አመራር (academic leadership) እንዲሁ እንደተራ ነገር የሚታይ አይደለም። ትልቅ ነገር ነው። ጥበባዊ ሞኒተር እና ግምገማ ወይም ምዘና መኖር አለበት። ኢትዮጵያ ውስጥ ምዘና እና ግምገማ የሚባል ነገር የለም። እንግሊዝ ውስጥ ከፍተኛ ዋጋ በመክፈል ተቋማት ይመዘናሉ። መዛኙ ተቋሙን በዚህ በዚህ ቦታ እየተጎዳችሁ ነው። በዚህ በኩል ደግሞ እያተረፋችሁ ነው ተብሎ ያስቀመጥላቸዋል።

የማኅበራዊ ምዘና (social evaluation) ላይም ትምህርት ይሰጣል። በአደባባይ ጦርነት ስላለ ብቻ አይደለም። ዱርዬ እንደፈለገ የሚያደርግ ከሆነና ዝርፊያ ካለ ሰላም አለ አይባልም። ያው ስጋት አለ። ሰላም የለም። ጠመንጃና መድፍ አይተኮስም እንጂ ሰላም የለም። ለምሳሌ ብራዚል ውስጥ በግልፅ ጦርነት የለም። ነገር ግን ከጦርነት የበለጠ በጣም የሚያስፈሩ ቦታዎች አሉ። እንደውም በመግደል ማዕረግ ይጨመራል። አንድ ዱርዬ የገደለ ፖሊስ ማዕረጉ ያድጋል። ሪዲዮጄኔሮ ብዙ ጦርነት እንዳለ እዛው ከሚኖሩ ሰዎች ሰምቻለሁ። ባንግላዴሽም በተመሳሳይ መልኩ ጦርነት የለም ነገር ግን ሰላም ነው ማለት አይቻልም።

በትክክል ሰላም ከሆነ ውጤቱ በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም። ነገር ግን እውነተኛ ሰላም እንዲመጣ መተማመን ያስፈልጋል። በጣም ግልፅ መሆን የግድ ነው። በድብቅ በብብት ሳንጃ ተይዞ ከሆነ አስተማማኝ ሰላም ይኖራል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ተዓምር ሊሠራ የሚችል ጥበብ ያስፈልጋል። ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ከየትኛውም አካል ከዓለም ባንክም ሆነ ከየትኛውም እርዳታ እና ብድር ሰጪ አገር ምንም ዓይነት ገንዘብ ቢገኝ ኢኮኖሚውን ማሳደግ አይቻልም። በተቦደሰ እንስራ ውሃ ቀድቶ ልጆች ለማጠጣት ማሰብ ትልቅ ስህተት ነው። እርዳታ ሰጪ ሀገራትን ማመን አይገባም ።

**አዲስ ዘመን፡- ጦርነት እና ሰላም እንዲሁም ደህንነት አለመኖሩ ስነልቦና ላይ የሚያስከትለው ቁስል እንደሚኖር አያጠያይቅም። በዚህስ በኩል ምን መሠራት አለበት ይላሉ?**

**አቶ ዲባባ፡-** በአማራ ክልል የአማራ ተቆርቋሪ መስሎ ሕዝብን መከራ የሚሳይ፤ በኦሮሚያ ክልልም ለኦሮሞ ተቆርቋሪ መስሎ መከራ የሚያሳይ እየዞረ የሰው ሚስት የሚቀማ እና የሚደፍር ፤የሰው ከብት የሚሰርቅ ይሔ ሁሉ አደብ መያዝ አለበት። ግልፅ ጦርነት ብቻ ሳይሆን የደህንነት ችግርም ሥነልቦናን ይጎዳል። ቢያንስ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶቹ ቢሟሉ ትልቅ ነገር ነው። ምግብ አግኝቶ፣ ቢያንስ ውሃ ጠጥቶ ትንሽ ሕይወት እንዲዘራ መደረግ አለበት። ቀጣይ ነገሮችን እናንሳ ካልን ከባድ ነው። በመሠረታዊነት የቸገረን ነገር አለ።

**አዲስ ዘመን፡- በአገራችን ጉዳይ ላይ ያገባናል ብለው የሚያምኑ በአገር ውስጥም ሆነ በውጪ የሚኖሩ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ ሰላም እና ዕድገት ጋር ተያይዞ ምን ማድረግ አለባቸው ይላሉ?**

**አቶ ዲባባ፡-** ስለሀገር አስተዳደር ሲፈተሽ በሰለጠነው ዓለም ከመንግሥት ባለስልጣናት አጠገብ እሳት የበሉ አማካሪዎች አሏቸው። አማካሪዎቹ መሥሪያ ቤት ውስጥ ቁጭ አይሉም። በሚያስፈልገው መጠን ባለስልጣኑን ያጎርሱታል። አንድ የመሥሪያ ቤት ባለስልጣን እንዴት መሥሪያ ቤቱን መንከባከብ እንዳለበት እየፈተፈቱ ያጎርሱታል። ምሑራኖችን በአማካሪነት የሚጋብዝ ሥርዓት መኖር አለበት። በትምህርት ዘርፍ ብቁ ሲሆን፤ የትምህርት ሥርዓቱን የሚያግዝበት ሁኔታ መኖር አለበት። ይሔ ስለአንድ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚው ዘርፍም ሆነ በሰላምና ደህንነት ጉዳይ ላይ ጥበበኞች ጥበባቸውን እንዲያመጡ ምቹ ሁኔታ መፈጠር አለበት።

እያንዳንዱ ፖለቲከኛ ሁሉንም ነገር እንዲያውቅ አይጠበቅም። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጁኒየር ጆርጅ ቡሽ ከስድስት ሺ በላይ አማካሪዎች ነበሩት። ስድስት ሺ ሰው ተሰልፎ ፕሬዚዳንቱን አያገኘውም። ነገር ግን በመጠን በመጠን እየተቀመመ ይሰጠዋል። በኢትዮጵያ ስንት ቀማሚ አለ የሚለው ያጠያይቃል። ለኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያውያን አርግዘው ለምን አይወልዱም? በዕውቀት እና በሳይንስ ላይ ብቁ ሆኖ ችግር የሚፈታ ካልተፈጠረ በዝምድና ሰዎች ተኮልኩለው ችግር ይፈታሉ የሚል እምነት የለኝም። ከዚህ በፊትም የተደረገ ነገር የለም። ምን ያድርጉ አይደለም እንዴት ያድርጉ የሚለው መጥራት አለበት።

የሰው ልጅ የሚኖረው በመዋጮ ነው። በሀገር ሰው ሲኖር ለአገር መዋጮ ያስፈልጋል። ለኢትዮጵያ መዋጮ ያስፈልጋል። አንዱ ከሌላው ላይ ተዋጥቶለት ይኖራል። የምሑራን ብቻ ሳይሆን ሁሉም ለአገሩ ማዋጣት አለበት። ጥበበኛ በጥበቡ፤ ጉልበት ያለው በጉልበቱ ሁሉም በየዘርፉ እያዋጣ ይኖራል። ጽዳት ሠራተኛው በአንድ በኩል ሲሮጥ፤ ሌላኛው እሳት አጥፊው እሳት ለማጥፋት ይሮጣል። ምግብ ሠራተኛው ምግብ ለመሥራት ይሯሯጣል። ሁሉም እያዋጣ የተሳለጠ ኑሮን ይኖራል።

ነገር ግን ሁለት ነገሮች መረሳት የለባቸውም። አንደኛው አንድ አገር ጀግናዋን በጣም መንከባከብ አለባት። ሁለተኛ ዶሮ ጫጩቶቿን እንደምትጠብቅና እንደምትንከባከበው ሁሉ ሀገርም ጥበበኞቿን ከጥቃት መጠበቅ አለባት። ጥበበኞቿ የሚገደሉ እና የሚታሰሩ ከሆነ ሁልጊዜ አገር የምትኖረው በኪሳራ ነው። ጥበበኞችን ከሌሎች አገሮች መበደር አይቻልም።

የኢትዮጵያ ችግር መፍትሔ መፍለቅ ያለበት ከውስጥ ሐሞት ሊሆን ይገባል። ከእኔ አዕምሮ፣ ከእኔ ልብ፣ ከእኔ አጥንት ፈሳሽ ወጥቶ መቅኔዬ መረቅ ሆኖ ትውልድ ጠጥቶ አገሩን የሚያጠናክር መሆን አለበት። ይሔንን ኢትዮጵያ ከገበያ ሔዳ በደላላ የምትገዛው ጉዳይ አይደለም። ለእንግሊዝ አገር የደሙላት ከሐሞታቸው መፍትሔ ያፈለቁላት ዜጎች አሏት። ለፈረንሳይም እንደዛው። ለተለያዩ አገሮች ሐሞታቸውን ያፈሰሱላቸው ዜጎች አሏቸው። ወደኋላ በመሔድ የዘመናትን ታሪክ አጥንቻለሁ።

ታሪክ ስፈትሽ ሀገርን ታላቅ የሚያደርገው የሀገሬው ሰው ነው። ፍቅር መኖር አለበት። ፍቅር ያለው ሰው ወገኑን እና አገሩን አይጎዳም። ምድሩን አያዋርድም። ፍቅር ምን እንደሆነ የማያውቅ የአውሬ መንፈስ ያለበት እንጂ ሕዝቤን ምድሬን እወዳለሁ የሚል በፍፁም ይደማላታል፤ ያለውን ይሰጣታል። አይበድላትም።

አፍሪካ የተቸገረችው ፈጣሪ አሳንሷት ሳይሆን ልጆቿ መንፈስ ሆነውባት ነው። በዛ ላይ ነጮች ቁማር የሚጫወቱባቸው ሆኖ ነው። እከሌ የሚባል የውጪ ካምፓኒ ይህን ያህል አተረፈ ይባላል። ወርቅና እንቁ እያዘረፉ ዱቄት የሚለምኑ የአፍሪካ ሀገራት አሉ። በዚህ ላይ ትውልድ መንቃት አለበት። ለምን አሁንም ከሞፈር እና ቀንበር መላቀቅ አቃተን የሚለው መታየት አለብን። የእኛ አገር ድሃ ናት መባል የለበትም። ኢትዮጵያ ድሃ አይደለችም። ችግሩ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ በንጉሥ ፋሲለደስ ጊዜ ሳይቀር ለጥበበኛ ቦታ እንደማይሰጥ ፈላስፋው ዘርያዕቆብ የፃፈው መጽሐፍ አለ።

ኢትዮጵያን ትተን በሱዳን መሬት ብቻ መጠቀም ቢቻል አፍሪካን መመገብ ይቻል ነበር። ነገር ግን ሱዳን በየቀኑ እየተበጣጠሰች አንድ ነበረች ወደ ሁለት ተካፍላለች። አንዱ ጄኔራል በአደባባይ የበለጠ ዶላር ለሚሰጠን እንታዘዛለን ብሏል። ይሔንን ለማመን ይከብዳል። ከእንደዚህ አይነት ሁኔታ መላው ኢትዮጵያውያን መውጣት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ዲባባ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ነብስ አድኑ ክትባትና አሁናዊ ሁኔታው

**እፀገነት አክሊሉ**



ክትባት ማለት ሰው ራስን ከበሽታ ለመጠበቅ የሚያስችል መከላከያ ነው:: የክትባት ንጥረ ነገሮች የተገደሉ ወይም የተዳከሙ የቫይረስ ባክቴሪያና ሌሎችም ትልልቅ ጥገኛ ተዋህስያን የተሠሩ ናቸው:: በጥሩ የክትባት ግኝቶችም ብዙ በሽታዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል ወይም ጠፍተዋል:: በተለይም በወረርሽኝና በተለመደ ሁኔታ የሚነሱ በሽታዎችን ከምንከላከልበት መንገድ አንዱና ዋነኛው ነው:: በዚህም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከል በርካታ ክትባቶችን በእርዳታና በተለያዩ መንገዶች እያስገባች ትገኛለች::

ማንኛውም ሕጻን ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ በተቀመጡ የጊዜ ሰሌዳዎች መሠረት ሁሉንም ክትባቶች የማግኘት የመከተብ መብት አለው:: ይህ በትክክል በሆነ ቁጥር ደግሞ አገር ከበሽታ የጸዳ ተተኪ ትውልድን ማፍራት ትችላለች:: አንድ ልጅ የክትባት መርሐግብሩን በአግባቡና በጊዜው ካጠናቀቀ የሚከተሉት በሽታዎችን መከላከል ይችላል:: ለምሳሌ፡- ሜኒንጎካል ሜነጃይተስ፣ ሮታቫይረስ፣ ኩፍኝ፣ መምፐስ፣ ሩቤላ፣ ከወቅት ጋር የሚመጣ ኢንፍሉዌንዛ፣ ዳይፔቲሪያ ፣ ቴታነስ፣ ውፒንግ ካፍ ፣ፖሊዮ፣ አይነ፣ት ቢ ሂሞፊለስ ኢንፍልዌንዛና የኒሞኒያ በሽታን በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው::

ሁሉም ሰው ልጆቹን ከባድ ከሆነ በሽታ ለመከላከል ክትባት ቀላሉ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ዘዴ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ሁሉም ክትባቶች ለልጆች እንደሚሰጡ የክትባት መርሐ ግብር አካል በነፃ የሚሰጡ ሲሆን፤ ልጆች ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ ክትባት ወሳኝ የሆነ ዘዴ ነው:: እናም በሕይወት ውስጥ ለመልካም ጅማሮ ክትባት አይነተኛ ዘዴ መሆኑን በመረዳት ልጆችን ማስከተብ ሀገርንም ማገዝ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል።

ክትባታቸውን ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቁ ሕጻናት ከተለያዩ የበሽታ አይነቶች የተጠበቁ የመከላከል ብቃታቸውም የዳበረ ሲሆን፤ ያልተከተቡት ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ለከባድ ሕመም ተጋላጭ፤ በትንሽ በትልቁ ችግር ውስጥ የሚወድቁ ይሆናሉ:: እናም አገራችንም በተለይም እንደ ፖሊዮና ኩፍኝ እንዲሁም ሌሎቹን ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት ከመደበኛው የክትባት ፕሮግራም በተጨማሪ የተለያዩ ዘመቻዎችን በማድረግ ብዙ ርቀቶችን ተጉዛለች:: ያም ሆኖ ግን በተለያዩ ምክንያቶች በክትባት ልንከላከላቸው በምንችላቸውን በሽታዎች ዛሬም ድረስ እየተፈተንን ነው:: በዚህም አሁንም ከመደበኛው የክትባት ሰሌዳ ውጪ በዘመቻ መልክ ክትባቶችን በመላው አገሪቱ ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት እንደቀጠለ ነው::

በያዝነው ዓመት ከታኅሳስ 13 ቀን እስከ 22 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በመላው አገሪቱ በተቀናጀ ሁኔታ የኩፍኝ በሽታ መከላከያ እንዲሁም የኮሮና ቫይረስ መከላከያ ክትባትን የመደበኛ ክትባት ያልተከተቡና ላቋረጡ እንዲሁም ለሕጻናት ለመስጠት ጤና ሚኒስቴር ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ ሥራ ገብቷል:: ከክትባቱ ጎን ለጎንም አጣዳፊ የምግብ እጥረት ያለባቸውን ሕጻናት ልየታ ፣የቫይታሚን ኤ ጠብታ እደላ፣የአንጀት ጥገኛ ትላትል መድኃኒት እደላና ከወሊድ ጋር የተያያዘ ፌስቱላ ያጋጠማቸውን እናቶች ልየታ ላይ ትኩረቱን አድርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን አስታውቋል:: በተለይም ኩፍኝ በአገራችን ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ያልጠፋ ከመሆኑም በላይ እስከ አሁንም በዓለም ላይ 140 ሺህ የኩፍኝ ኬዞች ተፈጥረዋል:: በሀገራችንም ከአምስት ዓመት በታች ያሉ 1 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሕጻናት ኩፍኝን ጨምሮ ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ ምንም ዓይነት ክትባት ያላገኙ ስለመሆናቸው በጤና ሚኒስቴር ከፍተኛ የክትባት ባለሙያ የሆኑት አቶ ተመስገን ለማ ይናገራሉ:: ስለሆነም ኩፍኝ በቫይረስ ምክንያት የሚመጣ ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ሕጻናትን የሚያጠቃ በጣም ሕመም በማስከተል እስከ ሞት የሚያደርስ ነውና በክትባት መከላከል እየተቻለ ትኩረት ሊነፈገው እንደማይገባ ያስረዳሉ::

ኩፍኝ በሀገራችንም ስርጭቱ ከ ከ1 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ ከ20 እስከ 50 የኩፍኝ በሽታ ታማሚዎች ይገኛሉ:: ይህ ደግሞ ስርጭቱ ቀላል አለመሆኑን ያሳያል:: በመሆኑም ክትባት መስጠት በሽታው የሚያስከትለውን ሕመምና ሞት ያስቀራል:: ክትባቱንም ሕጻናቱ ሲያገኙ የሰውነታቸውን በሽታን የመከላከል አቅም እንዲጨምር ያደርገዋል:: እናም አቶ ተመስገን እንደሚሉት፤ ክትባቱን ከ95 በመቶ በላይ መከተብ ሲቻል በተከተቡት ሕጻናት ምክንያት ሌሎች ሕጻናትን ከበሽታው መጠበቅ ይችላልና መከተብን ቅድሚያ እንስጠው::

ክትባት ውጤታማ የሚሆነው አንድና ሁለት ሕጻናትን በመከተብ ሳይሆን ከግማሽ በላዩን ማግኘት ሲቻል ነው:: የክትባት ዋና ጥቅምም ይህ ነው:: አንድ ልጅ የኩፍኝ ክትባትን ተከትቧል ለመባል ሁለት ጊዜ መከተብ አለበት:: በዚህም በተወለደ በዘጠነኛ ወሩ ከዚያ በኋላ ደግሞ አምስት ዓመቱ ላይ መከተብ ይገባዋል:: ስለዚህ ኅብረተሰቡ ይህንን ተረድቶ ልጆቹን ማስከተብ እንዳለበትም ያስገነዝባሉ::

እስከ አሁን በሀገራችን ይሰጥ የነበረው ልጆች ዘጠነኛ ወር ላይ ሲሆኑ ብቻ ነበር የሚሉት አቶ ተመስገን፤ ከኅብረተሰቡ የግንዛቤ ችግር አንጻር እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮች በስፋት በመኖራቸው የኩፍኝ ክትባትን በሁለት ዙር መስጠትን እንደ ሀገር በፖሊሲ ደረጃ ጸድቆ ለመጀመር አስገድዷል:: ይህም ቢሆን ግን የተሠራው ሥራ ውስን በመሆኑ ኅብረተሰቡ እየተረዳውና እየለመደው እንዳልመጣ ያነሳሉ::

የኩፍኝ ክትባት አሰጣጥ ላይ እንደ ሀገርም ችግር ያለብን መሆኑን የሚያሳየው የበሽታው ስርጭትና የመግደል መጠን ከዓመት ዓመት ያለመጥፋቱ ነው:: በዚህም እኤአ በ2015 ላይ 197 የነበረው እኤአ በ2016 ወደ 50 ዝቅ ብሎ ነበር፤ እኤአ በ2021 ላይ ደግሞ 18 ሕጻናት ሕይወታቸውን አጥተዋል:: ብዙ ጊዜም ዘመቻዎች የሚደረጉትም የበሽታውን ስርጭት ለመግታት፣ የከፋ ሞትና ሕመም እንዳይመጣ ለማስቻል ነው:: አሁንም በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የኩፍኝ ወረርሽኝ በመኖሩ ምክንያት የዘንድሮው ዘመቻው ማስፈለጉን ይገልጻሉ::

በአሁኑ ወቅትም አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ክልል እንዲሁም አፋር ላይ የኩፍኝ በሽታ ወረርሽኝ እንዳለ መረጃዎቻችን ያሳያሉ ያሉት አቶ ተመስገን፤ እነዚህ ቦታዎች ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከፍ ያለ አለመረጋጋት የሚታይባቸው በመሆናቸው አሁንም ተደራሽነቱ ላይ ችግር ያጠላ ሊሆን ይችላል:: እናም ዘመቻውን በተቻለ መጠን ለማድረግና ወረርሽኙን አማራጭ እንዳይጠቀምብን ለማድረግ ይሠራል:: በአሁኑ የተቀናጀ የኩፍኝ መከላከያ ክትባት ዘመቻ ላይም ከተወለዱ ሕጻናት ጀምሮ ምንም ዓይነት ክትባት ያልወሰዱ ፣ ጀምረው ያቋረጡ ሕጻናት ልየታና ክትባት የሚሰጥ ይሆናል::

ጎን ለጎንም መጠኑ እየጨመረ የመጣው የኮሮና ቫይረስ ክትባት ይሰጣል:: በተለይም ክትባቱ እስከ አሁን ላልተከተቡ እንዲሁም በጠርነት ቀጠና ውስጥ ለነበሩና ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች ልዩ ትኩረት ይቸራቸዋል:: በመሆኑም በመላው አገሪቱ ያሉ እናቶች ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ልጆቻቸውን የተቀናጀ የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት እንዲሁም ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸውን ወጣቶች ደግሞ የኮሮና ቫይረስ መከላከያ ክትባትን በአቅራቢያቸው ባሉ ጤና ኬላዎች ወይም ጊዜያዊ ጣቢያዎች እየሄዱ እንዲያስከትቡ ሲሉ ይመክራሉም::

## ቴሌ ሜዲስን የጤናው ዘርፍ ምርኩዝ

**እፀገነት አክሊሉ**

ዶክተር ይቅናሸዋ ሰለሞን ይባላል:: በቅዱስ ጳውሎስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የስነ አዕምሮ ሰልጣኝ ሐኪም ሲሆን፤ በአገራችን ያለው የአዕምሮ ሕመምተኛ መጠን 27 በመቶ አካባቢ እንደሆነ ያስረዳል:: ይህ ደግሞ ከሆስፒታሎቻችን አቅም እንዲሁም ከባለሙያው ቁጥር አንጻር የማይመጣጠን ነው:: በመሆኑም ብዙ ቁጥር ያለውን ታካሚ ለማየት ማድረግ የሚቻለው ነገር ቴክኖሎጂን መጠቀም እንደሆነ ያነሳል::

እስከ አሁን ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ የሕክምና አገልግሎትን ማግኘት እድሉ ያልነበረ ከመሆኑ አንጻር በርካቶች አገልግሎት ማግኘት ሲገባቸው ሳያገኙ ቀርተዋል:: ይህ ደግሞ አገልግሎት ፈላጊውን በሆስፒታሎች እየተመላለሰ እንዲሰላች አድርጎታል:: ነገር ግን ቴሌ ሜዲስን ኔትዎርክ ማበልጸግ ቢቻል ይህ ነገር በሙሉ መፍትሔ ያገኝ ነበር:: የአፍሪካ ሀገራት ደግሞ የራሳቸው የሆነውን ቴሌ ሜዲስን ማበልጸጋቸው እጅግ የሚያስደስትና እነዚህ ሁሉ ችግሮች የሚፈታ ነው ባይ ነው::

አገልግሎቱ በቦታና በጊዜ የሚገደብ ስላልሆነ በአቅም ችግር በቦታ ርቀት ወደጤና ተቋም መምጣት የማይችሉትን ብሎም መጥተውም የሚፈልጉትን ስፔሻሊስት ማግኘት ላልቻሉ አካላት ባሉበት ቦታ ሆነው የተንቀሳቃሽ ስልካቸውን በመጠቀም የሚፈልጉትን ጠይቀው ተረድተው ምርመራቸውን እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል:: የሚያስፈልጋቸውን መድኃኒት ታዞላቸው በቀላሉ እንዲጨርሱም ይሆናሉ:: ይህ ደግሞ በተለይም ከስነ አእምሮ ሕክምና ጋር ተያያዥነት ያለውና ለህክምናውም ከፍ ያለ ጥቅምን የሚሰጥ ሁኔታ አለውም ይላል::

"የሥነ አዕምሮ በሽታ በአብዛኛው በንግግርና በመድኃኒት የሚታከም ሕመም እንደመሆኑ መጠን ቴሌ ሜዲስን ደግሞ ጥሩ አማራጭ ነው:: ግለሰቡ ያለበትን

**ዜጎች ከየትኛውም የአህጉሪቱ ክፍል፤ ገጠራማውን አካባቢ ጨምሮ ማንኛውንም አይነት ሕክምና በሚያሻቸው ወቅት ካሉበት ሆነው፥ ስልካቸው ላይ በሚጭኑት ሃባሪዶክ (HabariDoc) የሞባይል መተግበሪያ የሚያሻቸውን የጤና ባለሙያዎች በኢንተርኔት አማካኝነት ብቻ የማግኘት፣ የማማከር እንደ አስፈላጊነቱም ቀጠሮ የማስያዝ ብሎም ለአገልግሎት የሚያስወጣቸውን ክፍያ በ online የክፍያ ሥርዓት ዝርጋታ መፈፀም የሚያስችላቸው ነው።**

ችግር በቀጥታ ከሐኪሙ ጋር እየተወያየ ሐኪሙም በንግግር የሚመክረውን ምክርም ሆነ የሚያዝለትን መድኃኒት በዛው መጨረስ ይችላል:: ይህ በጣም ፈጣን ቀልጣፋ 24 ሰዓት የሚሠራ በመሆኑ ጥቅሙ የጎላ ነው" ብሏል::

አገልግሎቱ ከከተማ እስከ ገጠር ድረስ የተዘረጋ ነው:: በቀጣይ ሊሠራ የሚገባው ነገር ቴክኖሎጂውን እንዴት መጠቀም ይቻላል የሚለው ላይ ነው፤ ይህንን ደግሞ በመላው አገሪቱ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ለማድረግ በሚያግባባቸው ቋንቋዎች ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል የሚል እምነት አለው::

በክሊኒካል ፋርማሲስትነት የምትሠራው ሕይወት ግርማ በበኩሏ፤ ቴሌ ሜዲስን አሁን ሀገራችን ያስፈልጋታል ከሚባለው የጤናው ዘርፍ ምርኩዝ አንዱና ዋነኛው እንደሆነ ታነሳለች:: ይህንንም የተገነዘቡት በኮቪድ ወቅት የተስተዋለው የታማሚና የኅብረተሰቡ መራራቅ እንደነበር ታወሳለች:: ስለዚህም ይህንን መራራቅ ለማቀራረብ ደግሞ እንደ ቴሌ ሜዲስን ዓይነት መላዎች በጣም ያስፈልጉ ነበር:: አሁን ላይም ይህ እውን መሆኑ በጣም አስደሳች ነው ትላለች::

ሌሎች አገሮች በዚህ ዘርፍ ብዙ ርቀትን ለመጓዝ ችለዋል:: እኛ ደግሞ ወደኋላ ነበርን:: ነገር ግን ይህ ሥራ ይህንን ርቀታችንን የሚያጠብና እነሱ የደረሱበት ላይ ከማድረስም ባሻገር በጤናው ዘርፍ ላይ ያሉትን ባለሙያዎች በሙሉ ከበሽተኞች ጋር በቀላሉ ለማገናኘት ጥሩ አማራጭ ነውና እንድንጠቀምበት ትመክራለች::

አሁን ሀገራችን ላይ አንድ የጤና ባለሙያ ለ10 ሺህ ሕመምተኞች ነው:: ይህ ደግሞ በጣም አስቸጋሪ ነው:: አብዛኞቹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ በገጠሪቱ የሀገሪቱ አካባቢ ላይ የሚገኙ ናቸው፤ በመሆኑም እነሱም የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ከማስቻል አንጻር ጥሩ መላ ነው ያለችው ሕይወት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከተማ ላይ ያሉ ሆስፒታሎችም ቢሆኑ የሚያስተናግዱት የታማሚ ቁጥር ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ ነገሮችን ያቀልላቸዋልና ማየቱ ያስፈልጋል:: ጤና ሚኒስቴር እንደ ሀገር ዘርፉን ለማሳደግ ችግሮቹን ለመፍታት ሰፋ ያለ ጥረት እያደረገ ብዙ ሥራዎችንም እየሠራ ነው፤ ነገር ግን ውጤታማነቱ ብዙም አይደለም:: እንደዚህ ዓይነት ቴክኖሎጂዎች ጥረቱን ከማገዛቸውም በላይ የሚታዩ ለውጦች እንዲመጡ የራሳቸውም ሚና ይጫወታሉ:: እናም ቢመለከታቸው ስትልም ሀሳቧን ታስቀምጣለች::

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ ቴክኖሎጂው ይፋ በሆነበት ወቅት እንዳሉት፤ ይህ ቴክኖሎጂ ኢትዮጵያ እኤአ በ2020 ሀገሪቱን ወደ ዲጂታሉ ዓለም በይበልጥ ለማስገባት ዓላማ አድርጋ ከምትሠራቸው ሥራዎች ጋር ተያያዥነት አለው:: ስለሆነም ቴሌሜዲስን አፍሪካ ውስጥ ላሉ አዳጊ ሀገራት ብዙ እንቅፋቶችን በማስወገድ አዎንታዊ ፋይዳ ይኖረዋል::

የአሜሪካ ሚዲካል ሴንተር ባለቤት ዶክተር አከዘ ጣዕመም ይህንን ሀሳብ ይጋራሉ:: አክለውም የሕክምና ባለሙያዎች በቁጥር እጅግ አናሳ ናቸው:: እናም አሁን ላይ ባለን የሕክምና ባለሙያዎች አቅርቦት ስሌት የዓለምን ሕዝብ የጤና ሽፋን ለማዳረስ አዳጋች ነው:: ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ሦስት መቶ ዓመታት ይፈጅባቸዋልም:: በዛው ልክ እጅግ እየፈጠነ ያለው የሕዝብ ብዛት ይህንን ስሌት ያባብሰዋል:: ስለሆነም ከማመጣጠን የዘለለ ችግር ያለበትን የሕክምና ባለሙያዎችና ሕክምና የሚያሻቸውን ሕዝቦች ተደራሽ ለማድረግ ቴሌ ሜዲስን ፕላትፎርም ፋና ወጊ ተስፋ ነው ብለዋል:: ታካሚውና የሕክምና ባለሙያው አካላዊ መገኘት ሳያሻቸው በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በመታገዝ ማንኛውንም ዓይነት ሕክምና ሰዎች ሆስፒታል መምጣት ሳይኖርባቸው የሚታከሙበት አማራጭ ነውና ለሕክምናው ዘርፍ የገዘፈ ስኬት እንዳለውም ተናግረዋል::

በአህጉሪቱ ያሉትን የጤና ባለሙያዎች በአንድ ጥላ ስር በዲጂታል የጤና ኔትወርክ ማስተሳሰር ያስችላል የተባለለት ይኸው አገልግሎት አሜሪካን ውስጥ የተጀመረ ሲሆን፤ ሁሉም የአፍሪካ ሀገራት የራሳቸውን ቴሌሜዲስን ኔትወርክ በተናጠል ፤ ብሎም በአህጉሪቱ ስር ያሉትን ደግሞ በአንድ ጥላ የሚተሳሰሩበትን የዲጂታል አሠራርን ይዞ መጥቷል። አገልግሎቱ ደግሞ ዜጎች ከየትኛውም የአህጉሪቱ ክፍል፤ ገጠራማውን አካባቢ ጨምሮ ማንኛውንም አይነት ሕክምና በሚያሻቸው ወቅት ካሉበት ሆነው፥ ስልካቸው ላይ በሚጭኑት ሃባሪዶክ (HabariDoc) የሞባይል መተግበሪያ የሚያሻቸውን የጤና ባለሙያዎች በኢንተርኔት አማካኝነት ብቻ የማግኘት፣ የማማከር እንደ አስፈላጊነቱም ቀጠሮ የማስያዝ ብሎም ለአገልግሎት የሚያስወጣቸውን ክፍያ በ online የክፍያ ሥርዓት ዝርጋታ መፈፀም የሚያስችላቸው ነው።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ሀገር ፍቅር፡- ነባሪ፤ ታሪክና ህላዌ

**ማዋዣና መንደርደሪያ፤**

ሰሞኑን በሀገር ፍቅር ቴአትር የተገኘሁት እግር ጥሎኝ እንጂ ለትዕይንተ ጥበባቱ ድግስ ታዳሚ ሆኜ አልነበረም:: በኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር የተጻፈ አንድ "የትብብር መጠየቂያ" ደብዳቤ ለማድረስ በተገኘሁበት በዚያ አጋጣሚ እጅግ ብዙ ጉዳዮችን ለመታዘብ ችያለሁ:: ቅጥረ ግቢው ውስጥ ዘልቄ እንደገባሁ አንዳች ሀሴት ይሉት መግነጢስ ሲያነዝረኝና ሲወረኝ ታውቆኛል::

በልጅነት፣ በወጣትነትና በጉልማሳነት የዕድሜዬ እርከኖች ጉዞ የቤቱን ያህል የማውቀው ያ ዘመን ጠገብ ግቢ "መታደስ" ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ ይዘቱን ሳይለቅ "ሥር ነቀል" ለውጥ ተደርጎበትና ተውቦ ማየት ስሜትን በደስታ ያረሰርሳል:: ከዓመታት በፊት በቴአትር ቤቱ መድረክ ላይ በቀረቡት ውሱን ቴአትሮች ላይ የዚህ ጋዜጣ እህት በነበረችው ተወዳጇ "ነፍሰ ሄር" የዛሬይቱ ጋዜጣ ላይ ያቀረብኳቸው ሂሳዊ ጽሑፎች እየታወሱኝም በትዝታ መንጎዴ አልቀረም::

የብርሃኑ ዘርይሁን "ባልቻ አባነፍሶ"፣ በተፈሪ ዓለሙ የተተረጎመው "አሉ"፣ የፍስሐ በላይ ይማም "የወፍ ጎጆ"፣ በመስፍን ዓለማየሁ ተተርጉሞ አርቲስት ደበበ እሸቱ የትወና ጥበቡን አሟጦ ችሎታውን ያስመሰከረበት "የቬኒሱ ነጋዴ" በዕድሜ ዘመኔ ሁሉ በፍቅር እንደታወሱኝ ይኖራሉ:: እነዚህ ድንቅ የጥበብ ውጤቶች በድጋሚ ለመድረክ መቅረብ ቢችሉ ተሸቀዳድሜ ለትኬት ግዢው ሰልፉን ለመምራት አልቦዝንም ነበር::

የዕድሜዬን ሦስት አራተኛ ያህል አውቀዋለሁ የምለው ያ ግቢ ከጥቂት ዓመታት በፊት የነበር ታሪኩና የትዝታው ክብር ሳይነካ ይመሳሰልብኝ የነበረው "እርጅና ተጫጭኗቸውና ጥርሳቸው በሙሉ ረግፎ በድዳቸው ፈገግ በማለት ዘመናቸውን እንደሚታዘቡ አንድ የከበሩ አዛውንት" ነበር:: ያለፈውን ዝርዝር የድክመት ገመና እንዲህና እንደዚያ ነበር በማለት ዛሬ ላይ ቆሞ መተረኩ እጅግም ስለማያንጽ ጥቁምታውን ብቻ ለአንባቢያን ፈንጥቆ ማለፉ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም::

ያ ተዘንግቶ የኖረው "የማዕደ ጥበባት" ቅጥረ ግቢ ቀን ወጥቶለት ተለውጦና አምሮ መመልከት በእጅጉ ደስ ያሰኛል:: በዚያ እግር በጣለኝ እለት ባለሙያዎቹም ሆኑ የሥራ ኃላፊዎቹ "ተፍ ተፍ" ሲሉ ያስተዋልኳቸው ፊታቸውን አኮስትረው ሳይሆን በፈገግታ እየተፍለቀለቁ ነበር:: የቤተ ተውኔቱ ሁለቱ ታሪካዊ አዳራሾች (ትልቁና ትንሹ)፣ ቢሮዎቹና መሰል መገልገያዎቹ በሙሉ የይዘት ተሐድሶ ተደርጎላቸዋል::

በተለይም "መለኪያ" ይጋጭበት የነበረውና ለረጅም ዘመን ቴአትር ቤቱን ሲያስወቅስና ሲያስተች የነበረው "ክበብ ተብዬ" ከፊት ለፊት ዞር ብሎ ወደ ጀርባ መዞሩ ሌላው አስመስጋኝ ተግባር ነው:: በውጫዊ ይዘቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በጥበብ ዝግጅቶቹም ላይ ተሐድሶው ነፍስ ዘርቶ አዳዲስ ዝግጅቶችን እንደምንመለከት ተስፋ አደርጋለሁ::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለዚህ አንጋፋ ቴአትር ቤት ትኩረት ሰጥቶ ትርጉም ያለው "የቅርጽ ተሐድሶ" ሥራ በመሥራቱ ምሥጋናችንን ብንቸረው ተገቢ ይመስለናል:: ብዕረ መንገዴን ሳልጠቅሰው የማላልፈውን አንድ ሌላ ተያያዥ ጉዳይ ላስታውስ:: ወግ ባለው ሁኔታ አምሮና ሰምሮ የተሞሸረው የአዲስ አበባ ባሕልና ቴአትር አዳራሽ ዕጣ ፈንታስ ምን ሊሆን ነው? የጥበብ ቤትነቱ ተለውጦ የፖለቲካ ሸንጎ መሰብሰቢያ ብቻ ሆኖ መቅረቱ ይሆንን?።

የከተማችን አስተዳደር ተገቢውን መልስ ሰጥቶ እህህ! እያሰኘ እንደ ሻህላ በቁጭት ሆድ ሆዳቸውን ለሚበላቸው የቤተ ጥበቡ ባለሙያዎችና ለሰፊው የከተማው አፍቃሬ ጥበብ ነዋሪዎች ቁርጡን ቢያሳውቅ አይከፋም:: የማዘጋጃ ቤቱ የቴአትር አዳራሽ የታደሰው ለጥበብ ሥራ ወይንስ ለሌላ ዓላማ? ሳይድበሰበስ ቢገለጽልን አዲስ አበባም ከሐሜት ትድናለች እኛም ከትዝብትና ከጉርምርምታ አደብ ገዝተን አርፈን እንቀመጣለን::

**"የሀገር ፍቅር"፡- ዝክረ ታሪክ፤**

"የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገር ፍቅር ማኅበር" የተመሠረተው ሐምሌ 11 ቀን 1927 ዓ.ም ነበር:: ዕድሜውን እናስላ ካልን 88 ዓመቱን ደፍኗል:: "ይህ የፍቅርና የአንድነት ጉባኤ" እንዲመሠረት ምክንያት የሆነው በሀገራችን ላይ አንዣቦ የነበረው የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ነበር:: ገና ከጅምሩ የማኅበሩ አባላት የወራሪውን ሠራዊት ይቃወሙ የነበረው በስብከት፣ በግጥም፣ በዜማ፣ በፉከራና በቀረርቶ እንደነበር በታሪኩ መዘክር ውስጥ በዝርዝር ተመልክቷል::

እነዚህን መሰል የቅስቀሳ ሥራዎች ይከወኑ የነበረው በወቅቱ ዝነኛ በነበሩት ባለቅኔዎች፣ ደራስያን፣ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች፣ የመንግሥት ሹማምንትና በተመረጡና አንደበተ ርቱዕ በነበሩ ዲስኩረኞች አማካይነት ነበር:: ሕዝቡ ጉልበቱ ሳይላላ አንድነቱን ጠብቆ ሊወረው የመጣውን ጠላት እንዲመክትና ራሱን እንዲያዘጋጅ ይኾጎደጉዱ የነበሩት የንግግርና የጽሑፍ መልዕክቶች፣ ግጥሞችና ፉከራዎች በእጅጉ የሚያስገርሙና ወኔን በማኮስተር የሚያጀግኑ እንደነበሩ ታሪክ ምስክርነቱን ይሰጣል::

ከብዙዎቹ የወቅቱ ተጠቃሽ ባለታሪኮች መካከል፤ ዮፍታሔ ንጉሤ፣ ተሰማ እሸቴ፣ አበበ ወልዴ፣ መላኩ በጎሰው፣ ሣህሌ ፀዳሉ፣ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፣ ተስፋ ገ/ሥላሴ፣ ሀጂ በዳሶ፣ ተመስገን ገብሬ፣ ደምስ ወ/አማኑኤል ወዘተ. የመሳሰሉት በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ:: ከእነዚህ የሀገር ባለውለታና የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጆች መካከል በወቅቱ ለቅስቀሳ የዋሉ ጥቂት የግጥም ስንኞችን እየመዘዝን እንደሚከተለው እናስታውሳለን:: ዮፍታሔ ንጉሤ በ1927 ዓ.ም ካስነበቧቸው ግጥሞች መካከል አንዱና ተደጋግሞ የሚታወሰው ይህ ግጥም ሳይደበዝዝ በብዙዎች ዘንድ እንደተጠቀሰ እነሆ ዛሬን ደርሷል::

**"አጥንቱን ልልቀመው መቃብር ቆፍሬ፣**
**ጎበናን ከሸዋ አሉላን ከትግሬ፣**
**ስመኝ አድሬያለሁ ትናንትና ዛሬ፣**
**አሉላን ስጥይት ጎበናን ስጭሬ::**
**አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ፣**
**ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ የእምቧይ**
**ካብ::"**

በኋለኛው ዘመን በደራሲነታቸውና በጋዜጠኝነታቸው የሚታወቁት ወልደ ጊዮርጊስ ወ/ዮሐንስም በዚያው ዓመት ለሕዝብ ያሰራጩት ግጥም እንዲህ ይነበባል::

**ደሙ እየተረጨ አጥንቱ እስኪፈስጥ፣**
**ሰው ሳገሩ ቢሞት ምንም አይቆጠቁጥ::**
**የሀገርን ፍቅር አጥብቀን ስናይ፣**
**ሰው ሳገሩ ቢሞት ቁምነገር ነው ወይ?**
**ጠላት በዋናው ሳይ ትርፍ አገኛለሁ ሲል፣**
**እኛስ ከዋናችን ስለምን እናጉድል::**
**ተጋዳይ፣ ተጋዳይ፣ ተጋዳይ አርበኛ፣**
**እንዴት ያመልጥሃል ያገርህ ደመኛ::"**

በሥዕል ጥበባቸው ከፍተኛ አድናቆት የተቸራቸው ሠዓሊ አገኘሁ እንግዳም በዚያው በ1927 ዓ.ም ከተቀኟቸው ግጥሞች መካከል አንዱ ይህ ነበር::

**ይህ የመጣ ጠላት ሳይደርስ ከጠረፍ፣**
**ተነሱ እንነሳ ደማችን ይፍሰስ::**
**ይሂድ ይቀሳቀስ ከዓባይ ጋር ይውረድ፣**
**ነፃነት ያጣ ሕዝብ አይባልም ወንድ::"**

እነዚህን የመሳሰሉ ግጥሞች በጋዜጣ፣በበራሪ ወረቀቶችና በመጻሕፍት እየታተሙና እየተሠራጩ ለሕዝቡና ለሠራዊቱ ይበተኑ ነበር::

በጠንካራ መሠረት ላይ የተመሠረተውና ወደ ዘጠኝ አሠርት ዕድሜ እየተጠጋ ያለው የሀገር ፍቅር ቴአትር ሀገራዊ አደራውን እንደጠበቀ ከትውልድ ትውልድ ተሸጋግሮ ዛሬ ላይ ደርሷል:: ይህ አንጋፋ የጥበብ ቤት ቢቻልና ቢሆንለት በተደራጀና በተጠና መርሐ ግብር የዛሬ ኑባሬ (አኗኗራችንንና ዐውዳዊውን ውሎ አምሽቷችንን) ከትናንቱ ታሪክና ተሞክሮ ጋር በማስተሳሰር "በታደሰው መድረክ" ላይ ዝግጅቱን ቢያቀርብልን ጎላዌነቱን አክብሮና አድምቆ ማሰንበት ለመቻሉ አያጠራጥርም::

ያለበለዚያ አካልቦ በሚያካልበው በዚህ በእኛ ዘመን አረጋግተውንና አስክነውን ወደ ቀልባችንና ወደ ሩሐችን እንድንመለስ መግራት ብቻም ሳይሆን ዳግም እንዳንስትም ወደሚያስጠነቅቁን የጥበብ ሥራዎች እስካላተኮርን ድረስ ዮፍታሔ ንጉሤ እንደተቀኙት "ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ" መሆኑ አይቀሬ ይሆናል:: በእድሳት የተሞሸረው ታሪካዊው የሀገር ፍቅር ቴአትር ይህን አደራ ተሸክሞ እንደተለመደው ትውልዳዊ ኃላፊነቱን እንደሚወጣ ተስፋ እናደርጋለን::

**ጭጋግ ያጠላበት ሀገራዊ ፍቅር፤**

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ለራሷ ለሀገሪቱም ሆነ ለዜጎች ዕንቆቅልሽ ለመሆን ዳር ዳር ወደሚባል ደረጃ እየተደረሰ መሆኑን በብዙ ውሎ አምሽቷችን እያስተዋልን ነው:: በዓለም ታሪክ (ተመዝግቦም ይሁን ወይንም በአሉ ተባባሉ ቅብብሎሽ) በአደባባይና በፀሐይ ፊት ሀገሩን በክህደትና በእብሪት እያንኳሰሰ "ገሃነም ትግባ፣ ትበጣጠስ፣ ትፈራርስ ወዘተ." እያለ ክፉ የተመኘና ክፉ የሚመኝ ትውልድ ከእኛ ውጭ መኖር ስላለመኖሩ እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: እንደሚመስለን ግን ይህን መሰሉ "ሠይጣናዊ ምኞት" ከፉና እርኩስ መንፈስ የሚያቀብለው የተረገመ ሃሳብ ካልሆነ በስተቀር ከጤናማ አዕምሮ የሚወጣ አይመስለንም::

ስለ ትልቋ ኢትዮጵያ ከመመስከር ይልቅ ስለ ራስ ጎጥና ብሔር ብቻ የተለየ ክብር መስጠት፣ በገናና ታሪክ ከመኩራት ይልቅ በተናጠል ማንነት ላይ ተንጠልጥሎ ዥዋዥዌ መጫወት የዘመናችን ፋሽን ከሆነ ሰነባብቷል:: በፍልስፍናው ጎራ "ሥነ ኑባሬ" የሚባል የመሚገቻ ሃሳብ በዘርፉ ባለሙያዎች የተለመደ የእንካ ሰላንትያ መፋለሚያ ርዕስ ነው:: የሥነ ኑባሬ ፍልስፍና በአብዛኛው በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ነው:: አንዱ በአካል ወይንም በማንነት ላይ ሲሆን ሁለተኛው በምንነት ላይ አጽንኦት ይሰጣል:: ስለዚህም "አካል" የኅላዌ መገለጫ ብቻ ሳይሆን የአካል መሠረትም ጭምር ነው::

አካል በራሱ ግዘፍ የነሳ ተፈጥሮ ነው:: ያ አካል ካላሰበ፣ በምክንያታዊነት ካልተመራ፣ ለነፍሱና ለሚገዳደረው የእውነትና የኅሊና ሙግት ምላሽ ለመስጠት ዳተኛ ከሆነ ወይንም ቅርብ ማደር ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ ሩቅ ከማሰብ ከተፋታ ውጤቱ የቁም ድንዛዜ ብቻ ሳይሆን ያ አካል ተብዬ ሰብዕና ትርጉም እንደጠፋበት ለማረጋገጥ አይከብድም::

"የሰው አካል" ማገናዘብ፣ ማሰብና ማሰላሰል፣ ከተሳነውና ለእውነት፣ ለፍትሕና ለበጎነት መጨከንን ችላ ማለት ከጀመረ "ሰው መባል ብቻ" ከተራ ቁስነት በምንም ሊሻል አይችልም:: በተለይም ጤነኛ አቋምና ሰብዕና ያለው ዘረ አዳም አዕምሮውንና ጊዜውን ለነፍሱና ለጉርሱ ብቻ መድቦ ከኖረ ምንትስ ከምንላቸው ፍጡራን በምንም ሊሻል አይችልም:: ይህ ፍልስፍና ትንሽ ረቀቅና ጠነን ስለሚል አቅልሎ ለማስረዳት ፈታኝ መሆኑ አይቀርም:: "መሆን ወይንም አለመሆን" የሚለው ሙግት የሚታወሰው እዚህ ላይ ነው::

ወደ ዋናው ጉዳያችን እንመለስና የሀገር ፍቅር መገለጫዎች እነዚህና እነዚያ ብቻ ናቸው ብሎ ለመበየን ይሞከር ካልሆነ በስተቀር ድምዳሜ የሚሰጥበት ጉዳይ አይደለም:: የሀገር ፍቅር ተዘርቶ፣ እየተኮተኮተና እየታረመ የሚፋፋ ስሜት እንጂ እንደ ወፍ ዘራሽ ፍሬ በተገኘው ቦታ ላይ የሚበቅል ተክል አይደለም:: የዘሩ መደብ የልጅነት ዕድሜ ነው:: በቀዳሚነት "መደቡ" መለስለስ የሚጀምረው በቤተሰብ ጓዳ ውስጥ ነው::

"ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው" እንዲል ቅዱስ መጽሐፍ፣ ቤተሰብ ለብዙ ሰብዓዊ ሥሪቶቻችንና የባህርይ ቀረጻ ዋናው ምንጭ ነው:: ይህ ከፍተኛ ኃላፊነት የወደቀበት የቤተሰብ ተቋም ችግር ኖሮበት ኃላፊነቱን ካልተወጣ ወይንም ምንጩ በተለያዩ ችግሮች የተበከለ ከሆነ ጨቅላ ዕድሜን በሀገር ፍቅር ለማነጽ ቀርቶ ራሱ ቤተሰቡ የችግሮች መፈልፈያ መሆኑ አይቀሬ ይሆናል:: የሀገሬ ቤተሰብ ይህንን ወሳኝ ጉዳይ ልብ ሊል ይገባል::

ከቤተሰብ ከፍ ሲል ማኅበረሰቡም ለሀገር ፍቅር ስሜት መዳበርና መጎልበት ድርሻው የላቀ ነው:: ጉርብትናው፣ የቤተዘመድ ቅርርቡና ተዛምዶው፣ የአካባቢው ልዩ ልዩ ተቋማት (ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ዘርፎች) ሚናቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ከፍ ሲልም የኅብረተሰብ ድርሻ (የትምህርት ሥርዓቱ፣ ፖለቲካው፣ ኪነ ጥበቡ፣ ሚዲያውና ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ ተቋማትና ክስተቶች) የዜጎች የሀገር ፍቅር ስሜት ወይ እንዲጎለበት አለያም እንዲጨነግፍ የሚያበረክቱት አሉታዊም ሆኑ አወንታዊ ተጽዕኖዎች ከሚገመተው በላይ የበረቱ ናቸው:: በዚህም ጉዳይ ላይ ልብ ገዝተን ልብ ልንል ይገባል::


በተለይም ቤተሰብ ውስጥ የተዘራው ዘር በትምህርት ቤት ውስጥ ሥር ካልሰደደ፣ ሥር የያዘው ዘርም በአትኩሮት ማኅበራዊና መንግሥታዊ ድጋፍ ካልተደረገለት በስተቀር "የሀገር ፍቅር" የምንለው ፀጋ ለመጠውለግ ፈጣን፣ ለመወየብም ቅርብ ነው:: እናስ ዛሬ በስፋት ሀገርን መውደድ የምንለው ስሜት ጭጋግ አጥልቶበት "ምን ግዴ" ትውልድ ሊፈጠር የቻለው በምን ምክንያት ነው? ከትልቅነት ይልቅ ማነስን፣ ሰፋ ያለ አመለካከትን በመጠየፍ መጥበብን ምርጫ አድርጎ የአስተሳሰብና የአመለካከት ድንክነት እንዲንሰራፋ ምክንያት የሆነው ሀገራዊ ችግራችን ምንጩ የተበላሸው የትና በምን ዓይነት አረም ተጠቅቶ ይሆን?

ከትልቅ ሀገርና ባለሀገርነት ይልቅ "እኔን ራሴን እና የእኔን" ብቻ አስቀድሙልኝ ማለትን ምልዑ በኩለሄ ምርጫችን አድርገን ነገሮችን ሁሉ በራሳችን ክበብ ውስጥ ለማሽከርከር ያስመኘንና ያስጨከነን ምን ይሉት አዚም ነው? የጥቂቶች ፍላጎትና የውስን ፖለቲካዊ ርዕዮት ተጽዕኖ ምክንያት ሆኖ ከሆነም ቆም ብሎ ማሰቡ፣ ሳይዘናጉ ግራ ቀኝ አስተውሎ መራመዱ ስለሚሻል "ጆሮ ያለው ይስማ፣ ልቦና ያለው ያስብ" የአዋጃችን መደምደሚያ መልዕክት ነው:: ያለበለዚያ ግን በመነሻችን ላይ እንደተንደረደርንበት ተዘንግቶ እንደኖረው የሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ይዞታ "ታሪክና ትዝታ በመሸከም" ነበርን ብቻ እየተረክን እንዳናልፍ ሀገራዊ መነቃቃትና ተሐድሶ ያስፈልግ ይመስለናል:: **ሰላም ይሁን::**

# ተናጋሪው ዶሴ

## ‹‹ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ...››

አስመረት ብስራት



ሁለት ባዕዳን የሆኑ ተቃራኒ ጾታዎች በፍቅር የሚመሰርቱት ቤተሰብ መተሳሰቡ፣ ፍቅሩ ፣አንተ ትብስ አንቺ መባባሉ በዛን መካከል ደግሞ የሚፈጠረው ውህድ ህጻን የቤተሰቡ ድምቀት ይሆናል። የፍቅር ማጣፈጫ ሆኖ ይቆጠራል። አይኔን በአይኔ አየሁ ደስታን ይፈጥራል። ይሄ ደግሞ ሌላ ዓለም ቤተሰቡን አጽንቶ የሚያቆይ አዲስ ምዕራፍ ይሆናል።

አርዓያ የሚሆን ቤተሰብ ከራሱ አልፎ ተርፎ ለተጋቢው ወገንም ልጅ ፣ ወንድም፣ እህት በአጠቃላይ ዘመድ አዝማድ በመሆን የሚተሳሰር እና የሚተሳሰብ ነው። እኔ ብቻ ልደመጥ፣ ልብለጥ የማይል ፣የሀሳብ ልዩነት ሲያጋጥም እንኳን ለማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ለመሸነፍ ዝግጁ የሆነ የቤተሰብ አካል ይሆናል። የሰላም መድረክም ነው ቤተሰብ። ሁሉንም ነገር የሚያይበት መነጽር ፍቅር ፣ርህራሄ በተሞላው ሁኔታ ነው። ልክ የሆነውን ለማስቀጠል ስህተት የሆነውን በማረምና በማስተካከል ነው ቤተሰብን የሚሰራው። ወላጆች እንደ አያቶቼ አላደጉም፣ እኛም እንደ ወላጆቻችን አላደግንም። ልጆቻችንም እንደኛ አያድጉም። በአጠቃላይ በዘመን ቅብብሎሽ ማህበረሰብ የሚገነባው ነው። ይሄ ትልቅ ተስፋ የተጣለበት የት ይደርሳል የተባለና ለብዙዎች አርአያ ሊሆን ይችላል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ቤተሰብ ባልተጠበቀ መልኩ ለችግር ሲዳረግ ይታያል። ካለ አንተ ካለአንቺ የተባባሉ የትዳር አጋሮች ጭራሽ የማይተዋወቁ ያክል ለከፋ ጉዳትና አደጋ የሚገባበዙበት ሁኔታ ይፈጠራል ። በአለት የተገነባ የሚመስለው ትዳርም ነፋስ እንደገባው የሳር ጎጆ በቀላሉ ይፈርሳል። የነበረው ፍቅር፣ የነበረው መተሳሰብና መከባበር ፣ የነበረው ሁሉ ነገር በዜሮ ተባዝቶ ህይወት እስከመጠፋፋት የደረሰ እርምጃ ውስጥ ይገባል።አስከፊ ወንጀል ተፈጸመ ሲባል ይሰማል።ይሄ እየተለመደ መጥቷል።

ዛሬ ስለ ቤተሰብ ላነሳ የወደድኩት በጤናዬ እንዳልሆነ ትረዱኛላችሁ።ከፍትህ ሚኒስትር ፌስ ቡክ ገፅ ያገኘሁትን እና በቤተሰብ መካከል ተፈጥሮ ወደ አልተገባ መንገድ ካመራው ግጭት ብንማርበት ብዬ ነው። የወንጀል ድርጊት በስሜት ይፈጸማል። ነገር ግን ሲቆይ ይጸጽታል። ያቺን ሰዓት ከስሜት ወጣ ብሎ ማሰብ ቢቻል፤ ለሚያጋጥሙ ችግሮች የተሻለ መፍትሄ መሳብ ቢቻል... አስከፊ የሚባለው ወንጀል ድርጊት ሁሉ አይኖርም ነበር።

### ቤተሰባዊ ትስስር

አቶ አሰፋ ለአቅመ አዳም ደርሰው በወግ ማእረግ ተድረው የልጅነት ሚስታቸውን ይዘው አዲስ አበባ ከከተሙ አንድ ክፍለ ዘመንን ሊደፈኑ ጥቂት ይቀራቸዋል። በልጅነት ወዛቸው ለፍተው ጥረው ግረው ባጠራቀሟት ጥሪት በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ልዩ ቦታው የካ ተራራ ትምህርት ቤት አካባቢ ሰፋ ያለ የመኖሪያ ቤትና ቅጥር ግቢ ሰርተው ከአምስት ልጆቻቸው ጋር በደስታ ይኖሩ ነበር።

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ልጆች አድገው ለወግ ማእረግ ሲበቁ አቶ አሰፋና የልጅነት ባለቤታቸው ደክመው በእድሜያቸው ማየት የሚገባቸውን ደስታ በሙሉ አይተው ይህችን አለም ይለያሉ። ወላጅ ሲሸኝ ልጅ በውርስ መተካት የነበረ ነውና የእናት የአባታቸው ቅርስ ላይ ልጆች ተተክተው በስርአት የድርሻቸውን ተካፍለው ወልደው ከብደው መኖር ይጀምራሉ።

ከአቶ አሰፋ አምስት ልጆች መካከል ሶስቱ በእናት በአባታቸው ቤት ሲኖሩ ሁለቱ ደግሞ የድርሻቸውን በኪራይ እየወሰዱ ከግቢው ውጪ ይኖሩ ነበር። ፍቅራቸው ወገን ዘመድ ጎረቤት የሚያስቀና በመከባበር የሚኖሩ ወንድሞችና እህትማማቾች ነበሩ።

በፍቅር መካከል ሳንካ አይጠፋምና በመካከል ወንድምና እህትማማቾች መካከል አልፎ አልፎ ግጭት ይታይ ጀመር። በማንኛውም ግጭት መካከል የአንደኛዋ ባል መካሪ ተቆጪ አስታራቂ ሆነ መካከላቸው በመግባት ነገሮቹ እንዲረግቡ የማድረግ ስራ ይሰራ ነበር።

### ስር እየሰደደ የመጣው ቁርሾ

ፀቡ ሲደጋገም፤ የዛሬው በይቅርታ ሲታለፍ ደግሞ ነገ ሌላ ጉዳይ ሲነሳ፤ እንዲሁ በቀላሉ ሲለባብስ የቀየው የቤተሰብ ፀብ ጭራሽ የትዳር አጋሮች መካከል አስገብቶ ያናጭ ጀመር። የእህትማማችና የወንድማማች ጉርብትና ከፍቅር አልፎ ለመገዳደል ወደ መፈላለግ ደረጃ ደረሰ። መዋደዳቸው መደጋገፋቸው ቀርቶ አይንህን ላፈር፤ አይንሽ ላፈር መባባል ጀመሩ። የአንድ አያት ልጆች የሆኑት ልጆቻቸውም ባልተገባው የቤተሰብ ፀብ የተነሳ አብረው መጫወት አቁመው ተኩራረፉ። የልጅነት ልባቸው ባይገባውም ቤተሰቦቻቸው መካከል ግን የከረረ ፀብ ስለመኖሩ ደመነፍሳቸው ነግሯቸዋል።

በፊት ሰላምን ቅድሚያ አማራጭ ያደረጉት በሙሉ እልህ ተጋቡ። ቆም ብሎ በማሰብ ያለባቸውን ችግር ከመፍታት ይልቅ ነፍስ ለመጠፋፋት ማሰብ ማሰላሰል ባገኙት አጋጣሚ ደግሞ መዛዛትና ጥርስ መነካከስ ጀመሩ። በተለይም አቶ ሙሉነህ አሰፋ የተባለው ወንድማቸው የእህቱን የወይዘሮ አልማዝ አሰፋን ባለቤት አቶ አበበ ለብሶን መካከላችን የገባ ጋሬጣ በማለት በክፉ አይኑ ይመለከተው ጀመር።

በክፉ አይን ከመተያየትም አልፎ መዛትና ማስፈራራትም እየተከተለ መጣ። ፀቡ ከእለት ወደ እለት እየከረረ መጥቶ አቶ ሙሉነህ አቶ አበበን እገልሃለው ብሎ ሲዝትበት ይውላል። ይህ ተደጋጋሚ ዛቻ ስጋት ውስጥ የከተተው አቶ አበበ ለክፉም ለደጉም በማለት ፖሊስ ጣቢያ አመልክቶ ሲመለስ ያልታሰበ ዱብዳ ይወርድበታል።

### ያልታሰበው ቅጥፈት

አቶ አበበ ለብሶ ለክፉም ለደጉም ህግ ያወቀው ነገር ይሻላል በማለት ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ ስለጉዳዩ አብራርተው ስጋታቸውን አስመዝግበው ወደ ቤት ይመለሳሉ። ገና ከቤት ሲወጡ የት እንደሚሄድ ተከተለህ እየው የተባለው የአቶ ሙሉነህ ልጅ የአክስቱ ባል ፖሊስ ጣቢያ መሄዳቸውን ተከታትሎ በማየት ለአባቱ መጥቶ ይነግራል። ይሄኔ እንዴት ተደፈርኩ ያለው አቶ ሙሉነህ በመደንፋት ቤት የደበቀውን ሽጉጥ ይዞ ሲወጣ ሁለቱ እህቶቹ ይከተሉታል። ደጅ ቆሞ የእህቱን ባል የሚጠባበቀው አቶ ሙሉነህ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ እየደነፋ አካባቢውን ያውካል።

ሀገር ሰላም ብለው ከፖሊስ ጣቢያ ወደ ቤታቸው የሚመለሱት አቶ አበበ ደጅ ሰብሰብ ብለው የቆሙትን ባለቤታቸውንና ወንድም እህቶቻቸውን በአይናቸው ገረፍ በማድረግ ወደ ቤታቸው ሊገቡ ሲሉ። " አንተ ማን አባክ ስለሆንክ ነው ፖሊስ ጣቢያ ሄደህ የምትከሰኝ፤ ከእንግዲህ በኋላ እዚህ ቤት መኖር አይደለም በህይወት አትቆይም...." በማለት የያዘውን ሽጉጥ ወደ አቶ አበበ ያነጣጥራል።

በድንጋጤ መካከል የገቡት እህትማማቾችን "ዞር በሉ ሰበብ እንዳትሆኑብኝ.." በማለት ቢጠይቃቸውም እህቶቹ ግን በእንባ መማፀንን ምርጫቸው አድርገው ወንድማቸውን ይለምኑት ጀመር። ምንም ጉዳት አያደርስበንም ብለው እግሩ ስር የተደፉትን እህቶች በትእግስት ማጣትና ንዴት አቅሉን የሳተው አቶ ሙሉነህ በየተራ አቁስሎ ጠላቴ ወዳለው የእህቱ ባል ፊቱን አዞረ።

ከፉከራ ባለፈ ጨክኖ ይሰነዝራል ብለው ያልጠበቁት አቶ አበበ እህቶቹ ላይ ያደረገውን ነገር ሲመለከቱ ለማምለጥ ሙከራ አደረጉ። ፊታቸውን አዞረው ከድንጋጤ የተረፈ ጉልበታቸውን አጠረቃቅመው እግሬ አውጪኝ ብለው ሊሮጡ ቢሞክሩም አንዴ በደም የሰከረው አቶ አበበ እጁን ሳያጥፍ ደጋግሞ በተኮሰው ጥይት የተነሳ እስከ ወዲያኛው አሸለቡ።

" የገደለው ወንድምሽ የሞተውም ባልሽ፤ ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ" ይሉት ነገር የደረሰባት ሴት በዚህ ከወንድሟ በተሰነዘረው ጥይት ደሟን እያዘራች በዛ የልጇ አባትን ሞት ሊያውም በወንድሟ ስለመገደሉ ባለማመን ስሜት ውስጥ ሆና ራሷን ሳተች።

በአካባቢው ነዋሪዎች የድረሱልኝ ጥሪ በቦታው የተገኘው ፖሊስ የቆሰሉትንና አስከሬኑን ወደ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል በመላክ ተጠርጣሪውን ይዞ ወደ ህግ ቦታ አመራ።

### የፖሊስ ምርመራ

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው ፖሊስ ተጠርጣሪውን ይዞ በህግ ጥላ ስር ካቆየ በኋላ ሆስፒታል ወደ ተኙት እህትማማቾች በመሄድ ቃላቸውን ይቀበላል። ከዚህም በተጨማሪ የአካባቢውን ነዋሪዎች የአይን ምስክሮችን አንድ በአንድ በመጠየቅ መረጃውን ያጠናቅራል። ወንጀሉም ሆን ብሎ በቂም በቀል ተነሳስቶ የተፈፀመ መሆኑን ከደረሰበት በኋላ ዐቃቤ ህግ ክስ እንዲመሰርት ያደርጋል።

የዐቃቤ ህግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ሙሉነህ አሰፋ በ4 ክሶች የተከሰሰ ሲሆን ታህሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 10፡40 ሰዓት ሲሆን በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ልዩ ቦታው የካ ተራራ ትምህርት ቤት አካባቢ የቤት ቦታን አስመልክቶ ከሟች አበበ ለብሶን ጋር በነበረ ፀብ ተከሳሹ እገልሃለው ብሎ ሲዝትበት ሟች ፖሊስ ጣቢያ አመልክቶ ሲመለስ አስቀድሞ በመዘጋጀት በሽጉጥ ተኩሶ ትከሻውን በመምታት ሲገድለው በስፍራው የነበሩ አልማዝ አሰፋ እና አዲስ አሰፋን ተኩሶ ጉዳት ያደረሰባቸው በመሆኑ በፈፀመው ከባድ የሰው ግድያ እና የመግደል ሙከራ ወንጀል 3 ተደራራቢ ክሶች ቀርበውታል።

እንዲሁም ተከሳሽ ወንጀሉን የፈጸመበት ሽጉጥ የፀና ፈቃድ ያልነበረው በመሆኑ የጸና ፈቃድ ሳይኖር የጦር መሳሪያ መያዝ እና መገልገል ወንጀል ሌላ ተጨማሪ ክስ የቀረበበት በመሆኑ በአጠቃላይ በ4 የወንጀል ክስ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ቀርቦ ክርክር ሲያደርግ ቆይቷል።

ግራ ቀኙን ያደመጠው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 1ኛ ሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎትም ወሳኔ ለማሳለፍ ህዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም ቀጠሮ ይሰጣል።

### ውሳኔ

በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው መግደል ወንጀል ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት የቀረበው ተከሳሽ ድርጊቱን አልፈፀምኩም በሚል የእምነት ክህደት ቃላቸውን የሰጡ በመሆኑ፤ ዐቃቤ ህግ ያሰባሰባቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በማቅረብ ተከራክሯል።

ምንም እንኳን ተከሳሽ ወንጀሉን አልፈፀምኩም እያለ ሲከራከር ቢቆይም ዐቃቤ ህግ ክሱን በማስረጃ በበቂ ሁኔታ ያስረዳ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ህዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሹ ዐቃቤ ህግ ባቀረባቸው 4 ክሶች ጥፋተኛ እንደሆነ ተረጋግጦ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ 2/2006 እርከን 38 ስር መነሻ ቅጣት በመያዝ የቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሆኑ 1 ማቅለያ ተይዞለት በእርከን 37 ስር በማሳረፍ ተከሳሽን ያርማል ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ያስተምራል ያለውን በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተከሳሽ በሁሉም መብቶቹ ለዘወትር እንዲሻር ሲል ወስኖበታል፡፡

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ትራንስፖርት ላይ የሚፈፀመው የሴቶች ፆታዊ ትንኮሳ

በስጥሻቸው ልዑልሰገድ

መዲናችን አዲስ አበባ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ሁሉን አቻችላ በእቅፏ የያዘች ከተማ ናት። ነዋሪዎቿም እንደየኑሮ ደረጃቸው ሰርተው ለማደር ከጠዋት እስከ ማታ ደፋ ቀና ይላሉ።

ያለው ባለው ላይ ለመጨመር የሌለው ደግሞ ካለበት የኑሮ ደረጃ ወደተሻለው ከፍ ለማለት፤ ከዛ ባስ ያለው ደግሞ የለት ጉርሱን ለማግኘት ይታትራል። በዚህ ሁሉ መሃል ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ፣ ከቤት ወደ ስራ ከስራ ወደ ቤት የሚንቀሳቀሰው ሕዝብ የተለያዩ የትራንስፖርት አማራጮችን እንደየ አቅሙ ይጠቀማል።

አብዛኛው የከተማዋ ነዋሪ የህዝብ ትራንስፖርት በተለይም የከተማ አውቶብስ ተጠቃሚ ነው። ለዚህ የተለያዩ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የከተማ አውቶብሶች በሮቻቸውን ለመዝጋት እስከሚቸገሩ ድረስ በሰው ታጭቀው ከማየት የበለጠ ማረጋገጫ የለም።

የከተማ አውቶብሶች የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚው ሕዝብ እጅግ ብዙ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ለማንም ምቾት የሚሰጥ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በተለይ ለሴቶች ደግሞ ምቾት ከማሳጣት ባሻገር ሌላም ጣጣ እንዳለው አዲስ አይደለም። በከተማ አውቶብሶች የሚጠቀሙ ሴቶች በወንዶች ፆታዊ ትንኮሳ እንደሚደርስባቸው የሴቶች መብት ተሟጋቾች በተለያየ ጊዜ እየጠቆሙ ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠው ለማድረግ ጥረት አድርገዋል። ይህ ጥረታቸው ግን አሁንም ድረስ በህግ ተደግፎ ሴቶች በሕዝብ ትራንስፖርት ላይ የሚገጥማቸውን የሞራልና የመብት ጥሰት ማስቀረት አልቻለም። ጉዳዩ በመብት ተሟጋቾችም በሌሎችም በአንድ ወቅት አጀንዳ ሆኖ ይነሳና ብዙም ሳይቆይ ይረሳል። እኔም በዚሁ ጉዳይ ላይ የታዘብኩትን ላካፍላችሁ ብእሬን ያነሳሁት ድንገት ነው።

ከእለታት ባንዱ ቀን ነው፣ እግር ጥሎኝ የከተማ አውቶብሶች ብዙ ተሳፋሪ በማያጨናንቃቸው ሰዐት ተሳፍሬ ወደ ጉዳዬ እየሄድኩ በነበርኩበት ጊዜ አውቶብሱ ውስጥ ተለጥፎ ያየሁት ጽሁፍ ቀልቤን ሳበው። ጽሁፉ «የህዝብ ትራንስፖርት ውስጥ ሴቶች ላይ የሚፈጸም ጾታዊ ትንኮሳን በጋራ እንከላከል » ይላል። ይህንን ፅሁፍ ካነበብኩ በኋላ ከራሴ ጋር በብዙ አወራሁ። እንዴት? የሚል ጥያቄ ውስጤ ተመላለሰ።

እንዴት ይሄ ጉዳይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ በገሃድ ያውም በጽሁፍ እስኪነገር ድረስ ከሰውነት ወረድን? ባህል፣ወግና እሴቶቻችን ምን ያህል ቢናዱ ነው ይህን ያህል የሞራል ዝቅጠት ውስጥ የገባነው? ብዬ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ። በእርግጥ ይህ ጉዳይ እንደ ከተማ አውቶብስ ባሉና በርካታ ሰው በሚጠቀምባቸው የትራንስፖርት አገልግሎቶች ላይ እንደሚፈጠር ሰምቼ ባውቅም በተለያዩ ምክንያቶች የህዝብ ትራንስፖርት ከተጠቀምኩ ቆይቼ ነበርና በዚህ ልክ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ይደርሳል ብዬ አልገመትኩም ነበር። በተሳፈርኩበት አውቶብስ ውስጥ ያነበብኩት ጽሁፍ ግን ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቼ እንዳስበው አደረገኝና በዙሪያዬ የማገኛቸውን ሴት ጓደኞቼን እና በተለያየ አጋጣሚ የማገኛቸውን ሴቶች ስለነገሩ እንድጠይቅ አድርጎኛል።

ጉዳዩ በዚህ ልክ አሳሳቢ መሆኑን ለመረዳት ዘወትር የአውቶብሶቹን አገልግሎት የሚጠቀሙ ሴቶች የነገሩኝን ጉድ ስሰማ ነው የገባኝ። ታዲያ የሰው ልጅ ያውም ጥብቅ ባህልና ወግ ባለበት አገር በዚህ ልክ ሰው ከሰውነቱ ወርዶ ከተገኘ ከእንስሳት የሚለይበትን የማሰብ ፀጋ ተነፍጓል ማለት አይደል?

ከጊዜ በኋላ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ በተደጋጋሚ አውቶብሶችን መጠቀም ሳዘወትር በዚህ ጉዳይ መናደድ ጀመርኩ ብል ይቀላል። ያቺን ጽሁፍ ካነበብኩበት ቀን አንስቶ የአውቶብስ ትራንስፖርት ስጠቀም ነገሩን በትኩረት መከታተል ጀምሬያለሁ። የህዝብ ትራንስፖርት የሚሰጡ የከተማ አውቶቢሶች ወንበሮቻቸው በሰዎች ከሞሉ በኋላ ቆመው የሚሄዱ ተሳፋሪዎችን ካፍ እስከ ገደፋቸው ጢም አድርገው መጫናቸው የተለመደ ነው።

ተሳፋሪው ከትራንስፖርት ችግሩ አኳያ ምቾቱን ወደ ጎን ትቶ ታምቆ ጉዞውን ሲጀምር አንዳንድ ስነምግባርም ሞራልም የጎደላቸው ወንዶች የአውቶብሱን በሰው መጨናነቅ እንደሰበብ ተጠቅመው ቆመው ወደሚጓዙ ሴት ተሳፋሪዎች በመጠጋት የወሲብ ትንኮሳ ለመፈጸም ይሞክራሉ። ይህን ለማድረግ ስራዬ ብለው አውቶብሶችን የሚሳፈሩ አሉ። ምቹ ሁኔታዎችን አይተው ሙከራ ለማድረግ የሚጥሩም ጥቂት አይደሉም።

እንዲህ አይነቱን ፀያፍ ድርጊት የሚፈጽሙ ወንዶች መጀመሪያ በቦታ ጥበት አሳበው ሴቶችን ይጠጋሉ። በሰዎች ታጭቆ መፈናፈኛ የሌለው አውቶብስ ውስጥ ብዙ ሴቶች ይህ ትንኮሳ እየተደረገባቸው መሆኑን እያወቁ እንኳን ራሳቸውን ለመከላከል አማራጭ የሚያጡበት ጊዜ አለ። በዚህም ምቾት በማጣት ፊታቸው ላይ የመጨነቅ ስሜት ይነበባል። በዚህ የተነሳ ብዙ ሴቶች መሄድ የሚፈልጉበት ቦታ ሳይደርሱ እስከመውረድ ይገደዳሉ።

ብዙ ሴቶች እንዲህ አይነቱ ነውር ሲፈፀምባቸው ዝምታን መርጠው የራሳቸውን ርምጃ ይወስዳሉ እንጂ የወንዱን ፀያፍ ድርጊት እዚያው ሰው በተሰበሰበበት አውጥተው አይናገሩም። ያው ጉዳዩ አሳፋሪና ከባህላችንም አንፃር ይህ ነው የሚሉት ባለመሆኑ ነው። በራሳቸውም ይሁን በሌሎች ላይ ይህን ነውር የሚፈፅሙ ወንዶችን እየተመለከቱ ዝምታን የማይመርጡ አንዳንድ አንጀት አርስ ሴቶች አሉ። ይህን ድርጊት ለመፈፀም የሚሞክረውን ሰው አደባባይ ላይ አውጥተው በማጋለጥ ከፍና ዝቅ አድርገው ተናግረው በጋራ ሲያዋርዱትና ያለቦታው ከመድረሻው ፌርማታ ሳይደርስ እንዲወርድ የሚያደርጉ።

የሰውየው ግዝፈት የሰው ብዛት ሳያስፈራት ምቾቷን የነሳትን ሰው ትግስቷ አልቆ ዞራ በጥፊ ፊቱን የምታቀላውም አለች። አቤት ከዚያ በኋላ የሰውየውን ፊት ማየት ነው። መሬት ተሰንጥቃ ብትውጠው እየተመኘ እንደሆነ በሚያሳብቅ ሁኔታ አንገቱን ደፍቶ አውቶብሱ ውስጥ ካሉ ሌሎች ጨዋ ወንዶችና ሴቶች የሚወርድበትን ቁጣ አምልጦ የሚገባበት ጠፍቶት ተገትሮ ይቀራል። እንዲህ አይነቱ ከመድረሻው ቢደርስም ባይደርስም አንገቱን እንደደፋ ይወርዳል። እዚህ ጋር ለሴት ልጅ ትንኮሳ ተቃዋሚ ሆነው እንዴት ብለው የሚቆጡ ወንዶችን ማመስገን አስፈላጊ ነው።

ሴቶች ጊዜ ተለውጦ እንደማንኛውም ሰው ኑሯቸውን ለማሸነፍ ከቤት ወጥተው ሰርተው መግባት በጀመሩበት በዚህ ጊዜ ሌላ እንቅፋት እንዳይገጥማቸው የማድረግ ሃላፊነት የሁሉም ነው። ይህን ጉዳይ ቀለል አድርገን ልንመለከተውም አይገባም። ሴቶች እንደማንኛውም ሰው ደህንነታቸው ተጠብቆ ወጥተው በሰላም እንዲገቡ ይህ ጉዳይ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ የአንድ ሰሞን ብቻ አጀንዳ መሆን የለበትም።

# ዓለም አቀፍ

## አዲሱ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኔታንያሁ “አዲስ ጥምር መንግስት መስርቻለሁ” አሉ

አዲሱ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ባለፈው ወር በተካሄደው ምርጫ የሊኩድ ፓርቲ እና አጋሮቻቸው አብላጫ ድምጽ ካገኙ በኋላ አዲስ መንግስት መመስረታቸውን ተናግረዋል።እስራኤላውያን በአራት ዓመታት ውስጥ ለአምስተኛ ጊዜ በፈረንጆቹ ህዳር 1 ቀን 2022 ምርጫ አካሂደዋል። የኔታኒያሁ ጥምረት 120 አባላት ካሉት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ 64 መቀመጫዎችን አሸንፏል።

ኔታንያሁ በትዊተር ገጻቸው “ባለፈው ምርጫ ለተደረገልን ከፍተኛ የህዝብ ድጋፍ ምስጋና ይግባውና ለሁሉም የእስራኤል ዜጎች የሚጠቅም መንግስት ማቋቋም ችያለሁ” ብለዋል።በፈረንጆቹ ጥር 2021 በሙስና ምርመራ ከስልጣን ከመባረራቸው በፊት ኔታኒያሁ ለ15 ዓመታት የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው አገልግለዋል።

አዲሱን መንግስት ለመመስረት ከቀኝ አክራሪ አጋሮች ጋር ለሳምንታት ተደራድረዋል ነው የተባለው።የኔታንያሁ የካቢኔ አባላት የደህንነት ሚኒስትር ሆነው የሚሾሙትንና የብሔራዊ ፖሊስ ኃይልን የሚመሩን ኢታማር ቤን-ጊቪርን ይጨምራል ሲል ፎክስ ኒውስ ዘግቧል።

የፋይናንስ ሚንስትር ሆነው የሚያገለግሉት የዌስት ባንክ ሰፈራ መሪ የነበሩት ቤዛል ስሞትሪክ ናቸው የተባለ ሲሆን፤ አቪ ማኦዝ የእስራኤልን የትምህርት ስርዓት ይመራሉ ተብሏል።በኢራን ስምምነት እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ከኔታንያሁ ጋር ከፍተኛ ልዩነት ያለው የባይደን አስተዳደር ከአዲሱ መንግስት ጋር በቅርበት ለመስራት ቃል ገብቷል።የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር አንቶኒ ብሊንከን በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ “መንግስትን ከግለሰባዊ ስብዕናዎች ይልቅ በሚከተላቸው ፖሊሲዎች እንለካለን።

ባለፉት ሰባት አስርት ዓመታት ውስጥ በግንኙነታችን ውስጥ ካስቀመጥነው የጋራ መመዘኛዎች ጋር እናያለን” ሲሉ ስለ እስራኤል አዲስ መንግስት ተናግረዋል።የኔታኒያሁ ሊኩድ ፓርቲ እና አጋሮቹ በህዳሩ ምርጫ ከፓርላማው 120 መቀመጫዎች 64ቱን መያዛቸውን አል ዐይን ዘግቧል፡፡



## በአፍሪካ ቀንድ ድርቅ ከ20 ሚሊዮን በላይ ህጻናትን ለከፋ ችግር ዳርጓል

በምስራቅ አፍሪካ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ለከፍ ችግር የተጋለጡ ህጻናት ቁጥር በአምስት ወራት ውስጥ ከእጥፍ በላይ መጨመሩ የተባበሩት መንግሥት የህጻናት አደን ድርጅት ዩኒሴፍ ትናንት ባወጣው መግለጫ አስታውቋል።

በአየር ንብረት ለውጥ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የዋጋ ግሽበት፣ በግጭትና በእህል ምርት እጥረት ምክንያት ለከፉ ርሃብና ውሃ ጥም እንዲሁም ለበሽታ የመጋለጥ ስጋት ያለባቸው ህጻት ባለፈው ሃምሌ ወር ከነበረበት 10 ሚሊዮን ወደ 20 ነጥብ 2 ሚሊዮን አሻቅቧል።

የዩኒሴፍ የምስራቅ እና ደቡብ አፍሪካ ምክትል ኃላፊ ሊኬ ቫን ዴዊሊ በጉዳዩ ላይ በሰጡት አስተያየት ድርቁ ያስከተለውን ችግር ለመቅርፍ የሚደረገው ጥረት ዝቅተኛ በመሆኑ በምስራቅ አፍሪካ አስከፊ ድርቅ ከሁለት ትውልዶች በላይ ዘልቋል ብለዋል።

“በርሃብ እና በሽታ ምክንያት ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣው እና ወደ ሞት ጠርዝ እየተገፉ፤ ምግብ፣ ውሃ እና ለከብቶቻቸው የግጦሽ ሳር ፍለጋ እየተሰደዱ ያሉ ሕጻናትንና ቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመታደግ እና ችግሮችን የመቋቋም አቅማቸወን ለማጠናከር



የሰብዓዊ እርዳታ ተደራሽነት ሊቀጥል ይገባዋል” ሲሉም አብራርተዋል።

የምስራቅ አፍሪካ አገራት ወደ 2 ሚሊዮን የሚጠጉ ሕጻናት በከፍ የተመጣጠነ የምግብ እጥረት ስላጋጠማቸው አስቸኳይ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናልም ብሏል ዩኒሴፍ።በተጨማሪም ቤተሰቦች ድርቁ እየፈጠረባቸው ባለው ጫና ምክንያት የሚደርግላቸው ጥበቃ አደጋ ላይ ወድቋል። ይህም የጉልበት ብዝበዛ፣ የህጻናት ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን ከፍ እንዲል አድርጓል።

በሌላ በኩል ጾታዊ ጥቃትና ብዝበዛ ጨምሮ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ እና መፈናቀሉ እንዳባባሰው ዩኒሴፍ ጠቁሟል።ዩኒሴፍ አጋሮቹና ለጋሾች በሚያደርጉለት ድጋፍ በአፍሪካ ቀንድ ሕይወት አድን የሆኑ አገልግሎቶችን እያቀረበ እንደሆነም አመላክቷል።

ድርጅቱ ለቀጣዩ የፈረንጆች ዓመት ለህይወት አድን ስራዎች እና ለሌሎች ተግባራት 759 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልገኛል ያለ ሲሆን ተጨማሪ 690 ሚሊዮን ዶላር ደግሞ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘና ሌሎች ዘላቂ ተግባራትን ለመከወን እንደሚያስፈልግ አመላክቷል።

ኃላፊዋ በምስራቅ አፍሪካ ያለውን ድርቅ እና ያስከተለውን ችግር ለመፍታት መንግስታት ድጋፍ እንዲያደርጉ የጠየቁ ሲሆን “በአፍሪካ ቀንድ ህጻናት ላይ ሌላ አስከፊ እና የማይቀለበስ ጥፋትን ለመቀነስ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብን ድጋፍ እንፈልጋለን። የህጻናትን ህይወት ለመታደግ፣ ክብራቸውን ለመጠበቅ እና መጻኢ እድላቸውን ለመጠበቅ አሁኑኑ እርምጃ ልንወስድ ይገባል” ሲል የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

# ከፍልስፍናችን ማንነት ግብአተመሬት በፊት

ግርማ መንግሥቴ

ይህ፣ ዛሬ በድንገት ለንባብ የበቃው ሀሳብ ከዚህ በፊት "ፍልስፍና ማለት" በሚል ርእስ ይፃፍበት ዘንድ ተረግዞ የነበረ ሲሆን፣ ሁሉም ያለ ጊዜው አይሆንምና ዛሬ ያ ሃሳብ በሚከተለው መልኩ ለንባብ ሊቀርብ ችሏልና "እነሆ በረከት ..." እንላለን።

እንደሚታወቀው፣ ብዙ ጊዜ በየዋህያን ዘንድ "ፍልስፍና ማለት"ን ከመጠየቅ ጋር ብቻ አያይዞ፤ ከመመለስ ጋር እንኳን ሳይገናኝ መጠየቅ ብቻም ሆኖ ምእተ አመታትን ዘልቆ፣ እዚህ እኛ ዘንድ ደርሷል። "ልክ ነው"፣ "ልክ አይደለም . . ." የሚለውን እየወረድን የምናየው ሆኖ፤ ሁሉም ግን በራሱ፣ ለየ እራሱ የሚለውን ለራሱ ሊይዘው ይገባልና ማንም ቢሆን ከጫና ሊያመልጥ የግድ ይሆናል። ጉዳዩን መሬት ለማሲያዝ ግን መነሻችንን እራሳችንን፤ ሌጋሲዎቻችንንም ፈላስፎቻችንን አድርገን ፈር እንያዝ። (እዚህ ላይ፣ ጉዳዩ "ፍልስፍና ማለት"ን ለመመለስ ከሞከረው፣ ከመጀመሪያው ፈላስፋ Thales (Raymond Geuss በበኩሉ Oedipus ነው ይላል) ጀምሮ የትኩረት ነጥብ ሲሆን፤ ወደ ፊት ስለመዝለቁም ጥርጥር የሌለ መሆኑን፤ ለዚህ ደግሞ ቀዳሚው ምክንያት አለም እንደ ወንዝ መሆኗና የሰማው ሲሄድ ያልሰማው መምጣቱ መሆኑን በመሰረታዊነት ልንይዘው ይገባል።)

የፍልስፍናን ፋይዳ ምን ያህል እናውቀዋለን? ካወቅነውስ አሳውቀናል? ነው ወይስ ዛሬም ድረስ "ፍልስፍና ማለት መጠየቅ ማለት ነው" እያልን ከሰው ልጅ የእለት ተእለት ሕይወት አርቀነዋል? ፈላስፋውንስ ቢሆን።?

ሲጀመር፣ ፈላስፋው እኮ ሀሳቡን ገለፀ፤ ይሆናል፣ ይበጃል . . . ያለውን እንካችሁ አለ እንጂ አነሳሱ ልፈላሰፍ የሚል (ብሎ) አይደለም። የፈላስፋነቱን ማእረግ ያገኘው ስራውን ከሰራው በኋላና በሚመለከታቸው ተመዝኖ ነው ባለ ስራው "ፈላስፋ" የሚባለውን ካባ የሚደርበውና የፈላስፋነቱን ደብር የሚቆጣጠረው። ፀጋዬ እኮ ከስራው በኋላ እንጂ ከስራው በፊት አይደለም ማህበራዊ አንቱታውን በእጁ ያስገባው። ገብረህይወት ባይከዳኝ፣ ሀዲስ አለማየሁ፣ በአሉ ግርማ፣ ከበደ ሚካኤል . . . ሁሉ እኮ እውቅናቸውን ያገኙትና ማህበረሰባዊ ከበሬታን የተቆጣጠሩት ስራዎቻቸውን መሬት ካወረዱና ፍሬያቸው ከተቀመሰ በኋላ ነው። ዘርአያእቆብ እኮ ሲፈላሰፍ "ፍልስፍና" የሚለው ቃሉም አልነበረም። እሱ ሲያከናውን የነበረው የነፍሱን ጥሪ ነበር። ማርክስም ለተጠየቀው ሲመልስ "እኔ ማርክስ እንጂ ማርክሲስት አይደለሁም" ነበር ያለው።

ዛሬም እንጉርጉሯችን "ፍልስፍና ማለት መጠየቅ ማለት ነው" ከሆነ፣ የፍሬሽ አፍ መፍቻ ቦታው የቱ ጋ ነው? ነው ወይስ ዘርዓያዕቆብ ስላነሳቸው ብርቱ ጉዳዮች ጠየቀ እንጂ አላብራራም፤ አልተነተነም፤ አልተነበየም፤ እውነቱን አላመለከተም፤ መሆን ያለበትን ከሌለበት አልለየም ወዘተ (ለ)ማለት ነው? ነፍሳቸውን ይማረውና አማረ ማሞ እንዳሉት ጉዳዩ - ያወያያል፤ ያነጋግራል፤ ያመራምራል።

"ፍልስፍና በጥቅሉ የተጻፉትንና በቃል ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉትን የጋርዮሽ የማህበረሰብ ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች፣ ወጎች፣ ልማዶች፣ እደ-ጥበቦች፣ የእውቀት ዘርፎቻችንና አስተሳሰቦችን፤ በጠባቡ አተያይ ደግሞ በግለሰብ ፈላስፎች በአንድ ዘመን ተሰርተው በጽሁፍ የተላለፉትን ስራዎች በጥቅል የሚመለከት ነው፡፡" የሚለው ብያኔ በብዙዎች ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን ሌሎች ብያኔዎችን በዚሁ ጽሑፍ ሂደት በእግረ መንገድ ተነካክተዋል።

ወደ ጉዳያችን ስንገባ (ሳንገባም ቢሆን) ከጥንቱ፣ ከግዕዝ ስልጣኔያችን (የዓባይንም አክለን) በመጀመር ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር፤ "መጀመሪያ ቃል ነበረ(ር?)" ተብሏልና እኛም "መጀመሪያ ግዕዝ ነበረ" ብንል "አልነበረም" የሚለን ስለማይኖር ማለት ነው። ከጊዜና ገጽ አኳያ ግን ከፍልስፍናና ፈላስፎቻችን እንጀምር።

ስለ"የኢትዮጵያ የፍልስፍና አባት ዘርዓያዕቆብ" ከመናገራችን አስቀድሞም ይሁን ቀድሞ፤ "የኢትዮጵያ የሥነጽሁፍ ታሪክ በአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግስት (1434-68)" ከሚል ነገራ በፊትም ሆነ በኋላ፤ ስለተለያዩ የፍልስፍና መጻሕፍት ከመናገራችን ሁሉ በፊትም ሆነ በኋላ፤ ስለ"ያሬዳዊ ዜማ" ከመተንተናችን በፊትም ሆነ በኋላ፤ ስለ"የዶርዜ ጥበብ" እና "ባህላዊ አልባሳቶቻችን" ከመደስኮራችን አስቀድሞ፤ የአክሱም ሀውልት ላይ ያሉትን ፈርጦች ማየታችንን ከማሳየታችን በፊት፤ ወይም በኩራት ከመናገራችን በፊት "ስለምን"አቸውን አጠይቀናል?

"በሎሬቱ አማካኝነት የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ ጨረቃ ላይ ወጥቷል" ስንል "በየትኛው የአሳሳል ፍልስፍና መሰረትነት?" የሚል ጥያቄ ቢኖር መልሱ ምን እንደሚሆን/ማይሆን ማን/ምን ያውቃል? የ"ትልልቅ ዐይን"ን ጥበባዊ መሰረት፣ ፍልስፍናዊ ክዋኔ ምንነት ለመግለፅ ከመሞከራችን በፊትም ይሁን ከሞከርን በኋላ "ኢትዮጵያ የ'ትልልቅ ዐይኖች' አሳሳል ጥበብ ባለቤት" ፍልስፍናችን የቱ ጋ እንኳን እንዳለ ሳንናገር፤ በ"አብስትራክት" የተተበተብን የተበላሹ አብስትራክቶች ሆነናል/አልሆንንም - ምርጫው የግል ሆኖ። (የሀበሻ ቢራ አርማን እንጥቀስ ካልተባለ በቀር።)

"ወግና ስርዓት፣ ነውርና ክብር ስለክፉትና ደግነት፣ ጥሩነትና መጥፎነት፣ እንዲሁም ስለሥነምግባር ጽንሰ ሃሳቦች ትክክለኝነትና ስህተትነት ምንነት፣ መስፈርትና አስፈላጊነት የመሳሰሉትን ሃሳቦች የሚያጠና ዓቢይ የፍልስፍና ዘውግ (ወይም ዖታ) ምን ይባላል?"ን ከመጠየቃችንም ሆነ አለመጠየቃችን፤ "ሥነ-ምግባር (Ethics)" "ነው" ወይም "አይደለም" ብለን ከመመለሳችንም ሆነ መመለስ ካለመቻላችን በፊት "ፍልስፍና ማለት" ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ አይገባንም/ይገባናል የሚለው እራሱ መመለስ አለበት/የለበትም ላይ ልንግባባ እየተገባም ይሁን እያልተገባ ይህን ሳናደርግ ዛሬ ድረስ መዝለቃችን ስህተተኞች መሆን/አለመሆናችን ላይ እራሱ እራሱን የቻለ (የመግባባያ ሰነድ የማያስፈልገው) መስማማት ወይም አለመስማማትን ይጠይቃልና እዳው ገብስ የሆነ ይመስል ልናቀ'ለው አይገባም።

ይህ "ፍልስፍና ማለት መጠየቅ ነው" አተያይ መረዳትን ሁሉ እስኪከልል ድረስ ስር ሰዷል (ይህ ደግሞ So obviously, attempting to sum it up in a few pithy blurbs is a fool's errand. ይሉት አይነት ነውና ፋይዳው ከዜሮ በታች ነው)። በመሆኑም - ሥነግጥም ከግጥምነት ያለፈ ፋይዳ የለውም፤ ልቦለድም ሆነ ሌሎች የፈጠራ ስራዎችም እንደዛው። ባህላዊ እሴቶቻችንና ታሪኮቻችን የፍልስፍናዎቻችን መገለጫዎች መሆናቸውን ልብ እንዳንልና የውጪውን እንድንጎመዥ አድርጎናል። የፈጠራ ሰዎችንና ስራዎቻቸውን ከተራው ሰው ለይተን ተገቢውን ስፍራ ሰጥተን "አንቱ" እንዳንል ጋርዶናል። በመሆኑም ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን በቃ ገጣሚ እንጂ ሌላ አይደለም፤ በ"እሳት"፣ "ውኳ" እና "ዋርካ" ላይ ያለው አመለካከት፣ በስራዎቹ ውስጥ ያሏቸው ስፍራዎችና ፋይዳቸው ለእኛ ምንም እንዲሆኑ አስተዋፅኦ አደረገ እንጂ ስራዎቹ የባለቅኔው ፍልስፍና ማራመጃዎች መሆናቸውን እንዳንለይ አድርጎናል - "... መጠየቅ ነው" መባሉ። ይህም በበኩሉ ስለ'ነዚህ የፍልስፍና ማሄጃዎቹ እስካሁን እሱ ከነገረምን ውጪ ሌላ ተጨማሪ የሰማነው ነገር የለም፤ በታትኖ የሚያሳየን ሥነጽሑፋዊ ሂስም ሆነ ሀያሲ አላየንም፤ አላገኘንም። "ጃንሆይ ፍቅር እስከ መቃብርን ልቦለድ ነው ብለው ባይንቁት ኖሮ የደረሰባቸው አይደርስባቸውን ነበር።" የሚባለውንም ከዚሁ አኳያ መረዳት እየተነጋገርንበት ያለነውን ከማቅለል ባሻገር ጉዳት የለውም።

ለነገሩ፣ የሂስና ሃያሲያን መንደር ጭር ካለ ቆይቷል። እንደው ጭራሹኑ ባዳ እንዳይሆንብ አድርገውት ከነበሩት አንዱ ነፍሱን ይማረውና አብደላ እዝራ ነበር። አስፋው ዳምጤም ሰሚ አጥተው የተሰላቹ ይመስላሉ - ጠፍተዋል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በ"የጋን ውስጥ መብራት"ነታቸው ፅንተው ንክች ያባ ቢላዎ ልጅ በማለት ቃለ መሀላ የፈፀሙ እስኪመስልባቸው ድረስ ትንፍሽ ሲሉ አይሰሙም። ታዲያ ሥነፅሁፍ ለፍልስፍና እያደረገ ያለው አስተዋፅኦ እንዴት ይታወቅ? ይህ ብቻም አይደለም ስንትና ስንት ዋልጌ ብእሮች አገር ምድሩን ሲያጥለቀልቁት ሀይ ባይ ሁሉ እስኪጠፋ ድረስ ቦታው ለምን ባዶ ሆነ? እኛንስ ለምን "ከፍልስፍናችን ማንነት ግብአተመሬት በፊት" በሚል ርእስ እንድንፅፍ አስገደደን???

"ሰው በሀገር ይወለዳል ይባላል። ግን ደግሞ ሀገርን የሚወልዱ ሰዎች አሉ።" እንደሚባለው ብዙ ሰዎች አሉ አገር የወለዱ፣ እየወለዱ ያሉና ወደ ፊትም የሚወልዱ። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሰዎች እስከነመኖራቸው እንኳን የሚታወቁት በጭንቅ፣ አገር እንደዚህ እንደ አሁኑ አይነት መከራ ውስጥ ስትገባና ዜጋው ሁሉ ወደ ላይ ሲያንጋጥጥ ነው። ለዚህ ደግሞ ፀጋዬ ገብረመድህንና ግጥሞቹን፣ ጥላሁን ገሠሠንና ዜማዎቹን፤ ባልቻ አባ ነፍሶ፣ አሉላ አባ ነጋ፣ በላይ ዘለቀ፤ አቡነ ጴጥሮስ ወዘተ ድልና መስዋእትነታቸውን መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው። አገርን ከአዘቅት ያወጡ፤ ማንነታቸውንም ካዘቅጥ ባወጧት አገር ላይ ያቆሙ ... ሆነው አልፈዋል።

ዛሬ፣ አስቀድሞ ሎሬቱ "ፍቅር ፈራን . . ." እንዳለው ሁሉ፣ እኛ እንደ ፍቅር የፈራነው ነገር የለም ለማለት የሌለውን ከሌለበት ፈልጎ እንደ ማምጣት ነው የሚቆጠረው። ዛሬ ፍቅር፣ እንደ ተስፋ . . . ሁሉ፣ ርቆ ተሰቅሎብናል፤ ወደ ላይ ዘልለን ያዝነው ስንል ጭራሽ ወደ ላይ ይወጣና እኛ የ'ሱ ድውያን አድርጎን እርፍ ይላል። ይህ በበኩሉ፣ የሚከባበሩት እንዳይከባበሩ፣ የማይፈራሩት እንዲፈራሩ፤ የማይጠላሉት እንዲጠላሉ . . . አደረገና እርፍ። እስኪ አሁን ማን ይሙት የሀይማኖት ተቋማት ካልተከበሩና ካልተከባበሩ ማን ሊከበርና ሊከባበር ነው??? ምእመን እርስ በርስ፤ እጅ ለ'ጅ ካለተያያዙ ማን . . .? ፅብ በእነሱ ያምራልን? በእነሱ ካማረስ በማንስ ሊያስጠላ ነው???

ዛሬ፣ ዋና ባለ ታሪኩ ሄኖክ የሆነው ሌላው ዓለም ከእጃችን እየነጠቀን ያለው "መጽሐፈ ሄኖክ"፣ ልክ እንደ ግእዝና ሌሎች ሁሉ አገር በቀል እውቀታችን መሆኑን ማን ነው የሚያውቀው? "ሀተታ ዘርዓያዕቆብ" የመካከለኛው ዘመን ፍልስፍና አባት ነው የሚለውን የምሁራን ጥናት ማን ነው ከልቡ የጣፈው? የተማሪውን፣ የወልደህይወትን ፍልስፍናዊ ውለታ ማን ነው "አባ ከና" ያለው፤ "ፍልስፍና ማለት መጠየቅ ማለት ነው" የሚለው ወገን እንኳን እነዚህን ሲጠይቅ አለመሰማቱ ምክንያቱ ምንድን ነው?? ይህ አለመጠየቅ፤ ከልብም አለመጣፍ ላለመከባበራችንስ አስተዋፅኦ የለውምን? ግዕዝስ ምን አጠፋ?

"የጥንታዊ ኢትዮጵያ(ዊያን) ፍልስፍና"፣ "የግዕዝ ቋንቋ/ሥነጽሑፍ" ("የሲግመንድ ፍሮይድ (Oedipus complex) ንድፈ ሃሳብ የተመሰረተበትን ታሪክ በጽሁፍ ይዘው ከተገኙት አምስት የዓለማችን ቋንቋዎች (ግሪክ፣ ላቲን፣ ሲራይክ፣ አረቢክ እና ግዕዝ) አንዱ (ሰምነር እንደደረሰበትና ፍቃዱ ቀነኒሳ እንደጠቀሰው) መሆን/አለመሆኑን እንኳን ሳንጠቁም፤ "የዓባይ ስልጣኔ" እያልን ከማወጃችን በፊት፤ "በኢትዮጵያ የሥነጽሑፍና ታሪክ ውስጥ በመጀመሪያው ክፍል እንደተጻፈ የሚነገርለት የመጀመሪያው የፍልስፍና ስራ መጽሐፈ ፊሳልግዎስ (physiologus) ይባላል፡፡" ከሚለው ማስታወቂያችን አስቀድመን፤ "ከአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በተለየ መልኩ በርከት ያሉ የፍልስፍና ስራዎችን በመስራት በቀዳሚነት የምትጠቀሰው ኢትዮጵያ ናት" እያልን ከማለታችንና መደምደሚያችንን ከማስቀደማችን አስቀድሞ፤ "ኢትዮጵያ ዘመናትን ያስቆጠሩ ሥነቃላዊ፤ ከዚያም የጽሁፍ ፍልስፍናዎች ባለቤት ናት፡፡" ወይም "ሀገራችን ኢትዮጵያ ገና ያልተጠኑ የበርካታ ጥንታዊ ሥነጽሑፎች ባለቤት ናት።" እያልን መሆኗን ከመናገራችን አስቀድሞ፤ "ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት፣ ስርግው ሃብተሥላሴ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም፣ ሎሬት ፀጋዬ ወዘተ እንዳጠኑት/እንዳሉት" ከማለታችን አስቀድሞ፤ ባህር ተሻግረን "እነ ፕሮፌሰር ፓኦሎ ማራሲኒ፣ አሌሳንድሮ ባውዚ፣ ሪቻርድ ፓንክረስትና ክላውድ ሰምነር ወዘተ የኢትዮጵያን ፍልስፍና ለዓለም እንዳስተዋወቁት" ሳንል፤ "አንጋረ ፈላስፋ፣ የስክንድር ሕይወትና አባባሎቹ፣ ሀተታ ዘርዓያዕቆብ እና ሀተታ ወልደ ህይወት" ወዘተርፈ እያልን ከመቁጠር፣ መቆጣጠርና መቋጠራችን አስቀድሞ ማድረግ ያለብንን አድርገናል/አላደረግንም የሚለው እራሱ ግዕዝ አፍ አውጥቶ "አይሲሲ" ላይ ቢከሰን ምክንያታዊ ነውና አይፈረድበትም።

የአዲስ አድማሱ አምደኛ ዘርዓያዕቆብን "የመካከለኛው ዘመን ፖስት ሞደርኒዝም አቀንቃኝ ነው" ሲለን ምን ማለቱ ነው? እየጠየቀን ነው? እየመለሰልን ነው? ምን እያለን ነው? ዘርዓያዕቆብን "የመካከለኛው ዘመን ፖስት ሞደርኒዝም አቀንቃኝ" ከሆነ ታዲያ ለምንድን ነው በአሁኑ ዘመን እንደ አሸን የፈሉት የፍልስፍና መጻሕፍት (በፍልስፍና የሚያላግጡትን "ፍልስምና"ዎች ጨምሮ) ነን በማለት አደባባይ ለይ የተዘረሩት ይሄንን እማይነግሩን? ወይም ሀሳቡን አስፋፍተው የማያስረዱን? እሱም ይቅር፤ ምእራባዊያኑ ላይ ብቻ ከማተኮርና እነሱኑ ብቻ ከማንቆለጳጰስ ልምን "ዘርዓያዕቆብን የመካከለኛው ዘመን ፖስት ሞደርኒዝም አቀንቃኝ" መሆኑን እንኳን ደግመው ደጋግመው ሲጠቅሱ አይታዩም? የሰምነር "ዘርዓያዕቆብ የመካከለኛው ዘመን የዓለም ፍልስፍና ፈር ቀዳጅ" ግኝትንስ ለምን ቦታ ይነፍጉታል?

"አንቀጽ 39 ሲፀድቅ ሲያጨበጭቡ የነበሩት ኢትዮጵያዊያን አልነበሩም እንዴ ዛሬ ምን ተገኝቶ ነው ..." የሚልውን የባእዳን ትዝብትም ሆነ ጥያቄ መመለስ/አለመመለስ ከእራስን ማወቅ/አለማወቅ ጋር ይገናኛል/አይገናኝም የሚለውም ያው አማረ አስቀድመው እንዳሉት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም/ይችላልና ፖለቲካዊ መፍትሄን እንኳን ባይሆን (ቢሆንም አናውቅም)፤ በአንድ ወቅት በዚሁ ጋዜጣ ላይ የደከምንበትን የ"ሀገር ግንባታ"ና "ሀገረ መንግስት ምስረታ"ን ጉዳይ ልምሻ ከማሲያዙ በፊት ሳይንሳዊ መላን፣ ፍልስፍናዊ ማጠቃለያን ይሻል እንላለን።

ሌላው አማረ አስቀድመው እንዳሉት የሚሆነው በ"ጭብጨባ! የድንቁርናና የአንባገነንነት ሽፋን" ርእሱ ስር በድሉ ዋቅጂራ (ዶ/ር) "ህዝባዊ አጨብጫቢነት" የሚለው ጉዳይ ነው። "ፍልስፍና ማለት" ምን ማለት እንደሆነ ሊነገር ይገባል እያልን እንዳልነው (ያላልነውንም ጨምሮ) ሁሉ፤ "ሕዝባዊ አጨብጫቢነት" ማለት ምን ማለት እንደሆነም ይሁን ምን ማለት እንዳልሆነ ሊነገር ይገባል፤ በየትኛው የፍልስፍና ዘውግ ሊታሽ እንደሚያስፈልግም ሊጠቆም/ሊጠቀስ ግድ ይላል የሚለው ነውና ኳሷን ለሚመለከተው መለጋት ይሁን ማቀበል ባይታወቅም ከሁለት አንዱ እንዲሆን ተደርጓልና ሀላፊነት ወርዷል ማለት ይሄኔ ነው (ማለት ነው?)።

## በመጨረሻም

ዘመኑ የሚጠየቀው ከማይጠየቀው፤ የማይደረገው ከሚደረገው፤ ተገቢው ከነውሩ፤ እውነቱ ከሀሰት . . . ድብልቅልቁ የወጣበት፤ ታናሽና ታላቁ ስፍራ የተለዋወጡበት፤ ፍልስፍናችን ሁሉ "ተበድለሃል..."፣ "ተፈልጠሃል"፣ "ተቆርጠሃል..." "ተገርፈሃል"፣ "ተጨቁነሃል" ወዘተ.... የሆነበት፤ የማይግባባው፣ ሊግባባ የሚይገባው የሚግባባበት (ለምሳሌ በአገር ማፍረስ ጉዳይ ማንም ሊግባባ የማይገባው ሆኖ ሳለ፣ አገር ለማፍረስ ተግባብቶ መስራት) ወዘተርፈ ሲሆን፤ መፍትሄውም ተነስ፣ ታጠቅ፣ ዝመት የሆነበት ቅጥ ያጣ የአላዋቂዎች ዘመን ነው። በመሆኑም ይህ ሁሉ ይቀር፣ ሥርአታት ወደ ተፈጥሯዊ ምንነትና ማንታቸው ይመለሱ፣ የሀይማኖት ተቋማት (በተራዛሚው ምእመናን) እርስ በርሳቸው ይከባበሩና በየእምነታቸው ቀኖና ይመሩ ዘንድ፤ አንዱ አንዱን መዝለፉን ያቆም ዘንድ የሁላችንም ምኞት ነው። ካልሆነ፣ "የበላችው ያገሳታል፤ በላይ በላዩ ያጎርሳታል" እንዳይሆንብን ያሰጋል። ከስጋቱ ነፃ ለመሆን ደግሞ ፍልስፍናችን ከነማንነቱ ግብአተመሬቱ መፈፀሙ በፊት መጠየቅንም፤ መመለስንም ... እንልመድ። መጠየቅ ብቻ ለሕይወት መልስ እንደማይሰጠው ሁሉ፤ መመለስ ብቻም እንደዛው። የማንነት ፍልስፍናዎቻችንን ማወቅ፣ መገንዘብ፣ መጠቀም ... እንዳለብን ሁሉ፤ የተግባቦት ክሂልም በእጅጉ ያስፈልገናል!!!

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## በጦርነት የወደሙ መሰረተ ልማቶች መልሶ ግንባታ - በአማራ ክልል

**በጋዜጣው ሪፓርተር**

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተካሄደው ጦርነት በአማራ ክልል ካደረሰው ሰብአዊ ቀውስ በተጨማሪ በርካታ መሰረተ ልማቶችን አውድሟል:: ከክልሉ መንግስት የተገኘ መረጃ እንዳመለከተው፤ በጦርነቱ 292 ቢሊየን ብር የሚገመት ቁሳዊ ውድመት ደርሷል:: ትምህርት ቤቶች፣ የጤናና የግብርና ተቋማት፣ ወዘተ ወድመዋል::

እነዚህን የወደሙ መሰረተ ልማቶች መልሶ ለመገንባት የሚያስችሉ ተግባሮች በፌዴራል መንግስት እንዲሁም በአማራ ክልል መንግስት መከናነወን ጀምረዋል:: በአንዳንድ አካባቢዎች የተገነቡ መሰረተ ልማቶች የተመረቁበት ሁኔታም ታይቷል::

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ባለፈው ጥቅምት ወር ፣ በኮምቦልቻና በከሚሴ ከተሞች ያካሄዳቸውን የመልሶ መገንባት ስራዎች ማስመረቁ ይታወሳል:: በመሰረተ ልማት ተቋማቱ ምረቃ ወቅት እንደተጠቆመው፤ በጦርነቱ ወቅት በእያንዳንዱ ተቋም አንድ ወንበር እንኳን ያልተገኘበት ሁኔታ ተፈጥሯል፤ ኮምፒውተርና ዶክመንቶች እንዲሁም ህጻናት የሚማሩባቸቸው ወንበሮች በሙሉ ተቃጥለዋል፤ወድመዋል::

በምረቃ ስነስርአቱ ላይ የተገኙት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትሯ ጫልቱ ሳኒ እንዳሉት፤ ህብረተሰቡ የወደሙትን መልሶ መጠገን ሳይሆን፣ ከነበረው ከፍ ባለ ደረጃ ለመገንባት በመግባባት ከክልሉ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የተሻለ መገንባት እንችላለን በሚል ወኔ የመሰረተ ድንጋይ አስቀምጦ ነው ወደ መልሶ ግንባታው የተገባው::

ለግንባታውም 150 ሚሊዮን ብር በመመደብ ወደ እንቅስቃሴ መገባቱንም ነበር ሚኒስትሯ በወቅቱ የተናገሩት:: የመሠረት ድንጋዩ ከተቀመጠ በኋላ እውነት በተባለው ጊዜ ውስጥ ግንባታው ይጠናቀቃል ወይ? የሚል ፍራቻ እንደነበራቸውም አስታውሰዋል:: ይሁንና በመልሶ ግንባታው ጊዜ በኮንስትራክሽን ዘርፉ ከሚታወቀውና ከስምምነቱ ውጪ ውልን በማራዘም ጊዜ ከመግዛት ተላቆ ለመጀመሪያ ጊዜ ውሉ አራት ወር ሆኖ በሦስት ወር የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ማየት እንደታቸለም ገልጸዋል::

የአማራ ክልል የከተማና መሠረተ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢያዝን እንኳሆነ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በከተሞች ሴፍቲኔት ፕሮግራም በኩል 150 ሚሊዮን ብር በመመደብ የተወሰኑ ተቋማትን መልሶ የመገንባት ሥራ ማከናወኑን አስታውቀዋል:: በዚህም በሚኒስቴሩ ድጋፍ በሰባት ከተሞች ማለትም በሰቆጣ፣ ላሊበላ፣ ወልዲያ፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ከሚሴና ሸዋሮቢት የ18 መሰረተ ልማቶች ፕሮጀክቶች መልሶ ግንባታ ሥራ መካሄዱን ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በሚኒስቴሩ በኩል 12 ክፍሎች ያላቸው ስምንት ትምህርት ቤቶች፣ ሦስት ጤና ጣቢያዎች፣ ሰባት የአንድ ማእከል አገልግሎት መስጫ ተቋማት በሰቆጣ፣ ላሊበላ፣ ወልዲያ፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ከሚሴና ሸዋሮቢት ከተሞች ላይ ተገንብተዋል:: ፕሮጀክቶቹ ትልቅ ትምህርት የተወሰደባቸውና ለወደፊት መልሶ ግንባታናሥራም መሠረት የተጣለባቸው ናቸው::

የአማራ ክልል መንግስትም የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፈንድ ጽህፈት ቤት አቋቁሞ የመልሶ ግንባታና ማቋቋም ስራውን ባለፈው ህዳር ወር በይፋ ጀምሯል:: ሰፊ ጊዜ ተወስዶ፣ በቂ ጥናት ተደርጎ ፣ ስትራቴጂክ እቅድ ወጥቶ ነው ስራው የተጀመረው:: መልሶ የመገንባት እና የማቋቋም ስራው በተቀናጀ መንገድ እየተሰራ መሆኑንም አስታውቋል::

የአማራ ክልል በጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፈንድ ጽህፈት ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ ዶክተር አባተ ጌታሁን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በስምንት ዞኖችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች በመጀመሪያውና ሁለተኛው ዙር ወረራ ብቻ 292 ቢሊዮን ብር ቁሳዊ ውድመት ደርሷል።

የአማራ ክልል በጦርነት ውድመት የደረሰባቸው አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት ከሀምሌ 1 ቀን 2014 ጀምሮ ጽህፈት ቤት አቋቁሞ እየሰራ ነው፣ በቀጣይ አምስት ዓመታት የሚተገበር ስትራቴጂክ እቅድም ባለፈው ሀምሌ ወር 2014 ዓ.ም በቦርድ ጽድቆ ወደ ስራ ገብቷል። እቅዱ በዋናነት የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናን


ዶክተር አባተ ጌታሁን

ጨምሮ ከ18 ዋና ዋና መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት የተነደፈ ነው። ከዕቅዱ በ2015 በጀት ዓመት የሚሰሩትን ለይቶ መስራት ተጀምሯል።

ከሁሉም መስሪያ ቤቶች አንድ አንድ ተወካዮች ያሉበት የዓመት እቅድ ወጥቶ እየተሰራ መሆኑን የገለጹት ዋና ስራ አስኪያጁ፤ ባለፈው ህዳር 23 በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር መሪነት የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ የመልሶ ማቋቋም ስራ በሰሜን ወሎ ዞን፣ ወርቄ ቀበሌ ላይ በይፋ መጀመሩን ተናግረዋል።

በሰሜን ወሎ ዞን ወርቄና ያያ በሚባሉ ሁለት አካባቢዎች በሚገኙ 023 እና 024 ቀበሌዎች ላይ ከፍተኛ ውድመት ደርሷል ያሉት ዋና ስራ አስኪያጁ፣ እነዚህ ቀበሌዎች 234 የሚደርሱ መኖሪያ ቤቶች፣ አንድ ጤና ጣቢያ፣ አንድ ትምህርት ቤት፣ ሙሉ በሙሉ እንደወደመባቸው ነው ያብራሩት።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የወደሙትን መኖሪያ ቤቶች መልሶ የመገንባት እና ማቋቋም ስራው ተጀምሯል። የአካባቢዎቹ ነዋሪዎች የወደመባቸውን ቤቶች ለመገንባት ለእያንዳንዱ ሰው 50 ቆርቆሮና ሰባት ፓኮ ሚስማር በመስጠት ስራው እንዲጀመር ተደርጓል:: የአካባቢው ማህበረሰብ በእርሻና በእንስሳት እርባታ የሚተዳደር ነው:: በእዚህ አካባቢ የነበረ የእንስሳት ክሊኒክም ወድሟል::

በጦርነቱ በዋናነት ስምንት ዞኖችንና ሁለት የከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ መልሶ የማቋቋም እንቅስቃሴ መጀመሩን የገለጹት ዶክተር አባተ፤ ከዚያ በፊት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ባሉበት ሁሉም የክልሉ ባለስልጣናት፣ የዞንና የከተማ አመራሮችና የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች በተሳተፉበት እቅዱ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት፣ በቀጣይም እያንዳንዱ ተወካይ በቀበሌ ደረጃ ወርዶ ሀብት ማሰባሰብ እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጦና ፕሮፓዛል ተዘጋጅቶ ነው ስራው የተጀመረው።

የመልሶ ማቋቋምና ግንባታው የክልሉ መንግሥት በመደበው አንድ ቢሊዮን ብር በጀት መጀመሩንም ስራ አስኪያጁ ጠቁመው፣ ይህ ገንዘብ ለዘጠኝ ዋና ዋና ቁም ነገሮች እንዲውል ለማድረግ እየሰራን ነው ይላሉ::

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ በዚህ ስራ ከሚከናወኑ ተግባራት የመጀመሪያው የትምህርት ቤት ግንባታ ነው:: የወርቄውን ጨምሮ 22 ትምህርት ቤቶች ይገነባሉ:: በሁሉም ዞኖች በዋናነት በሰሜን ጎንደር፣ ደቡብ ጎንደር፣ ዋግኽምራ፣ ሰሜን ወሎ፣ ደቡብ ወሎ፤ ደሴ ከተማ፣ ኮምቦልቻ ከተማ፣ ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞንና ሰሜን ሸዋ ላይ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ተለይተዋል፤ ዞኖቹና ከተማ አስተዳደሮቹ ከክልሉ የሚመለከታቸው ቢሮዎች ጋር በመመካከር በቦርድ በማስደቅ 22 የሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገነባሉ::

እንደ ዶክተር አባተ ገለጻ፤ በጦርነቱ አንድ ሺ 151 ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ወድመዋል። ከነዚህ ውስጥ በትምህርት ሚኒስቴር 45 ትምህርት ቤቶች፣ በክልሉ ደግሞ 22 ትምህርት ቤቶች እየተገነቡ ነው። ይሄ የመጀመሪያና የመነሻ ፕሮጀክት ነው::

በጤና ተቋማት 10 ክሊኒክ፣ አንድ ሆስፒታል (የቆቦ ሆስፒታል ስስት ጊዜ እንዲወድም ተደርጓል፤ የዚህ ሆስፒታል የወደመው ክፍል መልሶ ግንባታ ይካሄዳል); በግብርና ዘርፍ የተለያዩ የእንስሳት ክሊኒኮች፣ ግብርና ኮሌጆች፣ የምርምር ተቋማት፣ በአጠቃላይ ወደ 64 የሚሆኑ ፕሮጀክቶች እንዳሉም ጠቁመዋል:: ወጣቱን መሰረት አድርጎ መስራት እንደሚገባም ተናግረው፣ የወጣቱ ትውልድ ስነ ምግባር ላይ መስራት ያስፈልጋል:: ‹‹አልተጠቀምንበትም እንጂ እኛ እድለኞች ነን:: በርካታ የህብረተሰብ ክፍላችን ወጣት ነው›› ያሉት ዋና ስራ አስኪያጁ፣ ለዚህም የስነ ምግባር መገንቢያ ማእከላት እንደሚያስፈልጉ ይገልጻሉ:: በመሆኑም 17 የወጣት የሥነምግባር መገንቢያ ማዕከላትን/ ለሁሉም ዞኖች/ ማዕከል ያደረገ የመልሶ ግንባታ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከስራ እድል ፈጠራ ጋር ግንኙነት ያለው ስራም ይካሄዳል:: ስራ ፈጠራ ላይ አንድ ማእከል የሚባል ነገር አለ፣ አንድ ማእከል ወደ አስራ አምስት ሺ ለሚሆኑ ሰዎች አገልግሎት ይሰጣል:: በመልሶ ግንባታው አስር የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ይገነባሉ::

ጎን ለጎን አመራሩ ስራ ፈጠራ ላይ ያለው እውቀት እንዲዳብርና የተሻለ ሰራተኛ እንዲሆን በሀገር ደረጃ ካለው ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን በሶስት ዙር የፐብሊክ ኢንተርፕረነርሽፕ (Public Entrepreneurship) ስልጠና ተሰጥቷል:: ለ210 አመራር ስልጠናው ተሰጥቷል:: እያንዳንዳቸው አንድ ሺ ሰው የሚገለገልባቸው ማዕከላት መልሶ ግንባታ ይካሄዳል፣

በውሃ ዘርፍ 31 የሚሆኑ የተለያዩ ጉድጓዶችን፣ ምንጮችን የመገንባት፣ 421 ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ለመገንባት ኮንትራክተሮች ውል ወስደው በሁሉም ዞኖች ሄደው ስራ እንዲጀምሩ ተደርጓል። ለዚህ ሁሉ አንድ ቢሊዮን አንድ መቶ 29 ሚሊዮን ብር ተመድቦ እየተሰራ ስለመሆኑ ገልጸዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ውድመቱ በጣም ብዙ ነው:: ቁሳዊ ውድመቱ ብቻ ወደ 292 ቢሊየን ብር ነው፤ ችግራችን ቁሳዊ ትርጉም ብቻ እየሰጠን ነው እንጂ፣ በገንዘብ ሊተመን የማይችል የከፋ የሰብአዊ፣ ስነልቦናዊ፣ማህበረ ባህላዊ ውድመቶችም ደርሰዋል::

‹‹በዚህ አመት ምን ያህል ትሰራላችሁ›› የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው ዋና ስራ አስኪያጁ፣ ‹‹ትምህርት ቤቶቹን፣ የውሃ ተቋማቱን፣ የጤና ተቋማቱን ወዘተ ከቻልን በቀጣይ አምስት አመት እንጨርሳለን:: በዚህ አመት ይህን ያህል እንሰራለን ማለት አልችልም፤ ባገኘነው ሀብት ልክ እንሰራለን›› ሲሉ አብራርተዋል::

እንደርሳቸው ማብራሪያ፣ ውድመቱ ከባድ ነው፣ የሚፈልገውም ድጋፍ ከፍተኛ ነው። አለም አቀፍ ሁኔታው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ፓለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አለ:: ወደ ግራም ወደ ቀኝም መዋዠቅ አለ፤ ከእኛ ጋር የሚሰሩ የምናደንቃቸው አለም አቀፍ ድርጅቶች አሉ:: 53 የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተለይተው በተናበበ መንገድ እየተሰራ ነው።

በስትራቴጂክ እቅዳችን መሰረት የዓለም ባንክ፣ ዩኤንዲፒ፣ ወርልድ ቪዥን ከክልሉ መልሶ ማቋቋምና ግንባታ ጽህፈት ቤት ጋራ በቅንጅት እየሰሩ ናቸው። የአለም ባንክ እየጀመረ ነው፤ ዩኤንዲፒና ወርልድ ቪዥን እያገዙን ናቸው፤ በጣም በጥሩ ሁኔታ መሬት ወርደው እየሰሩ ያሉ ድርጅቶች አሉ፤ በተለይ ዩኤንዲፒ እጅግ በጣም ሊመሰገን ይገባዋል::

የአለም ባንክ ሰባት ወረዳዎችን መርጧል፤ ለትግራይ፣ ለአማራ ፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 300 ሚሊየን ዶላር ለአንድ አመት መድቧለ3፤ ስራው እድገት አሳይቷል፤ እኛም በቀጣይ አብረን ጥሩ እንሰራለን ብለን እያሰብን ነው::

አንዳንድ ያለመናበብና የድግግሞሽ ችግሮችን ለማስወገድ እንደሚሰራም ነው የተናገሩት:: ክልሉን ሊያግዙ የሚፈልጉ አካላት በዚህ ጽህፈት ቤት አማካይነት ሀብቱ በአንድ ቋት ውስጥ ተቀምጦ ቆጣቢ በሆነ መልኩ እንዲሰራ ክልሉ የሚፈልግ መሆኑን ገልጸዋል::

ዶክተር አባተ እንዳብራሩት፤ በጦርነቱ የተፈጸመው ሁሉ ይዘገንናል:: በቀጥታም በተዘዋዋሪም የደረሰው ውድመት ሰው የሚባል አካል ይፈጽመዋል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም:: ከዚህ በላይ ላለመውደም ሁሉም ሰው በውይይት እንዲያምን ማድረግ ያስፈልጋል:: በጣም የተማርን ነን የሚሉት በየዩቲዩቡና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች የሚያካሂዱት የጥላቻ ዘመቻና የጦርነት ቅስቀሳ እንዲያቆሙ ሚዲያዎች ትልቅ ሃላፊነት አለባቸው:: ሚዲያ ትልቅ ሀይል ነውና ሚዲያዎች መልሶ ሌላ ውድመት እንዳይከሰት መስራት ይጠበቅባቸዋል::

‹‹ ቆቦ ከተማ ላይ ሶስት ጊዜ የወደሙ ተቋማትን የተመለከተ ያሳዝናል:: በትግራይ፣ በአማራና በአፋር የተፈጸመው ጥፋት ዘግናኝ ነው፤ የእርስ በርስ ጥፋት ነው›› ያሉት ዶክተር አባተ፣ ‹‹እኛ እንደ ሰርገኛ ጤፍ ነን:: ልንለያይ የማንችል ነን:: ሁሉም ወደ ቀልቡ ተመልሶ ከጦርነት ታቅቦ ነገሮች በውይይት ቢፈቱ መልካም ነው፤ ይሄ ዘላቂው መፍትሄ ነው:: ጦርነት አያዋጣም ፤ ትልቅ ጥፋት ነው:: ሚዲያ ትልቅ ሀይል ነው:: ጋዜጠኞችም ትልቅ ሀብት ናችሁና ሁላችንም ከዘርና ከሃይማኖት ወገንተኝነት ወጥተን ብንሰራ ጥሩ ነው›› ሲሉም አስገንዝበዋል::

‹‹የወደሙትን ተቋማት ተጋግዘን መልሰን ማልማት አለብን፤ አንድ ጥናት ያመለከተውን ብቻ ይዘን ነው 292 ቢሊየን ብር ውድመት ደርሷል ያልነው:: ትምህርት ቤቶች የሉንም፤ ፊቱንም በኢትዮጵያ የተሻለ ትምህርት ቤት የለም፤ አሁን ደግሞ ብሷል፤ የጤና ተቋማት፣ የግብርና ተቋማት ወድመዋል:: ‹ጋን በጠጠር ይደገፋል› እንደሚባለው ሁላችንም ተረዳድተን የወደመውን ለመተካት መስራት አለብን፤ ነጠብጣብ ነው ጎርፍ የሚፈጥረውና እንረዳዳ›› ይላሉ::

የሚገኘውን ሀብት በተቻለ መጠን ቆጣቢና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መልኩ መጠቀም እንደሚገባም አሳስበው፣ በአማራ ክልል ቁጠባን ታሳቢ ያደረገ ከላይ እስከ ታች ድረስ የተናበበ አሰራር መከተል እንደሚገባም አስገንዝበዋል::

ሀብትን በትክክል በመጠቀም የመልሶ ግንባታና ማቋቋም ስራው ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን አስታውቀው፣ ለዚህ ስራ ስኬታማነት የአገር ውስጥ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶችና መላ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ እንዲያደርጉም ዶክተር አባተ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላም ስምምነቱ ትግበራ የሁሉንም ሰላም ወዳድ ኃይል ያልተቆራረጠ ድጋፍ ይሻል!

ለሁለት ዓመታት የዘለቀው እና አገርና ህዝብን ብዙ ዋጋ ያስከፈለው የሰሜኑ ኢትዮጵያ ግጭት በቅርቡ በፕሪቶሪያ በተደረሰ የሰላም ስምምነት መነሻነት አሁን ላይ የሰላም አየር መንፈስ ጀምሯል፡፡ የሰላም ስምምነቱ ታዲያ ዜጎች ከጦርነት አደጋ እፎይታን ያገኙበት ብቻ ሳይሆን፤ ለመኖር የሚያስፈልጓቸውን መሰረታዊ የሚባሉ የምግብ፣ የመድሃኒትና ሌሎች ሰብዓዊ ድጋፎችን እንዲያገኙ አስችሏቸዋል፡፡ የተፈናቀሉ ወገኖች ወደ ቀየያቸው የሚመለሱበትን ዕድልም ፈጥሯል፡፡ የፈረሱና አገልግሎት ያቋረጡ የውሃ፣ የመብራት፣ የጤና፣ የባንክ፣ የቴሌ፣ የመንገድና ሌሎችም መሰረተ ልማቶችም በየደረጃው እየተጠገኑና እየተደራጁ ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

ይሄ ዜጎች ከመንግስታቸው ማግኘት የሚገባቸው አገልግሎቶች እንዲያገኙ የመደረጉ ሂደት መሳካት ታዲያ፣ ከመንግስት ያላሰለሰ ጥረት በኋላ በሰላም ስምምነቱ ላይ እንዲካተት መደረጉ አጋዥ ምክንያት ነበር፡፡ ለዚህም ነው ቀደም ሲል ሲሰራ ከነበረው በተሻለ መልኩ የሚሰሩ ስራዎች ለውጤት መብቃታቸው፤ የሚላኩ ሰብዓዊ ድጋፎችም ለሚመለከታቸው ዜጎች መድረስ መቻላቸው፡፡ በዚህ ረገድ ደግሞ መንግስት እንደ መንግስት የወሰደው ግንባር ቀደም ቁርጠኝነት ጉልህ ሚና ያለው ሲሆን፤ የመንግስትን ቁርጠኝነት ተከትሎም በርካታ አጋር አካላት ድጋፍ ወደማድረግ እንዲገቡ፤ በሕወሓት በኩልም በስምምነቱ የገባውን ቃል ወደመፈጸም እንዲያማትር አድርጎታል፡፡

በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነትም ሆነ በናይሮቢው የጦር አመራሮች የመግባቢያ ስምምነት መሰረት፤ ለምሳሌ፣ ሕወሓት ታጣቂዎቹን በማወያየት ትጥቅ ማስፈታት እና ወደ ተሃድሶ መስጫ ማዕከላት ማስገባት እንዳለበት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ይሄን መነሻ በማድረግም የማወያየት እና በየደረጃው ትጥቅ የማስፈታት እንዲሁም ወደ ተሃድሶ መስጫ ማዕከላት የማስገባት ስራዎችን ስለመጀመሩ ተነግሯል፡፡ ይሄ ደግሞ መንግስት ለጀመረው መልካም ተግባር እንደ አንድ አጋዥ ሂደት የሚወሰድ ሲሆን በሕወሓትም በኩል ለሰላም ስምምነቱ እውን መሆን ሲባል የተጣለበትን ኃላፊነት በፍጥነት መወጣት እንዳለበት የሚያመላክት ነው፡፡

ይሄ በመንግስትም ሆነ በሕወሓት በኩል የታየው አበረታች ተግባር ታዲያ ሰላም ወዳድ የሆነውን ሕዝብ እና ለኢትዮጵያ መልካም የሚመኙ ኃይሎችን ሁሉ ይበል ያሰኘ ነው፡፡ በአንጻሩ ግን ለኢትዮጵያውያን ሰላምን፣ ለኢትዮጵያም ብልጽግናና ዕድገትን የማይመኙ በውስጥም በውጪም ያሉ ሰላም ጠል ኃይሎችን በእጅጉ እንቅልፍ የነሳ፣ ይልቁንም ለሰላም ስምምነቱ እውን መሆን የሚከወኑ ተግባራትን በየምክንያቱ እንዳይሳኩ ለማደናቀፍና በሃሰት ብሮፖጋንዳ ለማጓተት የሚያስችሏቸውን ስትራቴጂዎች ነድፈው እየተንቀሳቀሱ መሆኑ በተለያዩ ሁኔታዎች እየተገለጡ ናቸው፡፡

ሆኖም በጥቂት ሰላም ጠል ኃይሎች ሴራና አካሄድ የሚዝል የሰላም ክንድ፤ የሚታጠር የሰላም መንገድ፤ የሚዘጋም የሰላም በር አይኖርም፡፡ ለዚህም ነው መንግስትም ሆነ ሕወሓት ለሰላም ስምምነቱ እውን መሆን በየፊናቸው ከሚያከናውኗቸው ተግባራት በተጓዳኝ በሚሰሯቸው ስራዎች አካሄድና ውጤታማነት፣ እንዲሁም ቀጣይ አቅጣጫዎቻቸው ላይ በአፍሪካ ህብረት ጥላ ስር ሆነው መወያየትን መርጠው ከሰሞኑ በኬንያ ናይሮቢ የተገናኙት፡፡ በዚህም ውጤታማ ውይይት ማድረጋቸው የተነገረ ሲሆን፤ እስካሁን የተከናወኑ ተግባራትም የሚበረታቱና ተጠናቅረው ሊቀጥሉ የሚገባቸው ስለመሆኑም ነው መረጃዎች ያሳዩት፡፡

በዚህ ረገድ በሰብዓዊ ድጋፍ፣ በመልሶ ግንባታና በሌሎችም የተገለጡ የመንግስትን ቁርጠኝነትና ከፍ ያለ ስራ ያሳዩ እንደመሆኑ፤ ይሄው ተግባር በአጋር አካላት ጭምር ሊታገዝና የበለጠ በችግር ውስጥ ላሉ ዜጎች ተደራሽ እንዲሆን ማስቻል ከሁሉም የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ በሕወሓት በኩል የተጀመረው ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታትና ወደ ተሃድሶ ማዕከላት የማስገባቱ ተግባርም በአከባቢው ውጥረትን የማርገብና ለዜጎች የሰላም ፍላጎት እውን መሆን ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ እንደመሆኑ፤ ጅምሩ ወደ ላቀ ቁርጠኝነት ተሸጋግሮ የስምምነቱን ተግባራት በፍጥነት ሊተገብረው ያስፈልጋል፡፡

በዚህ መልኩ በመንግስትም ሆነ በሕወሓት በኩል የሰላም ስምምነት ላይ ለመድረስ ያሳዩት ቁርጠኝነትና ጽናት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በተለይም በመንገሰት በኩል ለተፈጻሚነቱ ያሳየው ትጋትና ቁርጠኝነት የሚበረታታ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የሰላም ኃይሎችን የሚያስደስትና በዛው ልክ ለሙሉ ድጋፍ የሚያነሳሳ፤ በተቃራኒው ሰላም ጠል ኃይሎችን ምኞት የሚያኮላሽ ነው፡፡ ሆኖም ለስምምነቱ ትግበራ መሳካት የተጀመረው አበረታች ሥራ በሁለቱ ወገኖች ጥረት ብቻ ከዳር የሚደርስ አለመሆኑን መገንዘብ፤ ይልቁንም የሁሉንም ሰላም ወዳድ አካላት ያልተቆራረጠ ድጋፍ የሚሻ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም ሰላም ወዳድ ኃይል ለውጤታማነቱ ያላሰለሰ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል!


ኢፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የበጎ ፈቃደኝነት ማጎልበቻ ሁነኛ ውሳኔ

**ሰላማዊት ውቤ**

በጎ ፍቃደኝነት ከበጎ ህሊና የሚመነጭ የተቀደሰ ተግባር ነው። ከራስ አልፎ ለሌሎች የመሆንን ፤አሳቢነትን አካፋይነትን አቋዳሽነትን፤ ተባባሪነትን ፤እኔ ብቻ አለማለትን ፤ተጋግዞና ተደጋግፎ መኖርን የሚገልፅ ከፍ ያለ ስብዕና መገለጫ ነው።

በጎነት ለራስ ጤንነት የሚሰጥ ፤ በፈጣሪ ዘንድም ውድ ዋጋ ያለው ነው።በጎነት በማግኘትና ማጣት ስሌት የማይለካ ከራስ ወዳድነት ነፃ በሆነ መንገድ ለሌሎች ያለምን ክፍያ የሚደረግ ተግባር ነው። የአፍ ወይም የቃል ምስጋናን እንኳን የማይጠብቅ ወይም ይሄን እንኳን ለማግኘት ታስቦ የማይደረግ ነው።በጎ ተግባር የሚፈፅሙ ሰዎች በሕይወታቸው አእምሯዊ እርካታን የሚያገኙ፤ጤናሞችና ደስተኞች መሆናቸውን የስነ ልቦና ባለሙያዎች ይጠቁማሉ።

ኢኮኖሚስቶችና የማህበራዊ ጉዳይ ጠበብቶች በፊናቸው እንዲህ መሰሉ በጎ ፈቃደኝነት ለአንድ ሀገርና ለእዛ ሀገር ሕዝብ ዕድገትና ሕይወት መሻሻል በተናጠልም ሆነ በጋራ የጎላ ፋይዳ እንዳለው ይናገራሉ።

ለተደጋገፉና ለተባበሩ እጆች ለውጥ ቀላል ነው።በጎ ፈቃደኝነትም የህብረተሰብን አኗኗርን ሊያሻሽሉና ሊለውጡ እንዲሁም ሃገርን ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራትን፤ በራስ ተነሳሽነት፤ ተጨማሪ ክፍያ ወይም ምንዳ ሳይጠየቅበት የሚከወን ተግባር ነው።

ኢትዮጵያና በጎ ፈቃደኝነት ረጅም አመታትን ያስቆጠረ ትውውቅና ትስስር አላቸው፡ለ ኢትዮጵያውያን የመረዳዳት፣ የተቸገረን የመደገፍ፣ የታመመን የመጎብኘት ልምድ አላቸው፡ይህ የእርስ በርስ መደጋገፍ ለዘመናት አብሮ የኖረ እና ዛሬም ድረስ የዘለቀ ነው።

እዚህ ጋር ለአብነት ትላንትና በአንድ ዳቦ ቤት ያየሁትን ላካፍላችሁ ።አንድ ታዳጊ የሚፈልገውን ዳቦ ለመግዛት አንድ ብር ጎደለው ።አንዱ ምስኪን እናት ለእኔ ዘጠኝ ዳቦ ስጠኝና ለእሱ አንድ ብሩን ሞልተህ የሚፈልገውን ስጠው አሉ።

ይሄን ለራሳቸው ሳይኖራቸው ሌላውን ለመደገፍ ወይም ካላቸው ለማካፈል የፈለጉን በጎ እናት ተግባር የሰሙ አንድ አባት በፊናቸው «ለእሱም ለእሳቸውም የሚፈልጉትን ስጣቸው»ብለው ለዳቦ ሻጩ 50 ብር ሰጥተው ወጡ። ከዚህ የበለጠ የኢትዮጵያዊያኖችን እርስ በእርስ መደጋገፍ መሰረት ያደረገና በማግኘትና ማጣት ስሌት የማይለካ በጎነት የሚያሳይ ምሳሌ የለም።

በአሁን ወቅትም ሚሊየኖች ባላቸው እውቀትና ሃብት በመላካምነትና በበጎ ፍቃድ ስራዎች ተሳታፊ በመሆን በርካቶችን እየደረሱ ናቸው።መንግስት ይህንን በጎ ተግባር ዕውቀቱ፣ ልምዱና ፍላጎቱ ያላቸውን ሰዎች ድጋፍ ከሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር እንዲገናኝ በማድረግ ተግባሩን በማስተባበር ወሳኙን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል።

ዓለም አቀፍ የበጎ ፈቃደኞች ቀን በኢትዮጵያ ካሳለፍነው ህዳር 26/2015 ጀምሮ «በጎ ፈቃደኝነት ለአብሮነት» በሚል መሪ ቃል በብሔራዊ ደረጃ እየተከበረ ይገኛል።የበአሉ መከበርም በሕዝቡ ዘንድ ለዘመናት የቆውን የበጎ ፈቃደኝነት አስተሳሰብ ከፍ ለማድረግ አቅም የሚፈጥር ነው።

የበጎ ህሊና ባለቤቶችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ የእርስ በርስ የመተዋወቂያ መድረክ በመፍጠር ልምድና ተሞክሯቸውን እንዲለዋወጡ ያስችላል።መልካም ተግባሩ ይበልጥ እንዲጎለብትና በርካታ ቅን ልቦናዎች እንዲፈጠሩም ያደርጋል።

ሀገራዊ አንድነትን፤ ሀገራዊ ትስስርና ፍቅርን የሰነቀው የክብረ በአሉ መሪ ቃልም እርስ በእርስ የመተሳሰብ፤ የመደጋገፍና የመረዳዳት ባህልን ማጎልበት ከፍ ሲልም እንደ ሀገር አንድ ሆነን የቆምንበትን የአብሮነት ገመዳችንን የበለጠ ለማጠናከር የሚያግዝ ነው።

በዓሉ በተከበረበት ወቅት ለመጀመሪያ ጊዜ ብሔራዊ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ፖሊሲ እና ብሔራዊ የወጣቶች የዜግነት አገልግሎት አዋጅ በረቂቅ ደረጃ መዘጋጀቱ ታውቋል። አገልግሎትን ለማሳለጥ የሚያስችል ሶፍት ዌር ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ መዋሉ ይፋ ሆኗል። አሁን ወቅትም ፖሊሲውና አዋጁ በተለያየ ደረጃና ቦታ ውይይት እየተደረገባቸው ይገኛል።

ብሔራዊ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ፖሊሲ እና ብሔራዊ የወጣቶች የዜግነት አገልግሎት አዋጅ እውን መሆንም ከበጎ ህሊና የሚመነጭ የተቀደሰ ተግባር ይበልጥ ለማጎልበት ፋይዳው ዘርፈ ብዙ ነው።

በጎ ፈቃደኞች ተጠያቂነትን ታሳቢ አድርገው የበለጠ ተግባራቸውን እንዲከውኑ ያግዛሉ።በተግባሩ ዙሪያ የትኛውም ዓይነት ጥርጣሬና ቅሬታ በውስጣችን እንዳይፈጠር ይረዳል።ግልፅነትን ለማስፈንም ጥሩ መደላድል ይሆናል።

በተለይ ወጣቶች በሰላም ግንባታ፣ በማህበረሰብ ልማት፣ በአካበቢ ጥበቃና በብዙ መስኮች በባለቤትነት ስሜት በመንቀሳቀስ ሀገራዊ አሻራቸውን እንዲያሳርፉ ያስችላል።በዚሁ ተግባር ዙርያ ያላቸውን ተሳትፎ የበለጠ እንዲያጠናክሩና እንዲቀጥሉበት ያግዛል።

ተግባራቸው በወቅት እንዳይወሰን በተለይም በበጋና ክረምት ብቻ እንዳይወሰን፤ በድንበር እንዳይገደብ የማድረግም ኃይል ይኖረዋል። ሥራው በራሱ የክረምት ወይም የአንድ ወቅት የዘመቻ ሥራ ሆኖ ከሚከናወንበት አሰራርም እንዲላቀቅ የጎላ ሚና ይኖረዋል።

በአጠቃላይ የፖሊሲና አዋጅ መዘጋጀት ወጣቱ የሕብረተሰብ ክፍል በተግባሩ ላይ ያለውን ተሳትፎ ወደ ላቀ ደረጃ ከማሸጋገር በተጨማሪ በሕዝቡ ዘንድ ለሀገር ዋልታና ማገር የሚሆን የተጠናከረ ማህበራዊ መስተጋብር እንዲኖር ከፍተና አቅምን የሚፈጥር ነው።

በወጣቶች የተዘጋጀው ሶፍት ዌርም መልካም ተግባሩን ከማሳለጥም ባለፈ ትርጉሙ ላቅ ያለ ነው።የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንቅስቃሴ አንድ ወጥ በሆነ፤በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ እንዲቀጥል ዘርፈ ብዙ ዕድሎችን ይፈጥራል።በውጭም በሀገር ውስጥ የሚገኙ በጎ ሰዎችን ቁጥር ያበራክታል።

ተግባሩ በዳበረ የመረጃ ቋት ተሳልጦ መሰራቱ በጎ ፈቃደኝነት ከባህላዊ ወይም ከዘልማድ ተላቆ ወደ ዘመናዊና የሰለጠነ አሰራር ደረጃ እንዲሸጋገር ያደርጋል። ለበጎ ፈቃደኝነት የዋለን ጊዜና ገንዘብ፤ተግባሩ እንደ ሀገር እያደረገ ያለውን አስተዋጾኦ በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል። በተለይ ኢኮኖሚው ላይ ያለውን አስተዋጾኦ በቁጥር መናገር የሚቻልበት ግልፅ ስርዓት ይዘረጋል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ‹‹ልጆቼ አንድ ቤት ተሰብስበው፤ መኝታ አግኝተው የሚያርፉበትን ቀን እናፍቃለሁ››

## - ወይዘሮ ብርሃኔ ድጉማ

ሰላማዊት ውቤ



ወይዘሮ ብርሃኔ ድጉማ ከጣሊያን ሰፈር ነዋሪዎች አንዷ ናቸው። የሚተዳደሩት በጥበቃ ሥራ የተሠማሩት ባለቤታቸው በሚሰጧቸው ጥቂት ብርና ደጃፋቸው ላይ ወይራን ጨምሮ ከሰልና ቁጤማ በመሸጥ ነው። ዘንድሮ ጅባው ቁጠማ ሦስት ሺህ ብር በመግባቱና ሲቸረቸር ባለማትረፉ ትተውት ወይራና ከሰል ብቻ ነው እየሸጡ የሚተዳደሩት።

ወይዘሮ ብርሃኔ መንገድ ዳር በምትገኘው ሁለት በሁለት በሆነች ቆርቆሮ ቤት ውስጥ ከባለቤታቸውና ከሦስት ልጆቻቸው ጋር ይኖራሉ። ቤታቸው መንገድ ዳር ይባል እንጂ ቤታቸው መንገድ ውስጥ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በዚያ ላይ ለቤቱ የንፁሕ መጠጥ ውሀ አገልግሎት ስላልገባ ወይዘሮዋ የንፁሕ ውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ አይደሉም።

እዚህ የሀገሪቱ ዋና መዲናና የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ ለዚያውም ጣሊያን ሰፈርን በመሰለ መሐል ከተማ ላይ ተቀምጠው እንደ ገጠሯ እንስት በንፁሕ መጠጥ ውሃ ይሰቃያሉ ቢባል ማንም አያምንም። ግን በባለ 20 ሊትሩ ጀሪካን አንዱን አራት ብር ሂሳብ ከአካባቢያቸው በመግዛት እየተሸከሙ ነው የሚጠቀሙት። የእሳቸውንና የቤተሰባቸውን ልብስ በሚያጥቡበት ወቅት እስከ 10 ባለ 20 ጀሪካን ውሃ በመቅዳት በጀርባቸው እየተሸከሙ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል።

ውሃ ብቻ ሳይሆን ቤታቸው የኤሌክትሪክ መብራትም የለውም። ይሄንንም ማለቱ ቢከብድም ወይዘሮዋ ከነባለቤታቸውና ልጆቻቸው ለዓመታት ጨለማ ውስጥ ነበር የሚያድሩት። በጨለማ መኖራቸውን ያስተዋሉ በጎ ሰው ታዲያ በብዙ ርቀት ከእሳቸው ጠልፈው እንዲያስገቡ ፈቅደውላቸው ነው የኤሌክትሪክ ገመድ አስገብተው ብርሃን ያዩት። የእግር መንገድ እንኳን የሌለው አስፋልት ውስጥ የገባው የ38 ዓመቷ የወይዘሮ ብርሃኔ የጣሊያን ሰፈሩ ቤት የሚገኝበት ቀበሌ 04/05 ነው።

ይሄ ቀበሌ በወረዳ ሁለት ውስጥ ይገኛል። በመሆኑም ቀበሌውም ሆነ ወረዳው የወይዘሮዋን ቤት አሳምረው ያውቁታል። የቤት ቁጥር 605 ብሎክ ዘጠኝ በሚል መዝግበውትም ይገኛል። ቤታቸው በቀጠና አምስትም እንዲሁ ዕውቅና ያገኘበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን ወይዘሮ ብርሃኔ እንደሚሉት፤ ግድግዳና ጣሪያው በአላፊ አግዳሚ መኪኖች ሲገነጠል፤ በዚሁ ምክንያት እንቅልፍ አጥተው ዘብ ቆመው ሲያድሩ ያገባኛል ብሎ ተከራክሮላቸው አያውቅም። በዚህም የወይዘሮ ብርሃኔ ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት ቀንም ሆነ ማታ ዕጣ ክፍሉ በመኪና መገንጠል ፤ በድንጋይ ውርወራ መነረት ነው ሥራው።

‹‹አሁን በቀደም ዕለት የቁራ መኪና ጣሪያውን ገንጥሎብኝ ነው የሄደው። ማታ ወይራና ከሰል ይገፔ ስመጣ ነው ያየሁት። ከትላንት በስቲያ ደግሞ አንድ ከባድ መኪና እንዲሁ ግድግዳውን ገንጥሎት ያሠራሁበት ሁኔታ አለ።” ይላሉ ወይዘሮ ብርሃኔ ሁኔታውን በምሬት እየተንገፈገፉ ሲገልፁት። ቀጥለውም ”አብዛኞቹ፤ እንደውም ሁሉም መኪኖች ቤታቸውን በዚህ መልኩ አጓጉል ካደረጉ በኋላ በፍጥነት እንደሚያልፉ በታከተ ስሜት ያወሳሉ። የገነጠሉት አጥር ይሁን ቤት ቁብ ስለማይሰጣቸው ዞር ብለው እንኳን አያዩትም። እንደ ነፋስ ሽው እያሉ ነው የሚያልፉት ። ሲገነጥሉት አይተን የአካባቢው ሰው ወይም እኔ ስንናገር አሽከርካሪዎቹ ቆም ብለው እንኳን አያዳምጡንም›› በማለት የዕለት ተዕለት ገጠመኛቸውን በምሬት ይገልፁታል።

በጥበቃ ሥራ የተሠማሩት ባለቤታቸው በየወሩ ከሚያገኙዋት ሦስት ሺህ ብር ላይ ለቤት ወጪ ብለው የሚሰጧቸውን አንዴ ጣሪያውን፣ ሌላ ጊዜ ግድግዳውን እያሉ ለዚሁ ቤት ጥገና ነው የሚያውሉት። በብዛት አንዳንድ ለነፍስ ያሉ አናጢዎች በነፃ ይጠግኑላቸዋል። ሰፈርተኛው መልሶ ለሚገነጠለው ባታሠሪው ይሻላል ይላቸዋል። ወይዘሮ ብርሃኔ በቤታቸው ዕጣ ፈንታ ከንፈሩን የሚመጣው ጎረቤት ብዙ እንደሆነም ይናገራሉ። እሳቸውም እንደለመዱትና ሁሉም ትዕይንት ምንም እንደማይመስላቸው ያወሳሉ። ግን ደግሞ በሁኔታው ቆሽታቸው እርር ድብን ማለቱ እንደማይቀር ፤ በዚሁ ምክንያትም በሚደርስባቸው ብስጭትም በአሁኑ ወቅት ለኃይለኛ ጨጓራ በሽታ መዳረጋቸውን ያስታውሳሉ።

የቤታቸው ስጋት የቆርቆሮ፣ግድግዳና ጣሪያ በመገንጠል ብቻ የሚያልቅ አለመሆኑ ወይዘሮ ብርሃኔን ዘወትር ያሳስባቸዋል። ቆርቆሮና አጥሩ ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡ በተለይም ሦስቱም ልጆቻቸው ለመኪና አደጋና ለድንጋይ ውርወራ የተጋለጡ እንደሆነ ያወሳሉ። ‹‹ ምንም ደሃ ብሆንና እንደዚህ ዓይነቱ ለኑሮ ምቹ ያልሆነ ቤት ብኖርም ልጆቼን በጥርሴ ይገፔ ነው ያሳደኳቸው›› የሚሉት ወይዘሮ ብርሃኔ፤ ብዙ መከራና ስቃይ እያዩ ያሉትም እነሱኑ ለማሳደግ ብለው እንደሆነ በአፅንዖት ይናገራሉ።

እነሱ ባይኖሩ እንደዚያ ባለ ቤት ውስጥ በአስከፊ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ መኖርን አይመርጡም ነበርም። ግን ‹‹ጎሽ ለልጇ ስትል ተወጋች›› እንዲሉት ሆነና ነገሩ ሁሉ ነገር ተደፍቶባቸው ኑሮውን እየኖሩት ይገኛሉ። ደስተኛ ባይሆኑም ‹‹ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል›› ዓይነት ሆኖም ለልጆቻቸው ደስታን ለመፍጠር እየተጉ ነው። ልጆቼን አሳድጋለሁ ብለው በማሰብ ሌት ተቀን መልፋታቸውንም አላቆሙም። ነገር ግን እሳቸው ለልጆቻቸው ይሄን ያህል ዋጋ በመክፈል ይኑሩ እንጂ ልጆቻቸው በዕለት ተዕለት ኑሯቸው በፍፁም አልተመቻቸውም። ለበርካታ አደጋ የተጋለጡም ናቸው። እንደውም ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ስላሉበት ጉዳይ ሲናገሩ እንባ ይተናነቃቸዋል። ከዚያም አልፎ ከንግግራቸው ቀድሞ መውረድ ይጀምራል። እናም ወይዘሮ ብርሃኔ የ14 ዓመቱና የሰባተኛ ክፍል ተማሪው ልጃቸው እግዚአብሔር ረድቶት ከሞት ይትረፍ እንጂ ደጋግሞ የመኪና አደጋ ሰለባ ሆኖ እንደነበርም ያስታውሳሉ። ሁለት ጊዜ ገፍትረው ጥለውት በመጡበት ፍጥነት በመሄዳቸው እራሳቸው ናቸው ያሳከሙት።

ከዚህ አገገመና ተረፈ ብለው ሲሉ ለሦስተኛ ጊዜ አንድ መኪና ገጭቶት እየበረረ ሄደ። እንደ ዕድል በሥፍራው የነበሩ የሰፈር ልጆች ገጭቶ ጥሎት እየበረረ መሄዱ በአጅጉ አስቆጭቷቸውም ሌላ መኪና በመለመን አሳድደው ያዙት። ታርጋውን የያዙም ነበሩ። በዚህ መልኩ ባደረጉት ርብርብም እንዲያሳክመው አደረጉ። ፊኛውን ስለመታው ፊኛው ክፉኛ ተጎድቶ ነበር። በዚያ ላይ ሲገጨው እንጨት ይዞ ሲጫወት ስለነበር እንጨቱ በመኪና ሲመታ ነጥሮ ወግቶት ከፍተኛ ጉዳት አድርሶበታል። በዚህ የተነሳ ልጃቸው ብዙ ጊዜ ታመመ።

ትምህርቱን በሥርዓት መከታተል ባለመቻሉም ዘንድሮ ሰባተኛ ክፍልን ደግሞ እየተማረ ይገኛል። በእርግጥ በአደጋው ብቻ ሳይሆን በቤቱም ምክንያት ነው ሰባተኛ ክፍልን ሊደግም የቻለው። ቤቱ ጠባብ በመሆኑ ቁጭ ብሎ የሚያጠናበት ቦታ የለውም። የሚያስጠናውም የለም። እሳቸውም ቢሆኑ የቀለም ትምህርት ባለመማራቸው አያስጠኑትም። ባለቤታቸውም እንዲሁ ።

ቤቱ ልጆች የሚያጠኑበት ቀርቶ የሚያድሩበት እንኳን አይደለም የሚሉት ወይዘሮ ብርሃኔ፤ ማታ ማታ ሁልጊዜ ራታቸውን ካበሏቸው በኋላ ለአዳር በአካባቢው ያሉ ዘመዶቻቸው ጋር እንደሚልኳቸውም ገልፀውልናል። እሳቸውና ባለቤታቸውም ቢሆኑ የአንድ ዓመት ከሦስት ወር ሕፃን ልጃቸውን ይዘው ተራ በተራ እየተጠባበቁ ነው የሚተኙት። ምክንያቱም ይህ ካልሆነ መኪናው በላያቸው ላይ ወጥቶ ቤታቸውን ደምስሶ እነርሱንም ያጠፋቸዋል። ስለዚህም ከመሞት መሰንበትን አስቀድመው በተራ ይተኛሉ። የቤቱ ጥበትም ቢሆን ተራ በተራ እንጂ በጋራ የሚያስተኛቸው አይደለም። እናም ወይዘሮ ብርሃኔ እንደሚሉት ዘወትር ምግብ የሚበላውም ሆነ ቡና የሚጠጣው አልጋ ላይ ተቀምጦ ነው። አልጋ ቢባል ደግሞ እዛው ከቤቱ ቆርቆሮ ጋር እንደ አልጋ ተመሳስሎ የተመታ እንጨት እንጂ የዕውነት አልጋ አይደለም። ልጆቹን እራት እያበሉ ዘመድ ቤት እንዲያድሩ የሚልኩትም ለዚሁም ሲሉ ነው።

ወይዘሮ ብርሃኔ ቆርቆሮ በቆርቆሮ በሆነው የቀበሌ ቤታቸው የሚያዩት አበሳ በዚህ ብቻ አያበቃም። ራሳቸውን ከስጋቱ ለመታደግ ከባለቤታቸው ጋር እየተጠባበቁ ተራ በተራ ቢተኙም እንቅልፋቸው እንዲህ በቀላሉ አይመጣም። ምክንያቱም በአካባቢው በርካታ መጠጥ ቤቶች አሉ። ከጎናቸው ደግሞ ሙዚቃ ቤት ይገኛል። ባለ ሙዚቃ ቤቱ 24 ሰዓት ሙዚቃ ያስጮሃል። ከዚሁ አጠገብ ያለው ሥጋ ቤት ጋርም ድራፍት ይሸጣል። ከእሱ ጎንም እንዲሁ መሸታ ቤት ነው የሚገኘው። ጩኸቱና ጫጫታው የጉድ ነው።

አረቄና ድራፍት ቤት ያሉት ተጠቃሚዎች ሲሰክሩ ጠርሙስና ድንጋይ ይወራወራሉ። የሚወረወረው ድንጋይ የሚያርፈው ደግሞ እሳቸው ጣሪያ ላይ ነው። አንዳንዴም እነሱ ላይ አርፎ ለጉዳት የሚዳረጉበት አጋጣሚ አለ። በተጨማሪም ቤቱ ፊት ለፊቱ አፉን የከፈተ ትልቅ የቱቦ ገንዳ ስለሚገኝ በአካባቢው የሚኖሩና መፀዳጃ ቤት የሌላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ማልደው ሰገራቸውን በባልዲ እየሞሉና እያመጡ ይደፉበታል። ከጎናቸውም ሌላ ቱቦ አለ። ይሄም ቱቦ ለተመሳሳይ ተግባር ይውላል። በዚህ ሽታም ወይዘሮ ብርሃኔና ቤተሰባቸው ተደጋጋሚ የጤና ችግር እያጋጠማቸው ነው የሚኖሩት።

አሁን በቅርቡ የአንድ ዓመት ከሦስት ወሩ ልጃቸው በሳንባ ምች ተይዟል ተብሎ ሆስፒታል ለሆስፒታል እየተመላለሱ ይገኛሉ። ለሳንባው ሽታ እንዳያገኘው በጣም ጥንቃቄ አድርጊለት፤ ምግብም በቤት ውስጥ አታብስይ ቢባሉም አማራጭ በማጣታቸው የሐኪሙን ትዕዛዝ ሊተገብሩት አልቻሉም። እንደመፍትሔ የወሰዱት ተለዋጭ ቤት እንዲሰጣቸው ቀበሌ መመላለስን ነው። ለቀበሌው‹‹ቤቱ ለልጆቹ ጤና ጠንቅ ነውና ተለዋጭ ይሰጣቸው›› ተብሎ ከጤና ጣቢያና ከሚመለከተው ሌላ አካል የተሰጣቸውን ማስረጃና ማመልከቻ አስገብተዋል። ሆኖም እሳቸው ያሉበትም ቤት ሆኖ ‹‹አንቺ ቤት ይዘሽ ቤት ትጠይቂያለሽ መጠለያ እንኳን የሌለው አለ›› የሚል ምላሽ ነው የተሰጣቸው።

ይሄንኑ ለኃላፊው ለመንገር በተደጋጋሚ ቢሄዱም ሊያገኙት ያልቻሉት ወይዘሮ ብርሃኔ፤ ዓይናቸው እንባ እንዳቆረዘዘ ‹‹ልጆቼ አንድ ቤት ተሰብስበው መኝታ አግኝተው የሚያርፉበትን ቀን እናፍቃለሁ›› ይላሉ። ያለባቸው ችግር ጊዜ የሚሰጥ አይደለም። ማስረጃ ካላቸው ደግሞ መፍትሔ መስጠቱ አስፈላጊ ነው። እናም ቀበሌው የችግራቸውን ክብደት ተመልክቶ መፍትሔ ቢቸራቸው ሲል መልካም እንደሆነ በመጠቆም ለዛሬ የያዝነውን አበቃን።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የሀብትና የመልካም ልብ ባለቤቱ ስኬታማ ወጣት

**አንተነህ ቸሬ**

‹‹ገንዘብ በ30 ፣ ልብ በ40 ›› ሲባል ደጋግመን እንሰማለን:: አንዳንዶች በወጣትነት እድሜያቸው የገንዘብ ባለቤት ይሆኑና ልጅነት ይዟቸው፣ማስተዋል አጥሯቸው ገንዘብ ያባክናሉ፤ በአንጻሩ እነዚህ በወጣትነታቸው በገንዘብ የተንበሸበሹ በጉልምስና እድሜያቸው ማስተዋሉን ያገኙና ገንዘብ ሲያጥራቸው ይስተዋላሉ:: እነዚህን ሁለት የህይወት ገጽታዎች የተመለከቱ ታዲያ ይህን አይነቱን ህይወት ‹‹ገንዘብ በ30፣ ልብ በ40›› በሚለው ብሂል ይገልጹታል::

ሰው በእድሜው እየተማረ የሚሄድ ፍጡር እንደመሆኑ መጠን የማስተዋል መሳሪያ የሆነውን ልብ የሚያገኘው እድሜው እየጨመረና በሕይወት የጉዞ ውጣ ውረድ ሂደት ብዙ ነገሮችን እየተመለከተና እያወቀ ሲሄድ መሆኑ ይታመናል:: ገንዘባቸው ልባቸውን ቀድሞ መጥቶ ገንዘብን በጥሩ ልብ መምራት ሳይሆንላቸው ቀርቶ ‹‹ ምነው ያኔ ከገንዘቡ ጋር ልቡም ኖሮኝ ቢሆን?!›› እያሉ ለገንዘብ ቅርብ፣ ለልብ ሩቅ ሆነው ያሳለፉትን ዘመናቸውን በቁጭት የሚያስታውሱ ብዙዎች ናቸው::

ጥቂት ቢሆኑም ሀብትንም ብስለትንም በአንድ ጊዜ፣ ያውም በጠዋቱ፣ የሚጨብጡትና ይዘው የሚያቆዩ አስደናቂ ሰዎችም አሉ:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች ሕይወት ገና በጠዋቱ ብዙ ያስተማረቻቸው፣ የሕይወትን ትምህርትና ልምድ በማስተዋል የተገበሩ፣ ያላቸውን ለሌሎች በማካፈል በፅኑ የሚያምኑ እና ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች መሆን የሚችሉ አርዓያዎች ናቸው:: ገንዘባቸው ልባቸውን ሳይቀድም የሚመጣላቸውና ልባቸውን ለገንዘባቸው መምሪያና ማስተዳደሪያ በብቃት የመጠቀም ችሎታ ያላቸውም ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ለገንዘብ ቅርብ የሆኑትን ያህል ለልብም ቅርብ ናቸው:: የዛሬው የ‹‹ስኬት›› አምድ ባለታሪክ የሆነው የ29 ዓመቱ ብሩክ አበራም ሀብትና ልብ በአንድ ላይ ተገናኝተው እውነተኛ ስኬትን ያጎናፀፉት ወጣት ነው::

ብሩክ አበራ የተወለደው በሲዳማ ክልል፣ በንሳ ወረዳ ነው:: አባቱ ልጆቻቸው ጠንካራና ስኬታማ እንዲሆኑላቸው ትልቅ ምኞት ስለነበራቸው ‹‹ልጆቼ የከተማ ባህርይ እንዳያዘናጋቸው›› ብለው እነብሩክን ትምህርት ቤት ያስገቧቸው ከሚኖሩበት ቦታ ትንሽ ራቅ ያለ ቀበሌ ውስጥ ነው:: ብሩክ አራተኛ ክፍል ሲደርስ ሃዋሳ ሐይቅ ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርቱን ተከታትሏል:: በእርግጥ ብሩክ ዛሬ ላይ ሆኖ ነገሮችን መለስ ብሎ ሲያስታውስ አባቱ የመረጡት መንገድ ጠቅሞት ለስኬት አብቅቶታል::

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የመጀመሪያ ድግሪውን ይዞ በ2005 ዓ.ም ከቤተሰብ ባገኘው 40ሺ ብር መነሻ ካፒታል በተማረበት የሙያ መስክ ተሰማራ:: ‹‹ብሩክ አበራ ኮንስትራክሽን ድርጅት››ን በማቋቋም ከስኬት ትግል ጋር ጉዞውን ጀመረ:: አባቱ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ስለነበሩ ስለንግድ ስራ እየሰማ አድጓል:: ይህም እርሱም የራሱን ስራ እንዲጀምር መነሻ ሆኖ አግዞታል::

የግንባታ ጨረታዎችን በማሸነፍ ስራውን ቀጠለ:: ለስራዎቹ የፈረማቸውን ውሎች አክብሮ በተለያዩ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ የአስተዳደር ሕንፃዎችንና ሌሎች ግንባታዎችን አጠናቅቆ በማስረከብ ምስጋናና ሽልማቶችን ማግኘት ችሏል:: ድርጅቱ ካከናወናቸው ግንባታዎች መካከል በሲዳማ ክልል፣ በስልጤ እና በጋሞ ዞኖች የሚገኙ የጤና፣ የትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ተጠቃሽ ናቸው::

‹‹ብሩክ አበራ ኮንስትራክሽን ድርጅት›› በስራ ላይ ከተሰማራበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ 17 የግንባታ ፕሮጀክቶችን አጠናቅቆ አስረክቧል፤ በአሁኑ ወቅት በ240 ሚሊዮን ብር የሚገነባውን የሐዋሳ አዳሪ ትምህርት ቤትን (Boarding School) ጨምሮ ሁለት የግንባታ ፕሮጀክቶችን እያከናወነ ይገኛል:: ‹‹ጨረታ አሸንፈን የወሰድናቸውን ስራዎች በታማኝነትና ቃል በገባነው መሰረት አጠናቅቀን ማስረከባችን ስኬታማ አድርጎናል:: በአጠቃላይ የስኬታችን አንዱ ምክንያት በታማኝነት ማገልገላችን ነው›› በማለት ይገልፃል::

ብሩክ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ብቻ ተወስኖ መቅረት አልፈለገም:: ከዚህ ስራው የሚያገኘውን ትርፍ ወደ ሌላ



ብሩክ አበራ

ተጨማሪ ስራ ለማስፋት ወሰነ:: ከኮንስትራክሽን ስራው ያገኘውን ትርፍ ወደ ሌላ የንግድ ዘርፍ በማሸጋገር ከባንክ ጋር ትስስር ፈጥሮ በ2010 ዓ.ም በቡና ንግድ ላይ ተሰማርቶ መስራት ጀመረ:: ‹‹ዶና ኮፊ›› የተሰኘው የቡና ድርጅቱ በሲዳማ ክልል በአራት ወረዳዎች (አርቤጎና፣ በንሳ፣ ሆኮ እና ጭሪ ወረዳዎች) በቡና ልማትና ንግድ ላይ እየሰራ ነው:: ዘንድሮ ደግሞ ቡናን ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ላይ መሳተፍ ጀምሯል:: በቡና ምርት ታዋቂ ከሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች አንዱ የሆነው የሲዳማ ክልል ለብሩክ የቡና ልማትና ንግድ ስራ ጥሩ እድል እንደሚፈጥርለት አያጠራጥርም::

ባለፈው ዓመት ከቡና ሽያጭ እስካሁን ድረስ ተገኝቶ የማያውቅ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ያገኘችው ኢትዮጵያ፤ ዘንድሮም በቡና ኤክስፖርት ከአምናው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ አቅዳለች:: ለዚህ እቅድ መሳካት ደግሞ በዘርፉ የተሰማሩ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ትጋትና ቅንጅት ያስፈልጋል:: በዚህ ረገድ የብሩክ ‹‹ዶና ኮፊ›› ጥራቱን የጠበቀ ቡና ለውጭ ገበያ በማቅረብ ለሀገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ብሩክ ይናገራል:: ‹‹በቻልነው መጠን በቂ የሆነና ጥራት ያለው ቡና አዘጋጅተን ኤክስፖርት በማድረግ ለሀገራችን ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማስገኘት ጠንክረን እየሰራን ነው›› ይላል::

ብሩክ አበራ ገና በ29 ዓመቱ የቢሊየነርነት ደጅ ላይ ደርሷል:: ከቤተሰብ ባገኘው 40ሺ ብር መነሻ ካፒታል የጀመረው ስራው ዛሬ ከ700 እስከ 800 ሚሊዮን ብር ካፒታል ላይ ደርሷል:: ‹‹ስኬት የሚገኘው በግል ጥረት ብቻ ሳይሆን በፈጣሪ እርዳታም ጭምር ነው›› የሚለው ስኬታማው ወጣት ብሩክ አበራ፤ ለስኬት ለመብቃት የግል ጥረት ወሳኝና አስፈላጊ ነገር መሆኑን ይገልጻል፤ ጊዜና ትኩረትን ለስራ መስጠት እንደሚያስፈልግም በአፅንዖት ይናገራል::

ብሩክ በወጣትነቱ የገንዘብ ሀብታም መሆን የቻለ ሰው ብቻ አይደለም፤ገና በወጣትነቱ ልባምነትንም የታደለ ነው:: ልባም ለመባል ያበቃው ሀብት እንዲያፈራ ያስቻለው ትጉህ ሰራተኛነቱ ብቻ ሳይሆን ያለውን ሀብት ለሌሎች የማካፈል ባህርይው ነው:: ‹‹ትናንትናን አለመርሳት ያለህን ለሌሎች ለማካፈል ያግዛል›› የሚለው ብሩክ፣ ያለፈበትን የሕይወት ጉዞ አለመርሳቱ ሀብቱን ለሌሎች ለማካፈል እንዳስቻለው ይገልፃል:: ብሩክ በአሁኑ ወቅት በሲዳማ ክልል በሐዋሳ ከተማ፣ በቦሪቻ እና አርቤጎና ወረዳዎች ቢሮዎችን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎት መስጫዎችን የሚያካትቱ ሦስት ትምህርት ቤቶችን በበጎ ፈቃደኝነት እያስገነባ ይገኛል::

‹‹ኢትዮጵያ ውስጥ የተወለደና ያደገ አብዛኛው ሰው በድህነት ህይወት ውስጥ ያሳለፈ መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: ያሳለፍነውን ጊዜ ብናስብ አብዛኞቻችን የተማርነው ጥራቱን ባልጠበቀ ትምህርት ቤት ውስጥ እንደሆነ እንገነዘባለን:: እኔ ሁለተኛና ሦስተኛ ክፍል

**‹‹ስራችን በዚህ ብቻ አይቆምም:: ሀብትን አከማችቶ ለብቻ በመኖር ደስተኛ መሆን አይቻልም:: የመጣንበትን አለመርሳት እንዲሁም ያለንን እያካፈልን መስራትና መኖር ስላለብን በቀጣይ ጊዜያትም የኅብረተሰቡን ችግር ሊያቃልሉ የሚችሉ ሌሎች ስራዎችን እንሰራለን››**

የተማርኩት ከጭቃ በተሰራ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው:: ይህን ሳስታውስ ለአሁኑና ለመጪው ትወልድ የተሻለ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ አስባለሁ›› በማለት ትናንት ያሳለፈው ሕይወቱ ለዛሬ የበጎ አድራጎት ስራው መነሻ እንደሆነለት ያስረዳል::

ብሩክ የክልሉ መንግሥት፣ ባለሀብቶች ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ተግባር ላይ እንዲሳተፉና እንዲያግዙ ያቀረበውን ጥሪ ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ የዋጋ ስሌት እያንዳንዳቸው ሦስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር የሚፈጁ (የግብዓት ዋጋ በየጊዜው ስለሚጨምር ዋጋው ሊጨምር እንደሚችል ይታሰባል) ሦስት ትምህርት ቤቶችን እያስገነባ ነው:: የትምህርት ቤቶቹ ግንባታ ከተጀመረ ሁለት ወራት ተቆጥረዋል፤ የቦሪቻው ትምህርት ቤት ከአንድ ወር በኋላ፣ የአርቤጎናው ከሦስት ወራት በኋላ እና የሀዋሳው ደግሞ ከሁለት ወራት በኋላ ተጠናቅቀው ለአገልግሎት ዝግጁ ይሆናሉ::

‹‹በአንድ ክፍል ውስጥ 100 ተማሪዎች ሲማሩ እናያለን:: ሐዋሳ፣ አዲስ አበባ ወይም ሌሎች ትልልቅ ከተሞች ላይ ያለውን በመመልከት ብቻ ትምህርትና ጤና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በበቂ ሁኔታ የተዳረሰ ሊመስለን ይችላል:: ወደ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ስንሄድ ግን ሽፋኑ በጣም ገና እንደሆነ እንታዘባለን::›› የሚለው ብሩክ፣ በብዙ ወረዳዎች ላይ ደረጃቸውን የጠበቁ ትምህርት ቤቶች እንደሌሉም ይናገራል::

ብሩክ ሲዳማ ውስጥ ካሉ 36 ወረዳዎች መካከል እኔ 12 ወረዳዎች ላይ ያለውን ሁኔታ እንደሚያውቅ ይገልጻል:: በአንድ ወቅት አርቤጎና ወረዳ ውስጥ አንድ ቀበሌ ላይ የአካባቢው ነዋሪዎች እንጨት አዋጥተው፣ አራት ክፍል ትምህርት ቤት ሰርተው ጣሪያ ማልበስ ሲቀራቸው ተመልክቶ ሁኔታቸው አንጀቱን ይበላዋል፤ 80 ቆርቆሮዎችን ገዝቶም ይሰጣቸዋል::

‹‹ትናንት የነበርክበትን ስታስብና ስታስተውል የምታደርገውን ነገር በጥልቅ የማካፈልና የመስጠት ስሜት ነው የምታደርገው:: እንዲህ ዓይነት ስራ የምትሰራው ከዚያ ላይ የምታገኘውን ትርፍ ታሳቢ በማድረግ አይደለም:: የክልሉ መንግሥት ባቀረበው ገለፃ ላይ ትምህርት ገና እንዳልተዳረሰና ጥራቱም ገና እንደሆነ ተመልክተናል:: እኔ ብቻ ሳልሆን በሲዳማ ክልል ውስጥ ያሉ ሌሎች ባለሀብቶችም በትምህርት ቤቶች ግንባታ እየተሳተፉ ነው›› በማለት ባለሀብቶች በትምህርት ዘርፍ ስለሚያከናውኑት የበጎ ፈቃድ ስራዎችም ያስረዳል::

ያለውን ሀብት በማካፈል መርህ በፅኑ የሚያምነው ብሩክ፣ ‹‹ትናንት የነበርክበትንና መጪውን ትውልድ ካሰብክ ያለህን ማካፈል አይከብድህም:: ንግድና ሀብት ወሰን የለውም፤አያልቅም:: ባለቤቱ ግን ያልቃል:: ስለዚህ ባለሀብቶች ከማለቃቸውና ከማለፋቸው በፊት ሀብታቸውን ለሌሎች ማካፈል አለባቸው:: ሀብትን ማካፈል ለራስ ህሊና ሰላም ይሰጣል፤ሌላውን ሰው ይጠቅማል ሲል ያስገነዝባል:: ‹‹ካለው ነገር አካፍሎ ስራ የሚሰራ ሰው፣ ኅብረተሰቡን በተለይም መጪውን ትውልድ የሚጠቅም ትልቅ ስራ እየሰራ እንደሆነ መገንዘብ አለበት›› በማለት የገንዘብ ባለቤት የሆኑ ሰዎች ከገንዘቡ በተጨማሪ የልብ ባለቤትም እንዲሆኑ ይመክራል::

‹‹ስራችን በዚህ ብቻ አይቆምም:: ሀብትን አከማችቶ ለብቻ በመኖር ደስተኛ መሆን አይቻልም:: የመጣንበትን አለመርሳት እንዲሁም ያለንን እያካፈልን መስራትና መኖር ስላለብን በቀጣይ ጊዜያትም የኅብረተሰቡን ችግር ሊያቃልሉ የሚችሉ ሌሎች ስራዎችን እንሰራለን›› በማለት አሁን እየሰራቸው ካሉ ማኅበረሰብ ተኮር የመሰረተ ልማት ስራዎች በተጨማሪ በሌሎች ስራዎች ላይም የመሳተፍ በጎ እቅድ እንዳለው ይናገራል::

ብሩክ እዚህ ደረጃ ለመድረስ ጉዞው ቀላል እንዳልነበር ያስረዳል። የአሁኑ ስኬቱ በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፎና ጫናዎችን ተቋቁሞ የተገኘ ድል ነው። ያሳለፋቸውን ጊዜያት ዛሬ ላይ ሆኖ ሲያስታውሳቸው የዛሬው ስኬቱ በቀላሉ እንዳልተገኘ ይገነዘባል። ለአብነት ያህል ስራ በጀመረ በሁለተኛው ዓመት በ2007 ዓ.ም በስራ መኪናዎች ላይ የደረሰውን ውድመት እንደአንድ ፈተና የሚስታውሰው ብሩክ፣ ‹‹ቢዝነስ ብዙ ፈተናዎች አሉት፤ሀብት መፍጠር ቀላል ነገር አይደለም:: በፈጣሪ እርዳታና በትጋታችን ፈተናዎቹን አልፈን አሁን ላለንበት ጥሩ ደረጃ ደርሰናል›› በማለት ይናገራል::

‹‹መስጠትና ማካፈል ከፈጣሪ የሚገኝ ስጦታም ጭምር ነው›› የሚለውና ሁሉንም የበጎ አድራጎት ስራዎቹን ዘርዝሮ ከመናገር ይልቅ ትህትናን የመረጠው ብሩክ አበራ፣ ባለትዳርና የሦስት ልጆች አባት ነው:: ‹‹ለዛሬው ስኬቴ መሰረትና አርዓያ የሆኑኝን ቤተሰቦቼን አመሰግናለሁ›› ይላል::

ወጣቶች ገንዘብ ለመስራትና ሀብት ለማፍራት ቀጥተኛ ያልሆኑ መንገዶችን ከመከተል እንዲቆጠቡና መንግሥት ደግሞ ወጣቶቹ ውጤታማ እንዲሆኑ በጥናት ላይ የተመሰረተ የፋይናንስና ሌሎች ግብዓቶች ድጋፍ እንዲያደርግም ይመክራል:: የወጣቱን እውቀትና የመንግሥትን ፋይናንስ በማጣመር የተሻለ ውጤት ማግኘት እንደሚቻልም ነው ያመለከተው::

‹‹በወጣትነታችን በትጋትና በፍጥነት ሰርተን ሀገርን ለመጥቀም መረባረብ አለብን›› የሚለው ስኬታማው ወጣት ብሩክ አበራ፣ ሌሎች ትልልቅ እቅዶችም አሉት:: አርቤጎና ወረዳ ላይ በቀን 24ሺ ሊትር የሚያመርት የውሃ ፋብሪካ የመገንባት፣ የቡና ልማትና ንግድ ስራውን በማስፋት በብዛት በቀጥታ ለውጭ ገበያ የማቅረብ፣ በሐዋሳ ከተማ በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥራቱን የጠበቀ ሪዞርት እንዲሁም በተሻለ ጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርብ የመኖሪያ አፓርታማ (G+10) የመገንባት፣ የስሚንቶ ፋብሪካ የማቋቋም እና በማዕድን ልማት ዘርፍ የመሰማራት እቅዶችን ለማሳካት እየሰራ ነው::

# ስፖርት





# አወዛጋቢው የፊፋ የሀገራት ወርሐዊ ደረጃ

ቦጋለ አበበ

ፊፋ የሀገራትን የእግር ኳስ ደረጃ ይፋ ሲያደርግ ኢትዮጵያ ከነበረችበት ደረጃ መሻሻል አላሳየችም። በዚህም ከነበራት ደረጃ ከፍም ዝቅም ሳትል ከዓለም 138ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 41ኛ ደረጃ ላይ ልትቀመጥ ችላለች። ይህም ባለፉት ጥቂት ወራት ዋልያዎቹ የአቋም መለኪያም ይሁን ሌሎች ጨዋታዎችን ባለማድረጋቸው ምክንያት የደረጃ ለውጥ ማምጣት እንዳልተቻለ ታውቋል።

ሁልጊዜም አወዛጋቢ በሆነው የፊፋ የሀገራት ደረጃ አሰጣጥ በኳታሩ የዓለም ዋንጫ የግማሽ ፍጻሜ ተፋላሚ በመሆን የመጀመሪያዋ አፍሪካዊት ሀገር የሆነችው ሞሮኮ የአፍሪካን ቀዳሚ ደረጃ ከሴኔጋል ተረክባለች። የዓለም ዋንጫው ክስተት የሆኑት የአትላስ አንበሶች ሀገር የሆነችው ሞሮኮ 11 ደረጃዎችን አሻሽላ ከዓለም 11ኛ ደረጃ ላይ መቀመጥ ችላለች። ይህም በትልቁ የዓለም ዋንጫ መድረክ ከምርጥ አራት ቡድኖች አንዷ ሆና ሳለ ቢያንስ ከአስሩ የዓለም ደረጃ ውስጥ አለመካተቷ በርካቶችን ያስገረመ ሆኗል። ሞሮኮ በዓለም ትልቁ ደረጃዋ 10ኛ ሲሆን ይህም እኤአ 1998 ላይ ያስመዘገበችው ነው። የአትላስ አናብስት ዝቅተኛ ደረጃቸው 92ኛ ሲሆን እኤአ 2015 ላይ ያስመዘገቡት ነው።

ከአትላስ አንበሶች በተጨማሪ የዓለም ዋንጫውን ያነሳችው አርጀንቲና በዓለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ ስትቀመጥ በሩብ ፍጻሜ ፍልሚያ የተሰናበተችው ብራዚል በአንጻሩ ከዓለም አንደኛ ሆና መቀመጧ ብዙዎችን ግራ አጋብቷል።




ፊፋ ወርሐዊ የሀገራትን ደረጃ ማውጣት የጀመረው እኤአ ከ1992 አንስቶ ሲሆን ደረጃውን የሚሰጠውም ሀገራት በተቀመጠው ወር ውስጥ በሚያስመዘግቡት ነጥብ መሠረት ነው። ፊፋ ለሀገራት ደረጃ የሚሰጥበትን ስልት እኤአ ከ2018 ወዲህ የለወጠ ሲሆን በአዲሱ ስሌት መሠረት ሀገራት የሚሰጣቸው ደረጃ በወር ውስጥ ከሚያስቆጥሩት አማካኝ ነጥብ ይልቅ ሀገራት ቀደም ሲል የነበራቸው አጠቃላይ ነጥብ ላይ የሚያስመዘግቡትን አዲስ ነጥብ በመደመር ወይም በመቀነስ ነው። በዚህም መሠረት ሀገራት የሚያስመዘግቡትን ነጥብ ለመደመር ወይም ለመቀነስ የሚገጥሙት ሀገር እንደሚገኝበት ደረጃ ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ ያህል ከአንድ እስከ አስር ደረጃ ውስጥ የሚገኝ አገርን ማሸነፍ ከአስር በላይ ደረጃ ውስጥ የሚገኝ አገርን ከማሸነፍ የተሻለ ነጥብ ያስገኛል። ከዚህ በተጨማሪ የውድድር መድረኮች ደረጃም የነጥብ አሰጣጡ ላይ ልዩነት ይፈጥራል። ለምሳሌ አንድ ሀገር የዓለም ዋንጫ ላይ አሸንፎ የሚያገኘው ነጥብ የወዳጅነት ጨዋታዎች ላይ አሸንፎ ከሚሰጠው ነጥብ ይበልጣል። እንደ ዓለም ዋንጫ፣አፍሪካ ዋንጫ፣አውሮፓ ዋንጫ ወዘተ ባሉ ውድድሮች ላይ ሀገራት በጥሎ ማለፍ ጨዋታ ቢሸነፉ የሚቀነስባቸው ነጥብ አይኖርም። አንድ አገር በመለያ ምት ቢሸነፍ ነጥብ አይቀነስበትም፣ እንዲያውም አንድ ነጥብ ከጨዋታው ያገኛል። ፊፋ ለሀገራት ደረጃ የሚሰጠው እነዚህንና ሌሎች በርካታ ነጥቦችን ከግምት በማስገባት ነው።

በዚህ መሠረት ለምሳሌ ሞሮኮ በዓለም ዋንጫው ብዙ ግብ ካለማስተናገዷ በተጨማሪ በፊፋ የደረጃ ሰንጠረዥ 2ኛ ላይ የነበረችው ቤልጂየምን፣ፖርቹጋልና ስፔንን አሸንፋለች። ሦስቱም ሀገራት በፊፋ ደረጃ አስር ውስጥ የነበሩ ሲሆን ስፔንን ብቻ ነው በመለያ ምት ያሸነፈችው። ይህም በዓለም ዋንጫ አራተኛ ሆና ከማጠናቀቋ ጋር ተደምሮ ቢያንስ ከዓለም አስሩ የመጀመሪያ ደረጃዎች ውስጥ መግባት ነበረባት የሚሉ ክርክሮችን ያስነሳል።

በተመሳሳይ የዓለም ዋንጫው ሻምፒዮን አርጀንቲና ከዓለም ዋንጫው አስቀድሞ 37 ጨዋታዎችን ያለመሸነፍ ጉዞ አድርጋ በሳውዲ ዓረቢያ ብቻ ነው የተሸነፈችው። ሻምፒዮን እስከሆነችበት ጉዞ ድረስም ጥሩ ደረጃ ያላቸው የአውሮፓ ሀገራትን ማሸነፍ ችላለች። ብራዚል በአንጻሩ በዓለም ዋንጫው ከሩብ ፍጻሜ የዘለለ ስኬት ማስመዝገብ ካለመቻሏ በተጨማሪ በአንጻራዊነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በምትገኘው ካሜሩን በምድብ ጨዋታ መሸነፏ ይታወቃል። ከዚህ አኳያ ብራዚል አርጀንቲናን በልጣ የዓለም ቁንጮ ሆና መቀመጧ ለብዙዎች የሚዋጥ አልሆነም።

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ብዙ ደምሴ የሰሌዳ ቁጥር 1-40757 ኦሮ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ30/03/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የአዳማ ከተማ መስተዳደር ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

## አማራ ክልል

ንብረትነቱ የሰቆጣ ወ/ፖሊስ ጽ/ቤት የሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ሰሌዳ ኮድ ፖሊስ 0090 አማ ሊብሬው የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በቀን 19/07/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ይህን ሊብሬ ወይቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአብክመ ትራንስፖርት ሎጅስቲክ ባለሥልጣን የደቡብ ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ቡድን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በአመልካች ወ/ሮ ፋሲካ ባልቻ ያኢ እና በተጠሪ ዶ/ር ወንደወሰን ሌሊሳ ሻቦ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተጠሪ ዶ/ር ወንደወሰን ሌሊሳ ሻቦ ለ26/04/2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 3:40 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ 6ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም ተመስገን ዮሀንስ ይማም የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B13421የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-0415073 ሞዴል UA-SCP10-AHPNK V የሞተር ቁጥር 1SZ 1051255 የሊብሬ ቁጥር 235894 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 5/4/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ተመስገን ዮሀንስ ይማም የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B13422 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-3289880 ሞዴል TA-SCP10-AHPNK የሞተር ቁጥር 1SZ 0885211 የሊብሬ ቁጥር 235790 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 5/4/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ጫልቱ ሙሊታ ጅሩ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B69048 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር KSP90-5214346 ሞዴል DBA-KSP90-AHXDK-B የሞተር ቁጥር 1KR-1131603 የሊብሬ ቁጥር 182725 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 30/3/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ወርቁ ጉርሙ ሰንበታ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A24651 የተሽከርካሪዉ አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H5F7P26756 ሞዴል NPR71 የሞተር ቁጥር 4HG1-380275 የሊብሬ ቁጥር 393971/027588 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 6/4/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ዐጋዬ ለማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-41692 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻሲ ቁጥር JT1G0AL2000017533 ሞዴል ALZOL-ZGMDSW የሞተር ቁጥር 2A-1395430 የሊብሬ ቁጥር 174181 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 3/4/2015ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አበበ አሰፋ ብሩ የሰሌዳ ቁጥር አአ 01-01-02401 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻሲ ቁጥር RN80-5001325 ሞዴል RN80- የሞተር ቁጥር 22R-2641291 የሊብሬ ቁጥር 339341 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ11/4/2015ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገርዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፉአድ ሲራጅ ኢሳ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A12059 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JAAKP34H0F7P00369 ሞዴል NPR71 የሞተር ቁጥር 4HG1-265036 የሊብሬ ቁጥር 142299 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ5/4/2015 አመልክተዋል፡ ፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ሶፎንያስ አስማረ ነጋሽ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-44783 የተሽከርካሪዉ አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር YN57-0009300 ሞዴል yn57 የሞተር ቁጥር 3Y-0151134 የሊብሬ ቁጥር 526878 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ4/4/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ከተማ ፈየራ ቀዲዳ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A27478 የተሽከርካሪዉ አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር JALK6A132E7103858 ሞዴል FSR6MF የሞተር ቁጥር 6HH1-478281 የሊብሬ ቁጥር 415931 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ23/3/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ 15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የአቃቂ ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**